# አማርኛ

## እንደ መጀመሪያ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ



፯ኛ ክፍል

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## የተማሪ መፅሐፍ

## ፮ (6) ክፍል


አዘጋጆች

ዐፀደማርያም ሲሻው ወግደረሰኝ

ዳንኤል ገላነው ምህረት

ጉድብ ንጉሴ ካሳ

ገምጋሚዎችና አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወልደመድህን

ትንቢት ግርማ ሐይሉ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬህይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ



አቀማመጥ እና ስዕል

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ(TMS)

© የመፅሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው::

# ምስጋና

የይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፐሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ፣ እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም ሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪ ጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ


| ይዘት | ገፅ |
|---|---|
| መግቢያ ..................................................................... | IV |
| **ምዕራፍ አንድ** | |
| ባህላዊ አለባበስ..................................................... | 1 |
| **ምዕራፍ ሁለት** | |
| ታዋቂ አትሌቶች.................................................... | 14 |
| **ምዕራፍ ሦስት** | |
| ቃላዊ ግጥም.......................................................... | 26 |
| **ምዕራፍ አራት** | |
| ዘመናዊ ግብርና..................................................... | 43 |
| **ምዕራፍ አምስት** | |
| ቱሪዝም.................................................................. | 59 |
| **ምዕራፍ ስድስት** | |
| ጸረ- አደንዛዥ እጾች............................................ | 76 |
| **ምዕራፍ ሰባት** | |
| የጥላቻ ንግግር.................................................... | 90 |
| **ምዕራፍ ስምንት** | |
| ኤች አይ ቪ ኤድስ.............................................. | 103 |
| **ምዕራፍ ዘጠኝ** | |
| ባህላዊ ልማዶች.................................................. | 116 |
| **ምዕራፍ አስር** | |
| ሴቶችን ማብቃት.................................................. | 130 |
| አባሪ......................................................................... | 147 |
| ዋቢ ጽሑፎች............................................................ | 150 |

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት ለሚማሩ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤በተጨማሪም የቃላት እና የሰዋስው ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው። ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ለዚህ የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትና ለሚሰጠው የትምህርት ሽፋን መረጃ ይሰጣል። ከዚህም በላይ ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## መሰረታዊ መርሆዎች

- ✧ ተማሪዎች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ።
- ✧ ለእነዚህ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ።
- ✧ በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ።
- ✧ ስለእነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ጽሑፍ ይጽፋሉ።
- ✧ አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል ሶስትና አምስት የቀረቡትን የቃላትና የሰዋስው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ።
- ✧ ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ጓደኞቻቸው ጋር ይማራሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ:: ከእነዚህ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል::

፩. የየዕለቱን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድህረገጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ::

፪. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለ መጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው::

፫. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ:: በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ:: ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤

፬. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤

፭. ስለርዕሰ ጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ::

፮. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ::

፯. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ::

፰. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው:: ለምሳሌ:- የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል /ተሰድረዋል/ ወይ? በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉት ሥርዓተ ነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ? ወዘተ.

፱. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች ለምሳሌ፡- ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ያላቸውን አስተያየት ወዘተ... እንዲጽፉ አበረታቷቸው፡፡

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አንድ
# ባህላዊ አለባበስ

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

ትክክለኛውን አገላለፅ ተጠቅማችሁ በተገቢው ፍጥነት ታነባላችሁ፡፡

የቃላትን አገባባዊ ሥርዓት ተከትላችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ውስብስብ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡


ቃላትን እያጣመራችሁ ታነባላችሁ፡፡

በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው መንገድ ትጠቀማላችሁ፡፡

# ፩ኛ ክፍል


## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ እና መናገር

### የሀገር ባህል ቀሚስ







### ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ከስዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?
2. ከስዕሉ ላይ ምን ምን አይነት ባህላዊ ቀሚሶችን አስተዋላችሁ?

## የማዳመጥ ሂደት

**‹‹የሀገር ባህል ቀሚስ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የምንባቡን ጭምቅ ሀሳብ ለማወቅ ማስታወሻ እየያዛችሁ አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. ባህላዊ ልብሶች በምን በምን አጋጣሚዎች ይለበሳሉ?
2. ባህላዊ አለባበስ ከዘመናዊ አለባበስ በምን ይለያል?
3. ባህላዊ ልብሶች ከምን ከምን ይዘጋጃሉ?
4. በምንባቡ ውስጥ ከቀረበው የባህል አለባበስ ሌላ ምን አይነት ባህላዊ አለባበስ ታውቃላችሁ?
5. ባህላዊ አለባበሶቻችን ጠብቀን ለማቆየት ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል?

### ተግባር ሶስት

**በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ሀ. ትውፊት

ለ. ሀገረኛ

ሐ. ሸማ ሰሪ

መ. በየፈርጁ

ሠ. አጥቢያ

### ተግባር አራት

**የምታውቁትን አንድ ባህላዊ አለባበስ መርጣችሁ ስለዚያ ባህላዊ አለባበስ፣ አሰራርና መቼ እንደሚለበስ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት፦ ንባብ

### ባህላዊ አለባበስ



### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር አንድ

**ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በርዕሱና በምስሉ መካከል ያለውን ዝምድና ግለጹ፡፡
2. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ምን የሚናገር ይመስላችኋል ?

#### ተግባር ሁለት

**ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ፡፡**

| | ነጥሎ ማንበበ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| 1 | በየ - አለባበስ -ኦች - ኣችን | በየአለባበሶቻችን |
| 2 | የ -ሁለንተና - ዊ | የሁለንተናዊ |
| 3 | ከ - አስ- ተዳደግ - ኣችን | ከአስተዳደጋችን |
| 4 | የ - ሚመረት - ኡ - በት -ና | የሚመረቱበትና |
| 5 | ተወዳጅ - ነት - ኣቸው | ተወዳጅነታቸው |
| 6 | የ - ተዥጎረ - ጎረ | የተዥጎረጎረ |
| 7 | ባህል - ነት -ኣቸው - ን | ባህልነታቸው |

## የንባብ ሂደት

**የሚከተለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ ። ስታነቡ ግልፅ ያልሆነ ሀሳብ ሲያጋጥማችሁ በማሳታወሻ ፃፉ።**

ኢትዮጵያዊያን እንደየ ባህላችን በልዩ ልዩ ቅርፅና ቀለማት ያሸበረቁ ባህላዊ አለባበሶች አሉን፡፡ እነዚህ ባህላዊ አለባበሶቻችን የሁላችንም የሁለንተናዊ ማንነታችን መገለጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ውብ የሆነ ያልተበረዘና ያልተከለሰ ባህላዊ አለባበሳችን ሀገራችንን ከሌሎች የአለም ሀገራት እንድትለይ ያደርጋታል፡፡ ባህላዊ አለባበሳችን ከማንነታችን የሚመነጭ ሲሆን ከተለያዩ ሀገራት በሚመጡና እኛም ወደ ተለያዩ ሀገራት ስንሄድ በአሸበረቀው ባህላዊ አለባበሳችን ውበት የሚደነቁት ብዙዎች ናቸው፡፡

ከሌሎች ሀገራት አለባበሶች የኛን ልዩ የሚያደርገው የራሳችንን የፈጠራ ስራ የሚያካትት መሆኑ ነው፡፡ በተለያዩ የደስታና የሀዘን ስሜቶች የምንለብሳቸው ባህላዊ አለባበሶቻችን ለስራው የሚሆኑትን ጥሬ እቃዎች፣ የሚመረቱበትና ወደልብስነት የሚለወጡት በራሳችን ጥበብ ነው፡፡ እንደየባህላችን በተለያዩ ጥልፎች፣ ጌጣጌጦችና ጥበቦች ያሸበረቁ ባህላዊ ልብሶችን ለብሰን ልዩ ልዩ ባህላዊ ክንውኖችን ስንከውን ልዩ ህብር ፈጥሮ ስሜትን ይቀሰቅሳል፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ምን ተረዳችሁ? ቀጣዩስ ክፍል ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

ባህላዊ አለባበሶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አለምአቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡ የተወዳጅነት ሚስጥሩም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ጎብኝዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡ በአለባበሳችን ተማርከው እነሱም የተለያዩ አልባሳትን እየገዙ በመልበስ ሀሴትን መጎናፀፍ ችለዋል፡፡ እነዚህም ባህላዊ አለባበሶች በተለያዩ አመታዊ ክብረበ ዓላትና ህዝባዊ በአላት ማለትም በሰርግ፣ በጥምቅት፣በአረፋና በመውሊድ መሰል አጋጣሚዎች ይለበሳሉ፡፡

እነዚህ ባህላዊ አለባበሶች እንደየ ህብረተሰቡ ባህል በተለያዩ ቀለማት የተዥጎረጎሩ ሆነው በቀሚስ፣በነጠላ፣ በኮትና በሱሪ መልክ ልንለብሳቸው እንችላለን፡፡ የወንድና የሴት፣የወጣቶችና የአዛውንቶች፣ እንደየ እድሜ ደረጃችን የባህሉ አሻራ ያረፈባቸውም ናቸው፡፡ በዚህ መካከል በየአለባበሳችን የባህል ልውውጥ መኖሩን የሚያሳዩ ሲሆን

የማንነታችን መገለጫዎች ከመሆናቸው ባሻገርም አምረንና ተውበን እንድንታይ ያስችላሉ፡፡ ባህላዊ አለባበሳችን ለቀጣዩ ትውልድ የምናወርሳቸው ውድ ቅርሶቻችን ናቸው፡፡ ‹‹ ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም›› እንደሚባለው ባህላዊ አለባበሶቻችንን ለተተኪው ትውልድ ለማስተዋወቅና ለማስተላለፍ እንዲሁም ባህልነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል፡፡

ምንጭ (ፈንታሁን እንግዳ፣2000 ታሪካዊ መዝገበ ሰብዕ ከጥንት እስከዛሬ ለ6ኛ ክፍል ማስተማሪያ ተሻሽሎ የቀረበ፡፡)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ

**ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ ‹‹ እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ‹‹ሐሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡ ለምትሰጡት መልስ ምክንያት አቅርቡ፡፡**

1. ባህላዊ አለባበሶቻችን የማንነታችን መገለጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. ባህላዊ ልብሶቻችን ከሌሎች የሚለዩት የራሳችን የፈጠራ ውጤት በመሆናቸው ነው፡፡
3. ባህላዊ ልብሶቻችን ከጊዜ ወደጊዜ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡
4. የባህል አልባሳትን ይዘት ጠብቆ የማቆየት ድርሻ የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ብቻ ነው፡፡
5. በማህበረሰብ ባህልና እሴት መሰረት ባህላዊ አልባሳት በተለያየ ቅርፅ ይዘጋጃሉ፡፡

### ተግባር ሁለት

**ለሚከሉት አዳዲስ ቃላት በጽሁፍ ፍቺ ስጡ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ቱሪስት | ሐ. ሁለንተናዊ | ሠ. ባህላዊ |
| ለ. ሀሴት | መ. መገለጫ | ረ. ያልተበረዘ |

**ተግባር ሶስት**

**ተማሪዎች ከዚህ በታች ባህላዊ አለባበስ ከሚለው ርዕስ ተቀንጭቦ የቀረበውን ምንባብ በጥንድ በጥንድ በመሆን ደቂቃ እየያዛችሁ በተገቢው ፍጥነት አንብቡ።**

ባህላዊ አለባበሶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አለማቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል። የተወዳጅነት ሚስጥሩም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ጎብኝዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱ ነው። በአለባበሳችን ተማርከው እነሱም የተለያዩ አልባሳትን እየገዙ በመልበስ ሀሴትን መጎናፀፍ ችለዋል። እነዚህም ባህላዊ አለባበሶች በተለያዩ አመታዊ ክብረ በዓላትና ህዝባዊ በዓላት፣በሰርግ፣ በጥምቀት፣በአረፋና በመውሊድ መሰል አጋጣሚዎች ይለበሳሉ።

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### አዳዲስ ቃላት

**ተግባር፡- አንድ**

**ከዚህ በታች በ ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሆኑትን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በጋራ | ሀ. ልዩ |
| 2. ውርስ | ለ. ብቸኛ |
| 3. ደንብ | ሐ. ብዙ |
| 4. ነጠላ | መ. ስርዓት |
| 5. መላምት | ሠ. ግምት |
| 6. ብርቅዬ | ረ. በቡድን |
| | ሰ. ስጦታ |

### ተግባር ሁለት

**ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አውዳዊ ፍቺ መሰረት አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ሀ. ያሽበረቀ
መ. ኣሻራ
ለ. ፈጠራ.
ሠ. አዛውንት
ሐ. አሻራ
ረ. ጥበብ

### ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን አውጡ፡፡**

1. ሀ. አማረረ ለ. አመሰገነ ሐ. አሞገሰ መ. አወደሰ
2. ሀ. ጥድፊያ ለ. ትጋት ሐ. ንቃት መ. ልግመኛ
3. ሀ. ቀላወጠ ለ. ለመነ ሐ. ደከመ መ. ተመፀወተ
4. ሀ. ተወዘፈ ለ. ተዘረጋ ሐ. ተዘረፈጠ መ. ተጎለተ
5. ሀ. እንደነገሩ ለ. ለይስሙላ ሐ. ለማስመሰል መ. ለቁም ነገር

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### አንቀፅ

### ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች የቀረበውን ጅምር ቢጋር መነሻ በማድረግ አንቀፅ ለመፃፍ የሚያስችላችሁን ቢጋር አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

የቢጋር ርዕስ፡- የሀበሻ ቀሚስ አሰራር

1. የሀበሻ ቀሚስ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ግብአቶች

1.1. የሀበሻ ጥጥ

1.2. ------------------------------------------------

1.3. ------------------------------------------------

1.4. ------------------------------------------------

1.5. ------------------------------------------------

2. የሀበሻ ቀሚስ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ የሽማኔ ቁሳቁሶች

2.1. መወርወሪያ

2.2. -----------------------------------------

2.3. ---------------------------------------

3. የሀበሻ ቀሚስ ለማስጌጥ የሚያገለግሉ

3.1. መርፌ

3.2. ---------------------------------------

3.3. ----------------------------------------

**ተግባር ሁለት**

**ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ንድፍ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ስርአተነጥብ በመጠቀም አንቀፅ ጻፉ። የፃፋችሁትን ጽሁፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በየተራ አንብቡላቸው።**

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### የተጸውዖና የወል ስም

**ማስታወሻ**

ሀ. የተጸውዖ ስም የምንለው ለአንድ ነገር ብቻ የሚውል መጠሪያ ወይም መታወቂያ በመሆን የሚያገለግል ቃል ነው።

ምሳሌ :- የሰው ስም:- ስምኦን፣ዘመዴ ፣ያስሚን፣ ቤተልሔም ወዘተ.

የአገር ስም፡- ኢትዮጵያ፣ኬንያ፣ኡጋንዳ ወዘተ .

የተራራ ስም፦ ራስ ዳሽን፣መቅደላ፣ ወዘተ.

የከተማ ስም፡- አዲስ አበባ፣ጎንደር፣ለንደን ወዘተ.

ለ. የወል ስም የሚባለው ደግሞ አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስም (መጠሪያ) ነው፡፡

ምስሌ ፡- ሰው፣እፅዋት፣ ተማሪ፣ገበሬ፣ ነጋዴ፣ መምህር፣
መሃንዲስ፣እንስሳት፣ዶክተር፣ መጓጓዣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ተግባር አንድ

**ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ስሞች የተጸውዖና የወል ስም በማለት በምሳሌው መሰረት መድቡ**

ምሳሌ ሀ. ወጣት_ የወል ስም

ለ. ሴት _ የወል ስም

ሐ. አለሙ_ የተፀውዖ ስም

መ. ሀሊማ_የተፀውዖ ስም

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መሃመድ | ፍየል | በሬ | ፖሊስ | መሰረት |
| ሀና | አዋሽ | ሀይቅ | ገበሬ | ሀገሬ |
| ተራራ | ጥራጥሬ | | | |

| | የተጸውዖ ስም | የወል ስም |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

## ተግባር ሁለት

**ከላይ ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች ውጭ ሌሎች አምስት አምስት የተጸውዖና የወል ስሞችን በደብተራችሁ ፃፉና ዐረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

**ማስታወሻ፡- ምዕላድ**

ምዕላድ ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ የቋንቋ ንዑስ ክፍል ነው፡፡ የመጨረሻ የተባለበት ምክንያት አንድ ምዕላድ ወደሌላ አነስተኛ ትርጉም ያለው ክፍል ሊከፈል ስለማችል ነው፡፡ ምዕላድ ነፃና ጥገኛ በሚል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ነፃ ምዕላድ፡- ትርጉም ያለው ብቻውን መቆም የሚችል ቃል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ተራራ፣ ቤት፣ሰው፣ ልጅ፣ ድንጋይ ወዘተ.

ለ. ጥገኛ ምዕላድ፡- ብቻውን መቆም ስለማይችል ወደ ነፃ ምዕላዶች ተጠግቶ በግራ ወይም በቀኝ እየገባ የራሱን ትርጉም የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ትርጉም የሚኖረው ሁልጊዜም በነፃ ምዕላዶች ላይ ሆኖ ሲገባ ብቻ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ስለ-፣ ወደ-፣ እንደ-፣ከ-፣የ-፣-ዎች፣-ኦች፣ ወዘተ.

## ተግባር ሶስት

**የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት በምሳሌው መሰረት ጥገኛ ምዕላዱን ከዋና ቃሉ ለይታችሁ አስቀምጡ፡፡**

ምሳሌ፡- መንገደኛ መንገድ-ኧኛ
አስደነገጠ አስ-ደነገጠ

| ተ/ቁ | ቃል እና ሀረግ | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለሀገራችን | | |
| 2 | መምህራን | | |
| 3 | እየሔደች | | |
| 4 | ወደመፅሀፉ | | |
| 5 | ሰላማዊነታችን | | |
| 6 | ስለፍቅራቸው | | |

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ለቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ማለት የቃሉ አቻ ፍቺ ሲሆን አውዳዊ ደግሞ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው አገባባዊ ፍቺ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቢጋር በማዘጋጀት አንቀጽ ጽፈናል፡፡ አንቀጽ አንድን ሀሳብ ብቻ መነሻ አድርጎ በኃይለ ቃልና በመዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች የሚዋቀር ጽሁፍ መሆኑን ተረድተናል፡፡ የተጸውዖ ስም የአንድ ነገር መጠሪያ መሆኑን፣ የወል ስም ደግሞ አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች የጋራ መጠሪያ እንደሆነ  አይተናል፡፡ በመጨረሻም የምዕላድን ምንነት፣የነፃና ጥገኛ ምዕላድ ማስታወሻ ጽፋችሁ ጥገኛ ምዕላድን ከዋና ቃል ለይተን አይተናል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን የማጠቃለያ ጥያቄዎች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ ምንነትና ልዩነት ግለጹ ፡፡
2. ስለተጸውዖና የወል ስሞች የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. የሚከተሉትን ቃላት ወደነፃና ጥገኛ ምዕላድ ተንትኑ

ሀ. በሬዎች

ለ. ደብተሩ

ሐ. መኪናችን

መ. ተማሪዎቻችን

አማርኛ
፮ኛ ክፍል


# ምዕራፍ ሁለት
# ታዋቂ አትሌቶች

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከቃላት ውስጥ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላት ትመሰርታላችሁ፡፡
- የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድታችሁ የንባብ ድምፀቱን በመጠበቅ ታነባላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ ማዳመጥ

## ‹‹ ኦሎምፒክን በባዶ እግር ››





### ቅድመ ማዳመጥ

#### ተግባር አንድ

**ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› የሚለው ርዕስ ስለማን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. በሃገራችን ካሉት ታዋቂ አትሌቶች መካከል ቢያንስ አራቱን በመጥቀስ ያስመዘገቧቸውን ድሎች ዘርዝሩ፡

### የማዳመጥ ሂደት

‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› በሚል የቀረበውን ተራኪ ምንባብ የታሪኩን ቅደም ተከተል እየጠበቃችሁ አዳምጡ፡፡

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**ምንባቡን በጥሞና አዳምጣችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡**

ሀ. አበበ ቢቂላ ‹‹ ኦሎምፒክን በባዶ እግር ›› የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ሀገራቸውን ወክለው ወደሮም ያመሩት ኢታዮጵያውያን ማን ማን ነበሩ?

ሐ. አበበ ቢቂላ ለ1942 ዓ. ም ለሮም ኦሎምፒክ ውድድር ለመመረጥ የቻለው በምን ምክንያት ነው?

መ. ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?

ሠ. አበበ ቢቂላ የዓለምን ክብረ ወሰን ሰባብሮ ያሸነፈው በስንት ሰዓት ውስጥ ነበር?

ረ.‹‹ እያሸነፈ ክብረ ወሰኖቹን በእጁ አስገባ›› የሚለው አባባል ምንን ይገልጻል?

ሰ. ንጉሰ ነገሥቱ ለአበበ ቢቂላ የሸለሙት ምን ነበር?

ሸ. የሮም ኦሎምፒክ ሩጫን በባዶ እግሩ የሮጠው በምን ምክንያት ነበር?

### ተግባር ሶስት

**‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› የሚለውን ምንባብ ታሪክ አስታውሱና ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ በየተራ ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ‹‹ አንጸባራቂዋ እንስት››




**ቅድመ ንባብ**

**ተግባር አንድ**

1. አንፀባራቂዋ እንስት የሚለው ርዕስ ስለማን የሚገልፅ ይመላችኋል?
2. ስዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

**የንባብ ሂደት**

**ቀጥሎ የቀረበውን ተራኪ ንባብ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል እያስተዋላችሁ በለሆሳስ አንብቡ።**

ሩጫ ነፍሷ ነው፤ በህይወቷ ደስታ ይሰጣታል፤ እንደ ስራ ሳይሆን እንደመዝናኛ ነው የምትቆጥረው። ‹‹ሩጫ በቃኝ ፤ ከአሁን በኋላ አልሮጥም፣ ብየ ከቶውንም ላስብ አልችልም፤ አሸንፌ የወርቅ ሜዳሊያዎችን ማጥለቅና ብርታት የሚሰጠኝን የኢትዮጵያ ህዝብ ማስደሰት ታላቅ እርካታ ያጎናፅፉኛል›› በማለት ትናገራለች። የተወለደችው አርሲ በቆጂ ከተማ በ1977ዓ.ም ሲሆን አንድ ወንድና ሰባት ሴት ልጆችን ላፈሩት ወላጆቿ ሶስተኛ ልጅ ናት። ቤተሰቦቿ አርሶ አደር ስለነበሩ ከትምህርት ቤት መልስ በሥራ እያገዘች ነው ያደገችው።እሩጫ የጀመረችው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስፖርት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ነው።

አሰልጣኟ በጣም ጥሩ ተወዳዳሪ እንደምትሆን ዘወትር ይነግሯት ነበር። በሌላ በኩል ስለአትሌቲክስ በሚያቅና ሩጫን በሚያበረታታ ቤተሰብ ውስጥ መወለዷ እድለኛ አድርጓታል። በእሷ አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ልጃገረዶች ሩጫ ለመለማመድና ለመወዳደር ቀርቶ ትምህርት ቤት ለመሄድም አይፈቀድላቸውም ነበር። እርሷ ግን ከእርሷ በፊት አትሌት የሆኑ የቤተሰብ አባላት ስለነበሩ ተቃውሞ አልገጠማትም። በተለይም ከሩጫ ልምምድ ስትመለስ በቤት ውስጥ ስራ እንዳትጠመድ ከማድረግም በላይ በላቀ መንገድ ያበረታቷት ነበር።

1.እስካሁን ካነበባችሁት ምን ቁም ነገር አገኛችሁ?

2.ከዚህ ቀጥሎ ያለው ፅሁፍ ስለምን የሚያትት ይመስላችኋል?

የመጀመሪያዋን የኦሎፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ለአፍሪካና ለኢትዮጵያ ያበረከተችው የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት ደራርቱ ቱሉ እና ለቤተሰቦቿ በሩጫ ፈር ቀዳጅ የሆነችው እጅጋየሁ ዲባባ ለእሷ አርያዎቿ ናቸው፡፡ ጥሩነሽ ዲባባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ለመማር ወደ አዲስ አበባ መጣች፡፡ ነገር ግን ምዝገባ አልፎ ስለነበረ በሁኔታው ብታዝንም ተመልሳ ወደ መጣችበት ቦታ መሄድን አልመረጠችም፡፡ ከዚህ ይልቅ በስፖርት ክለብ የምትታቀፍበትን መንገድ ማፈላለግ ጀመረች፡፡ እናም ታላቅ እህቷ ውጤታማ ወደሆነችበት የማረሚያ ቤቶች የስፖርት ክለብ መቀላቀል ቻለች፡፡ በፖሊስ ክለብ አባልነት ሀገሯን በመወከል የመጀመሪያዋን አለም አቀፍ ውድድር በቤልጄም በአስራ አምስት አመቷ በባዶ እግሯ በመሮጥ ‹‹ሀ›› ብላ ጀመረች፡፡ ከዚያም በመቀጠል በአስራ ዘጠኝ አመቷ ፓሪስ ላይ በተካሄደው ዘጠነኛው አለም አቀፍ (የIAAF) የአለም ሻምፒዮን ውድድር በአምስት ሺ ሜትር ተወዳድራ ለሀገሯ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ ማስመዝገብ ችላለች፡፡

ጥሩነሽ ሁሌም ማሸነፍን፣ጠንክሮ መስራትን፣ የቀደሙ ታላላቆቿን አርዓያ በማድረግ ለታላቅ ስኬት እራሷን ያበቃች አትሌት ናት፡፡ ለአብነት ያህልም በ2000ዓ.ም የቤጅንግ ኦሎምፒክ ውድድር ላይ በአምስት ሺ ሜትር እና በአስር ሺ ሜትር ተወዳድራ በሁለቱም ርቀቶች ድርብ ድል የወርቅ ሜዳሊያን ለሀገሯ አስገኝታለች፡፡ በዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ እራሷን እያሻሻለች በተወዳደረችባቸው የውድድር መድረኮች ሁሉ በርካታ ሜዳሊያዎችን ለራሷና ለሀገሯ ማስመዝገብ የቻለች ታሪክ የማይረሳት ሀገር ወዳድ አትሌት ናት ፡፡

ምንጭ፡ ሜሪ ጆይ ግሌይና ሳባ ገ/መድህን ፡፡ (2007 ዓ.ም) ‹‹ተምሳሌት›› መጽሐፍ ከገፅ122-123 ለ6ኛ ክፍል ተሻሽሎ የቀረበ፡፡

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ ማብራሪያ ስጡ።**

1. አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ለመጀመሪያ ጊዜየወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበችበት ሀገር የት ነው?
2. ጥሩነሽ ዲባባ የተወለደችበት ልዩ ቦታ ማን ተብሎ ይጠራል?

3. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ግለፁ ?

4. አትሌቷ ወደ ቤተሰቦቿ ተመልሳ ቢሆን ኖሮ ምን ይገጥማታል ብላችሁ ታስባላችሁ?

5. ተማሪዎች ከጥሩነሽ ዲባባ ህይወት ምን እንደተማራችሁ በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡- ሀ. ክለብ ቡድን፣ ስብስብ

ለ. ማጥለቅ ማስገባት፣ መልበስ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ደስታ | መ. አርዓያ | ሰ. እድለኛ |
| ለ. ብርታት | ሠ. አርሶ አድር | ሸ. ተቃውሞ |
| ሐ. የላቀ | ረ. ዘወትር | ቀ. እርካታ |

## ተግባር አራት

**ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡-1. አብነት፦ ለሌሎች ሰዎች አርዓያ መሆን

2. ተወዳዳሪ፡- የተሻለ ሆኖ ለመገኘት የሚደረግ ፉክክር

ሀ. ልምድ

ለ. ስመ ጥር

ሐ. ክብረ ወሰን

መ. ተደናቂነት

ሠ. ኮከብ

ረ. ድርብ ድል

ሰ. ሜዳሊያ

ሸ. መድረክ

## ክፍል ሶስት ቃላት

### የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

**ተግባር አንድ**

**በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት በፍቺ የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሙዳ | ሀ. ውስታ |
| 2. ረብ | ለ. ግምገማ |
| 3. ዛለ | ሐ. ብርድ |
| 4. ቆፈን | መ. የስጋ ቁራጭ |
| 5. በነቂስ | ሠ. ከተመ |
| 6. ወሮታ | ረ. ጥቅም |
| 7. ደራ | ሰ. ፌዝ |
| 8. ሰፈረ | ሸ. ደመቀ |
| 9. ቧልት | ቀ. በሙሉ |
| 10 ሂስ | በ. ደከመ |

**ተግባር ሁለት**

**የሚከተሉትን ቃላት በቀረበው ምሳሌ መሰረት ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ልጅነት ልጅ-ነት

ለ. አይናማ- አይን-ኣማ

ሀ. ከተወዳዳሪዎቹ

ለ. መረጣችሁ

ሐ. ጓደኞቻቸውን

መ. ውጤታማነታችን

ሠ. ስኬታማነት

ረ. ሀገራችን

ሰ. ወታደሮቻችን

ሸ. ቤታቸውን

ቀ. ሰዎቹ

## ተግባር ሶስት

**ከዚህ ቀጥሎ ከ1-6 ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ መልሱ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ደባ | ሀ. ደፈጠ | ለ. በርኖስ | ሐ. ካባ | መ. ተንኮል |
| 2. አያሌ | ሀ. ጥቂት | ለ. ትልቅ | ሐ. ብዙ | መ. ከባድ |
| 3. ጎመጀ | ሀ. ቋመጠ | ለ. መታ | ሐ. ጓጓ | መ. ሀ እና ሐ |
| 4. ማነፅ | ሀ. ማቃናት | ለ. መግራት | ሐ. ማስተካከል | መ. ሁሉም |
| 5. ተግዳሮት | ሀ. ችግር | ለ. ደከመ | ሐ. አረጀ | መ. ፈራ |
| 6. አለመ | ሀ. ጎዳ | ለ. አነጣጠረ | ሐ.ቀመቀመ | መ. በረበረ |

## ተግባር አራት

**ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ምእላዶችን በማጣመር ቃላት መስርቱ፡፡**

ሀ. ዘመን - ኣዊ - ነት

ለ. ክብር - ት

ሐ. ወጣት - ኡ

መ. ሴት - ዮ - ዋ

ሠ. ሸጥ - ኡ - ት

ረ. በ - ጥልቅ - ኧ - ት

ሰ. በ - አደገ - ች - በት

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### አንቀጽ መፃፍ

**ማስታወሻ**

አንቀጽ የሀሳብ ቁርኝት ያላቸው አረፍተ ነገሮች እርስ በእርስ ተገጣጥመው አንድን ነጠላ ሀሳብ ብቻ ለመግለፅ የሚያገለግል አነስተኛ የድርሰት ክፍል ነው፡፡ በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሊነሳ የሚችለው ሀሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡ ሌላ የተለየ ሀሳብ መግለፅ ካስፈለገ ሌላ አዲስ አንቀፅ መመስረት ያስፈልጋል፡፡ አንቀፅ ሁለት መሰረታዊ አካላት አሉት፡፡ እነሱም፡- ኃይለ ቃል ወይም ዋና ዓረፍተ አገር እና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

- ኃይለ ቃል ወይም ዋና ዓረፍተ ነገር የሚባለው አንቀጹ የሚያስተላልፈውን ሙሉ ሀሳብ የሚይዝ አንድ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ በአንቀጽ ውስጥ ኃይለ ቃል በተለያየ ቦታ ላይ ሊገኝ ይችላል፡፡ ይኸውም በአንቀጽ መጀመሪያ፣ መካከል፣ መጨረሻ እና መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ነው፡፡ አንድ አንቀጽ ሊኖረው የሚችለው ኃይለ ቃል አንድ ብቻ ነው፡፡

- መዘርዝር ዓረፍተ ነገር ደግሞ በኃይለ ቃሉ መነሻነት የተለያዩ ምሳሌዎችንና መረጃዎችን በማቅረብ ዝርዝር ሀሳቡን ለማብራራት የሚጠቅም ነው፡፡

### ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥበመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ቢጋር በማዘጋጀት ከግማሽ ገፅ ያልበለጠ ጽሁፍ ፃፉ።**

ሀ. የሰላም አስፈላጊነት ሐ. መልካም ስነ-ምግባር

ለ. ጠንካራ የስራ ባህል መ. ውጤታማነት

### ተግባር ሁለት

**ከላይ በተግባር አንድ የጻፋችሁትን አንቀጽ በክፍል ውስጥ ተራ በተራ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።**

### ተግባር ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ አንብባችሁ ኃይለ ቃሉን ለይታችሁ አውጡ።**

ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው። ሰዎች የማያውቁትን የዚህ ዓለም ሚስጥር መረዳት እና መጠቀም የሚችሉበት በትምህርት ኃይል ነው።የራስን ኑሮ ማሻሻል፣ህብረተሰቡን መምራት የሚቻለው በትምህርት ነው። ትምህርት የሰዎችን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሻሽልና የኑሮ ዘይቤውን ቀለል አድርጎ ለመኖር የሚያስችል መሳሪያ ነው። ትምህርት አዳዲስ አሰራርና ለውጥን ለማስፈን፣ ሰላምና ፍትህን ለማምጣትና የተሻለች አለምን ለመፍጠር አይነተኛ ሚና ይጫወታል።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የወል ስሞች

### ተግባር አንድ

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የወል ስሞች በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አውጡ።**

ምሳሌ፡- ሀ. አትክልቶችን አዘውትሮ መመገብ ለጤና ጠቃሚ ነው።
መልስ -አትክልቶችን
ለ. በኢትዮጵያ በርካታ ወንዞች አሉ።
መልስ ፡- ወንዞች

ሀ. መሀመድ ከክፍሉ ተማሪዎች በቁመት ረጅሙ ነው፡፡

ለ. እድር የሚመሰረተው በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ነው፡፡

ሐ. በመኪና መንገድ ላይ የሚጓዙ እንስሳቶች በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ መጠንቀቅ ይገባል፡፡

መ. ትዕግስት የተለያዩ ቅርሶችን መጎብኘት ትወዳለች፡፡

ሠ. በረሃማነትን ለመከላከል እፅዋትን መንከባከብ ተገቢ ነው፡፡

ረ. ተማሪዎቹ ለፈተና ዝግጁ ሆነዋል፡፡

## ተግባር ሁለት

**አምስት የወል ስሞችን በመጥቀስ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በእያንዳንዳቸው አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ቤት- ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ ቤት አንዱ ነው፡፡

ሰራዊት- ኢትዮጵያ በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ ሰራዊት ገንብታለች፡፡

## ተግባር ሶስት

**በምዕራፍ አንድ በተማራችሁት መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች የወል ስሞችን ብቻ ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. ዓሳ

ለ. ልጅ

ሐ. ሰው

መ. ሀዋሳ

ሠ. ናሆም

ረ. ቅርስ

ሰ. ወንበር

ሸ አሊማ

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ የቃላትን ተመሳሳይ ፍች ለማየት ተሞክሯል። ተመሳይ ፍች ማለት ለአንድ ቃል አቻ ፍች መስጠትመሆኑን አይተናል፤ በመቀጠልም ዋና ቃልን ከቅጥያ እንዴት መለየት እንደሚቻል፤ ዋና ቃል ማለት ብቻውን ትርጉም የሚሰጥ እና ወደ አነስተኛ ትርጉም አዘል አሀድ መሸንሸን የማይችል ሲሆን ቅጥያ ማለት ደግሞ ራሱን ችሎ የማይቆም ነገር ግን ከዋና ቃል ጋር ሲጣመር ትርጉም የሚሰጥ እንደሆነ ተምረናል። ስለሆነም ዋና ቃልና ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላትን መስርተናል፤ የአንቀጽ ክፍልን ለይተን ርዕስ በመምረጥ አንቀጽ ለመጻፍ ልምምድ ያደረግን ሲሆን አንቀፅ አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ የሚያስተላለፍ አነስተኛ የጽሑፍ ክፍል መሆኑንም አይተናል። በመጨረሻም የወል ስሞችን ከሌሎች ስሞች ለይተን ለማሳየት ችለናል።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. የዋና ቃልና ቅጥያዎች ልዩነት እና አንድነት በቃል አብራሩ።
2. ለሚከተሉት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ

   ሀ. ኪነ- ጥበብ    ሐ. ፈርጥ

   ለ. ሚስጥር    መ. አንጋፋ

3. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ለይታችሁ ጻፉ።

   ሀ. ቂመኛ    መ. ተራራማ

   ለ. ኢትዮጵያዊነታችንን    ሠ. ተማሪዎቻቸውን

   ሐ. መንገደኛ    ረ. አንደበታዊነታቸውን

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሦስት

# ቃላዊ ግጥም

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ለአዳዲስ ቃላት ፍች በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ግጥም ፅፋችሁ በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- ቅንፍንና እዝባርን በአረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- አዳዲስ ቃላት በመጠቀም ገላጭና ተራኪ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፡፡
- ቃላቂ ግጥምን በመጻፍ  ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ታነባላችሁ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# በእርሻ ጊዜ የሚገጠም ቃላዊ ግጥም





## ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

**መምህራችሁ በእርሻ ወቅት የሚነገር አንድ ቃላዊ ግጥም ያቀርቡላችኋል፡፡ቃላዊ ግጥሙን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች  በቃላችሁ አብራሩ፡፡**

ሀ. ቃላዊ ግጥም ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ከቀረበው ስዕል ምን ተረዳችሁ፡፡

ሐ. የምታውቁትን ቃላዊ ግጥም አስታውሳችሁ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## የማዳመጥ ሂደት

**በእርሻ ስራ ላይ የሚቀርብ ቃላዊ ግጥም መምህራችሁ ሲያቀርቡላችሁ እናንተ በትክክል እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን ማስታወሻ ያዙና ተወያዩባቸው፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በጥሞና በማዳመጥ የጎደለውን ሀረግ በማሟላት በቃላችሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ. ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው ፣

ሞፈር ቀንበሩን_______________፡፡

ለ. ሚያዚያ ግው ሲል ግንቦት ሲያገሳ፤
______________ጎድጓዳ ማሳ፡፡

ሐ. ሆ ይላል ገበሬ ፣
ሆ ይላል ገበሬ ፣
________________፡፡

መ. በሬና ገበሬ ________________ ፣

እንዲያ ስተት ብሎ ይጠመዳል እንጂ፡፡

## ተግባር ሶስት

**ካዳመጣችሁት ቃላዊ ግጥም የወጡ አዳዲስ ቃላትን በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ክምር

የእነ አቶ በላቸው የጤፍ ክምር በጣም ትልቅ ነው፡፡

ሀ. ጀርጃራ
ለ. ቀንበር
ሐ. እረኛ
መ. እርኩም
ሠ. ዲብ
ረ. ቀሚስ

## ተግባር አራት

**ተማሪዎች መምህራችሁ ያቀረቡላችሁን የቃላዊ ግጥም አነባበብ ስልት ተከትላችሁ፡-**

ሀ. በመማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም አንብቡ፡፡

ለ. ያነበባችሁትን ቃላዊ ግጥም ጭብጥ (ዋና መልእክት) እና መቼ እንደሚባል ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**በሰብል ጥበቃ ጊዜ የሚዜም**

ኧረ ተይ ዝንጀሮ ግፍ አትናገሪ፣

አሁን ትገኛለሽ ውድማ ስትጭሪ፡፡

ኧረ ተይ ዝንጀሮ ልቤን ቆረጥሽው፣

ለፍቼ ለፍቼ ሰብሌን ጨረሽው፡፡

ዝንጀሮ ታረቀች ምላ ተማምላ፣

ማሽላውን ትታ ገብሱን ልትበላ፡፡

ዝንጀሮ መንጀሮ፣

በበላሽ ቀበሮ፡፡

ዝንጀሮ ከመጣች ሰብሉን ለመብላት፣

በወንጭፍ ገባሁኋት ተመለሽ በሏት፡፡

ተይ ተመለሽ ዝንጀሮ ተንኮል ያጠፋሻል፣

ነፍስሽን በጤና ብትይዥ ይሻልሻል፡፡

ተግባር አምስት

**ያዳመጣችሁትን ቃላዊ ግጥም ጭብጥ በቡድን በቡድን ተወያይታችሁ በተወካዮቻችሁት አማካኝነት በክፍል ውስጥ የቃል ንግግር አቅርቡ፡፡**

## ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ቃላዊ ግጥም

ቅድመ ንባብ

ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና ተገቢውን ማብራሪያ በቃላችሁ አቅርቡ፡፡**

1. በአብዛኛው ከሚዘወተሩት የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች መካከል የምታስታውሱትን በቃል አቅርቡ፡፡
2. በተለያዩ ክብረ በዓላት የሚዘወተሩ ባህላዊ ግጥሞች የሚኖራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ በተመለከተ አብራሩ፡፡
3. የሙሾ እና የሰርግ ቃላዊ ግጥም ልዩነታቸው ምን ይመስላችኋል?

የንባብ ሂደት

ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ እያዳመጣችሁ የሀረግ አከፋፈልን፣ ዜማንና ድምፀትን መጠበቃችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ፡፡

ቃላዊ ግጥም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያ ልዩ ልዩ ክስተቶች እና የህይዎት መልኮች መግለጫ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡ ይህ ኪነ ጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያካበቱትና የሚያካብቱት ቅርስ ነው፡፡ ቃላዊ ግጥም ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅም ማንፀባረቂያ ነው፡፡ በተለይ ፊደል ቀርፀው በፅሁፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነት፣እምነት፣የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን እንዲሁም አጠቃላይ የአለም አመለካከትን ቀርፆ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ቃላዊ ግጥም ህዝቦች ማንነታቸውን ይገልፁበታል፤ ወግና ልማዳቸውን አጠናክረው ያቆዩበታል፤ሀዘንደስታቸውን፣ምኞትተስፋቸውን፣ፍቅርጥላቻቸውን፣ድልሽንፈታቸውን፣ በአጠቃላይ የህይዎታቸውን መልኮች ያንፀባርቁበታል፡፡ቃላዊ ግጥም የማህበረሰቡ አንጡራ ሀብት ነው የሚባለው የልጆች ጨዋታ፣የሀዘን እንጉርጉሮ፣ልመና፣ፉከራና ቀረርቶ፣የክብረ በዓላት፣ የስራ፣ የፍቅር ግጥሞች አመንጭው እከሌ ነው ስለማይባል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ አጠር ባለና ቁጥብ በሆነ መልክ ይቀርባል፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችኋቸው አንቀፆች ምን ተረዳችሁ?
2. የቃላዊ ግጥም አይነቶች ምን ምንይሆናሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?



1.ቀረርቶና ፉከራ

ቀረርቶ ወይም ፉከራ ወኔን ለመቀስቀስ የሚያገለግሉ የስነቃል ዘውጎች ሲሆኑ፤ ክዋኔውም ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ እየተንጎራደዱ በወኔ የሚያቀርቡበት ሂደት ነው፡፡ቀረርቶና ፉከራ በሚቀርቡበት ጊዜ ሀይለኛ ስሜትና አካላዊ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ በአቀንቃኝና በተቀባይ የሚከወን ነው፡፡

የሚከተሉትን የቀረርቶናየፉከራ ግጥሞችእንመልከት፡፡፡፡

| ፉከራ | ቀርረቶ |
|---|---|
| ዘራፍ! ዘራፍ! ዘራፍ! | ሲያመኝ ውሎ ሲያመኝ ሊያድር ነወይ፣ |
| ልከህ ስደደኝ ቆላ ለቆላ፤ | ይኸ ሰርቶ መብላት ጤና ላይሆን ነወይ፡፡ |
| ክላሹን ላምጣው ጥሬ ሲቆላ፤ | የጠፋ መስሏችሁ እንዳትገቡበት፣ |
| ዱብ ዱብ ባይ እንደበረዶ፤ | ተረከዝ የሚያወልቅ ረመጥ አለበት፡፡ |
| በልጅነቱ በረሃ ለምዶ፤ | አረጀ አሉ አረጀ አሉ፣ |
| መራኸ ተኳሹን እኛ ስናውቀው፤ | ተከዜ አረጀ አሉ ሽበት ቀላቀለ፣ |
| ዝናር በቅፌን ምን አስጨነቀው፤ | አንድ ሰው ብቻውን ይሻገር ጀመረ፡፡ |

ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ

ጥይት ዘነበ እሳት ወረደ

እትትት….ዘራፍ!...አካኪ ዘራፍ!

2. በውቂያና አጨዳ  የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች





ለማወደስ፣ሰነፍን ለመኮነን ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ገበሬው ሲያርስ ፣ሲጎለጉል፣ ሲወቃ፣ሲያጭድ ወዘተ. የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን ይጠቀማል፡፡

| የውቂያ ግጥም | የአጨዳ ግጥም |
|---|---|
| በርዬ  እሽሩሩ | ይችን ማጭዴን ሆዷን አሟታል፣ |
| በርዬ እሽሩሩ፣ | እየቆረጠ ያጋድማታል፡፡ |
| የበሬን ውለታ፣ | ማጭዴ ቁረጭ ፣  እንዳትበለጭ፡፡ |
| እንጫወት ማታ፣ | |

በሰፊ ገበታ፣

በዋንጫ ጋጋታ፡፡

በርዬ እኔና አንተ የወረድንበቱ፣

ከካራ ይብሳል የድንጋይ ስለቱ፡፡

አያ በሬ ሆይ አያ ጎኔ ሆይ፣

ሳሩንአየህና ገደሉን ሳታይ፡፡

3. የሙሾ ቃላዊ ግጥሞች

ሙሾ ሰዎች የምድርን አለም በሚሰናበቱበት ጊዜ ዘመድ ወዳጅ በተሰበሰበበት ጊዜ ለሚኞቹ ያለንን ሁኔታ ደረት እየተመታ፣ እየተዘለለ የሚከወን ነው፡፡ ዋና አላማው የሀዘንን ስሜት እየፈጠሩ ስሜትን መቀስቀስ ሲሆን የሟቾችን ገድልና ታሪክ በታሪክነት ያስተላልፋል

እንጀራውን ጋግረሽ ከማን ጋር በላሽው፣

ደረት የሚመታ ጎረቤት ያጣሽው፡፡

የእናትና የልጅ መመሰጋገኛው፣

ገረገራግቢ ሲፈታ መጫኛው፡፡

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥም በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች፣ ማለትም የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ስደት፣ ራብ፣ ወረርሽኝ፣ ጦርነትን ወይም መልካም አጋጣሚን በተለያየ መልኩ እያቀረበ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የስነ-ቃል ዘርፍ ነው፡፡

ምንጭ (ዘሪሁን አስፋው የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን 2004፤ 20-63)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር አንድ

**በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ትክክል ከሆኑ ‹‹ እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ቃላዊ ግጥሞች የአንድ ማህበረሰብ ወግና ባህል መገለጫ ናቸው፡፡

ለ. የቃላዊ ግጥም ባለቤት ግለሰብ እንጅ ማህበረሰቡ ሊሆን አይችልም፡፡

ሐ. ቃላዊ ግጥሞች በገጠሩ ማህበረሰብ ብቻ የሚነገሩ ናቸው፡፡

መ. የስራ ቃላዊ ግጥሞችየተለዋጭነት ባህሪ አይታይባቸውም፡፡

ሠ. ቃላዊ ግጥሞች  የሚቀርቡት በትረካ ብቻ ነው ፡፡

ረ. ቃላዊ ግጥም ከጽሁፋዊ ግጥም የሚያመሳስለው የጋራ ባህሪ አለው፡፡

## ተግባር ሁለት

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. አይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ፣ ይቸግራል እና መሪ ማባበሉ፡፡ ይህ ቃላዊ ግጥም ምን በመባል ይታወቃል፡፡

   ሀ. የሙሾ ግጥም　　　　ለ. የልመና ግጥም

   ሐ. የፉከራ ግጥም　　　　መ. የዘፈን ግጥም

2. እንጀራውን ጋግረሽ  ከማን ጋር በላሽው፣

   ጠላውንስ ጠምቀሽ  ከማን ጋር ጠጣሽው፣

   ደረት የሚመታ ጎረቤት ያጣሽው፡፡

3. ይህ ቃላዊ ግጥም  ለምን አይነት ሴት የተገጠመ ይመስላችኋል?

   ሀ. ደግ በመሆኗ ለቅሶዋ ለደመቀላት ሴት፡፡

   ለ. ክፉ በመሆኗ ለቅሶዋ እንደ ነገሩ ለሆነላት ሴት፡፡

   ሐ. ዘመድ አልባ  ሆና አልቃሽ ላጣች ሴት፡፡

   መ. ግጥሙ የሴትዮዋን ምንነት አይገልጽም፡፡

4. በበጋ እረስ ቢሉት ፀሐይን እየፈራ፣

   በሀምሌ እረስ ቢሉት ዝናብ እየፈራ፣

   ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ፡፡

   የሚለው ቃላዊ ግጥም ለምን አይነት ሰው የሚገጠም ይመስላችኋል?

   ሀ. ለታታሪ ገበሬ　　　　ሐ. ለብልጥ ገበሬ

   ለ. ለሰነፍ ገበሬ　　　　መ. ለሞኝ ገበሬ

5. ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣

   ------------------------------፡፡ ለሁለተኛው ስንኝ የሚስማማው ሀሳብ የቱ ነው?

   ሀ. ምን ይበጀው ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   ለ. ቀኝ ተገዝቶ ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   ሐ. ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   መ. የት ይገባ ነበር ይህንጊዜ አበሻ

6. ከደጅሽ ይቅበሩኝ በስንደዶ ምሰው፣

   እንዳይቆረቁረኝ አንችን አንተርሰው፡፡ ይህ ቃላዊ ግጥም የሚያስተላልፈው መልእክት ____________ ነው?

   ሀ. የሀዘን　　　　ሐ. የፍቅር

   ለ. የምኞት　　　　መ. የብሶት

7. ከወደዱም አይቀር ይወዳሉ ቀይ፣ እንደ አደይ አበባ------------------፡፡ ግጥሙን ሊያሟላው የሚችለው ሀረግ የትኛው ነው?

   ሀ. የቀይ የቀይማ　　　　ለ. ከሩቅ የሚታይ

   ሐ. አጭር የሚታይ　　　　መ. የጓደኛ ቀይ

8. ከዋኙ ሲያቀርብ ተደራሲው ‹‹ እሺ . . . ከዚያስ . . . ደግሞስ ›› በሚል የሚቀርብ የስነ ቃል አይነት የትኛው ነው ?

ሀ. እንቆቅልሽ ሐ. ተረት

ለ. የልመና ግጥም መ. የፍቅር ግጥም

## ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ በገላጭና በተራኪ የቀረቡትን ሁለት አንቀፆች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በየተራ አንብቡ።**

ሀ. በጣት እየጠነቆሉ የማንበብ ሂደት በአብዛኛው የሚታየው በእድሜ ዝቅ በሚሉ ህፃናት ላይ ነው፡፡ ሂደቱ በቶሎ ካልተገታ አብሮ ሊያድግ ይችላል፡፡ በጣት እየጠነቆሉ ማንበብ በንባብ ሂደት ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ ይህ አይነቱ ልምድ የንባብ ፍጥነትን በጣም ከመቀነሱም በተጨማሪ አድካሚ ነው፡፡ በጣት እየጠነቆሉ ማንበብ ለጀማሪ አንባቢዎች ጠቃሚ መሆኑ ባይካድም ውሎ አድሮ የንባብ ችሎታ ሲዳብር ካልተወገደ ግን ችግር ይፈጥራል፡፡ ይህንን ልማድ ለማስቀረትም አንባቢዎች ከጣታቸው ይልቅ አይናቸው በተሻለ መንገድ ይህንን ተግባር ሊወጣ እንደሚችል በተግባር በማለማመድ ቀስ በቀስ ችግሩ እንዲቀረፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

ምንጭ ፦ (አለም እሸቱ፣16፣1996፣ያልታተመ ፅሁፍ)

ለ. መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም አርበኞች ሁሉ በድል አድራጊነት ሲገቡ በላይ ዘለቀም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸው፡፡ ዳሩ ግን በዙሪያቸው የተሰገሰጉት ባንዳዎች ‹‹አላሰራም›› ስላሏቸው ሸፍተው ጫካ ገቡ፡፡ በመሰሪ ጥላቶቻቸው አቀነባባሪነት በላይ እጃቸውን ቢሰጡ ምህረት እንደሚደረግላቸው ተደርጎ ስለቀረበ በላይ በተግባራቸው ተፀፅተው እጃቸውን ሰጡ፡፡ ሆኖም ግን ምህረት ሳይሆን ሞት ስለተፈ ረደባቸው በተወለዱ በ33 ዓመታቸው ተሰቀሉ፡፡

ምንጭ፦ (ታሪኩ ፋንታዬ ፣አማርኛ ሁሉ ለሁሉ ከመለስተኛ እስከ ኮሌጅ ገጽ 168፡፡)

## ክፍል ሶስት ቃላት

### አዳዲስ ቃላት

**ተግባር አንድ**

**በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለቀረቡትቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ‹‹ለ›› ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቅርብ | ሀ. ከባድ |
| 2. መቀላቀል | ለ. ቀነሰ |
| 3. በሽተኛ | ሐ. ጥቂት |
| 4. ጨመረ | መ. አፀዳ |
| 5. ቀላል | ሠ. ሩቅ |
| 6. ብዙ | ረ. በርካታ |
| 7. በከለ | ሰ. መለያየት |
| 8. ትንሽ | ሸ. ጤነኛ |

**ተግባር ሁለት**

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ፊደል ብቻ ምረጡ፡፡**

1. ላመ ሀ. ደቀቀ ለ. ተሰረቀ ሐ. ተሸረከተ መ. በተነ
2. ህቡዕ ሀ. ድብቅ ለ. ገሀድ ሐ. ስውር መ. የማይታይ
3. ሁከት ሀ. ረባሽ ለ. አምባጓሮ ሐ. ሰላም መ. ቂም
4. ጥቂት ሀ. ትንሽ ለ. ቅንጣት ሐ. ሰፊ መ. አያሌ
5. ቆንቋና ሀ. ስስታም ለ. ለጋስ ሐ. ንፉግ መ. ገብጋባ
6.

## ክፍል አራት ጽሕፈት

ማስታወሻ:- ቅንፍ ( ) እና እዝባር / ስርአተ ነጥቦች

ሀ. ቅንፍ( ):- ቅንፍ ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ በጽሁፍ ውስጥ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ:- እንደ እሱ ያለ እንብርቱን የተተኮሰ (ሚስጥር የማይቋጥር ) አይቼ አላውቅም፡፡

ለ. እዝባር /አቆልቋይ :- አህፅሮተ ቃላትን ለመመስረት እንደ አንድ ነጥብ (ይዘት) እናቀንና ዓመተ ምህረትን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ:- 20/11/2013ዓ/ም ፣ ዶ/ር ወዘተ.

### ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በእዝባር አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡**

ሀ. ጽሕፈት ቤት

ለ. ወይዘሮ

ሐ. ትምህርት ቤት

መ. የኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽፈት ቤት

ሠ ፍርድ ቤት

### ተግባር ሁለት

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅንፍን በተገቢው ቦታ በማስገባት አሳዩ፡፡**

ሀ. በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለመታደግ ለመርዳት ሁላችንም ኀላፊነት አለብን፡፡

ለ. በአሁኑ ወቅት ኮረና ኮቪድ-19 በዓለም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው፡፡

ሐ. ልጁ ወደዚህ ምድር ከመጣ ከተወለደ ጀምሮ ቤተሰቦቹ ችግር አጋጥሟቸው አያውቅም፡፡

መ. የአባይ የህዳሴ ግድብ የህልውናችን ጉዳይ ነው ፡፡

### ተግባር ሶስት

**ተማሪዎች ከቀረበላችሁ ርእስ አንዱን መርጣችሁ ግጥም በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

ሀ. ህዳሴ ግድብ ለ. እርቅ ሐ. ኮቪድ19

መ. ድህነት ሠ. መጤ ባህል

## ክፍል አምስት ሰዋስው

የጊዜ ተውሳከ ግስ

ማስታወሻ

የጊዜ ተውሳከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት ይገልጻል፡፡ በዚህም መቼ የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፡፡

ምሳሌ፡- ዛሬ ፣ በኋላ ፣ አሁን

### ተግባር አንድ


**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

1. አለሚቱ ባለፈው ዓመት ከአምስተኛ ክፍል አንደኛ ወጥታለች፡፡
2. ሀሚድ ትምህርት ቤት በጧት ይደርሳል፡፡
3. ወይዘሮ በለጡ ትናንት ህፃናትን ስለመልካም ስነ-ምግባር አስተማሩ፡፡
4. መገርሳ ዛሬ ጧት በቀጠሮው መሰረት ከቦታው ደረሰ፡፡
5. መቅደስና ሪሃና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ሀዋሳ ለመሄድ ተስማሙ፡፡
6. ነብዩ ባለፈው ሳምንት ቤተሰቦቹን ጠይቆ ተመለሰ፡፡
7. ወታደር ዘወትር የሀገሩን ሰላም ለማስከበር ዘብ የቆመ ነው፡፡

### ተግባር ሁለት

**ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ በቻርቱ ውስጥ ጻፉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወዲያውኑ | በመኪና አደጋ | አሁን | ሌሊት |
| አሳዛኝ | ስለረበሹ | ጥሩ | ትምህርት ቤት |
| ዛሬ | ነገ | አስደሳች | ያለፈው ዓመት |




### ተግባር፡- ሶስት

**የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች በተገቢው ቦታ እያስገባችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡**

ሀ. ሁል ጊዜ

ለ. አንዳንድ ጊዜ

ሐ. ገና

መ. ቶሎ

ሠ.ክፉኛ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ቃላዊ ግጥም ጽፈን ያነባበብ ስልትን ጠብቀን በማንበብ ያነበብነውን ግጥም ጭብጥ ተናግረናል፡፡ ቃላዊ ግጥም በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ፣አሁንም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል የማህበረሰቡን አጠቃላይ ወግና ባህል የሚገልፅ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቅንፍ ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባ ሲሆን እዝባር ደግሞ ቃላትን አሳጥሮ ለመፃፍ የሚያገለግል የስርዓተ ነጥብ አይነት እንደሆነ አይተናል፡፡ ስለሆነም ስርዓተ ነጥብን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተገቢው ቦታ ተጠቅመናል፡፡ አዳዲስ ቃላትን ተጠቅመን ዓረፍተ ነገር መስርተናል፤ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ በመጨረሻም የጊዜ ተውሳከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልፅ እንደሆነ አይተናል፡፡ ተውሳከ ግሶች ለይተን በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተጠቅመናል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ ቃላዊ ግጥም ከመፅሄት፣ ከጋዜጣና ከመጽሐፍት ፈልጋችሁ በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡
2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. እንከን | ሐ. ቁንጠኛ |
| ለ. በረረ | መ. ዛበረ |

3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ሞከከ | ሐ.ጥቂት |
| ለ. ወላንሳ | መ. ብልጥ |

4. ሶስት የጊዜ ተውሳከ ግስ ጽፋችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አራት
# ዘመናዊ ግብርና

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች:- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-


- አዳምጣችሁ በቃል ትመልሳላችሁ።
- አከራካሪ አንቀፅ ትጽፋላችሁ።
- ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም ትሰጣላችሁ።
- የጊዜ ግስን ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።

## ክፍል አንድ-- ማዳመጥ

### ድሮና ዘንድሮ

### ቅድመ ማዳመጥ





### ተግባር አንድ

1. ‹‹ ድሮና ዘንድሮ ›› የሚለው ርዕስ ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል? እስቲ ተወያዩና ግምታችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡
2. በአካባቢያችሁ ከትንሽ ነገር ተነስተው ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰው ታውቃላችሁ? ካሉ ምን እንደሰሩና ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ ግለጹ፡፡

### የማዳመጥ ሂደት

**‹‹ድሮና ዘንድሮ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል፤ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**ምንባቡን እያዳመጣችሁ ባዶ ቦታውን አሟልታችሁ ጻፉ።**

ሀ. እኔና እናቴ ከችግራችን የምንወጣበት _______________ ብሩህ ሆኖ ታየኝ፡፡

ለ. "ችግር መፍትሄ ይወልዳል" እንዲሉ _________________ከመስሪያ ቤት ስልክ ተደወለልኝ፡፡

ሐ. የወተት ምርቱም ከጊዜ ወደጊዜ መጠኑ _______ መጣ፡፡

መ. በአካባቢያችን ላሉ አትክልትና ፍራፍሬ መደብሮች ምርቶችን __________ ጀመርን፡፡_

ሠ. _______________ በአነስተኛ ቦታና ጉልበት ብዙ ምርት ማስገኘት የሚያስችል ዘርፍ ነው፡፡

ረ. እንደ ________________ ተደስቼና ቦርቄ ሳይሆን በስቃይና በፈተና መግፋት ጀመርኩ፡፡

ሰ. ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናቴን የማገዝ ሀላፊነቱ በኔ _______ ወደቀ፡፡

ሸ. ከዕለት ፍጆታ የሚተርፈንን _______ ጀመርን፡፡

### ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ በቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. መቸርቸር

ለ. ተሰናብቶን ሄደ

ሐ .መግፋት

መ. ግብዓት

ሠ. የኑሮ ዘይቤ

ረ. የዕለት ፍጆታ

**ተግባር አራት**

**ከዝቅተኛ የገቢ መጠን ወደ ከፍተኛ ገቢ መጠን እንዴት ማደግ እንደሚቻል በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ሀሳብ በየተራ ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት ንባብ

### የከተማ ግብርና

**ቅድመ ንባብ**

**ተግባር አንድ**

ሀ. የከተማ ግብርና ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል ?

ለ. በእናንተ አካባቢ የሚከናወን የከተማ ግብርና አለ? ካለ ምን ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡

ሐ. በከተማ የሚከናወን ግብርና ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

**የንባብ ሂደት**

ምንባቡን ድምፅ ሳታሰሙ እያነበባችሁ አዳዲስ ቃላትን በደብተራችሁ ጻፍ፡፡

ከከተማ ግብርና የሚገኝ ምርት የምግብ ስርዓትን በማሳደግ ጤናማ ማህበረሰ ለመገንባት ዘርፈ ብዙ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ለዚህ እንደማሳያ ማህበረሰቡ በአነስተኛ ቦታ ዘመናዊ የግብርና ዘዴዎችን በመጠቀም ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የግብርና ምርቶችን በማምረት ለዕለት ፍጆታ ማዋል ሲጀምር የምግብ ደህንነቱን ከመጠበቁም በተጨማሪ በምርቱ ላይ የሚኖረው እምነት ይጨምራል፡፡ይህም በቀላሉ በጥቂት ቦታ፣ብዙ የሰው ሃይል ሳያስፈልግ የከተማውን ነዋሪ የአርሶ አደሩን እጅ ሳይጠብቅ የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ ያስችለዋል፡፡ይህም የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ በማድረግ ጤናማ ማህበረሰብ መፍጠር ያስችላል፡፡

ከነባሩ የዶሮ ዝርያዎች የተሻለ የምርት ልዩነት የሚሰጡ የዶሮ ዝርያዎችን፣ ከአንድ የወተት ላም በቀን ሊገኝ የሚችልውን የወተት መጠን ማሳደግ የሚችሉ የላም ዝርያዎች፣ እንዲሁም የተለያዩ የሰብል፣የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጂዎች ወደ

ተጠቃሚ ተሸጋግረው ማህበረሰቡ ውጤታማ ምርት ማምረት የሚያስችለውን አሰራር በመዘርጋት የምግብ ደህንነትን ለማስጠበቅ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ አካል የሆኑት በርካታ ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው የሥራ እድሎችን ይፈጥራል፡፡ በከተማ አካባቢ የሚለሙ በርካታ የግብርና ዓይነቶች ሲኖሩ በእያንዳንዱ ግቢ ውስጥ በቀላሉ ሊመረቱ የሚችሉ የአትክልት ዓይነቶች ማለትም ቲማቲም፣ ካሮት፣ ጥቅል ጎመን፣የሀበሻ ጎመን፣ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ምን ተረዳችሁ?
2. ቀሪዉ የንባብ ክፍል ስለምን የሚገልጽ ይምስላችኋል?

**ቲማቲም**



በሀገራችን በስፋት ከሚመረቱት የአትክልት ሰብሎች ውስጥ አንዱ ቲማቲም ነው፡፡ ቲማቲም የተመጣጠነ የምግብ ይዘት ያለው በተለይም ማዕድናትንና ቫይታሚኖችን ከማስገኘቱም ባሻገር የአምራቹን ህብረተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ በማሳደግ የስራ እድል ለመፍጠርና በተወሰነ ቦታ ላይ ብዙ ገቢ በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው አትክልት ነው፡፡ ምርቱንም የቲማቲም ድልህ፣ ጭማቂ፣ ካችአፕ፣ቋንጣና የቲማቲም ዘቢብ በማዘጋጀት ለቤት ውስጥ ፍጆታ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ጥቅል ጎመን**



ጥቅል ጎመን በቀዝቃዛ አካባቢዎች የሚመረት የጓሮ አትክልት ሲሆን ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጅ በምግብነት ከታወቁት አትክልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ጥቅል ጎመን በአነስተኛ ማሳ ላይ የሚመረት የተለያየ ቀለም፣የራስ ቅርፅ፣ ለምግብነት የመድረሻ ጊዜ ያላቸው ዝርያዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ በብዛት የሚታወቀው ግን አረንጓዴ ቀለምና ጠፍጣፋ ራስ ያለው ነው፡፡ በቫይታሚን ኤ እና ሲ ምንጭነቱ የታወቀ ሲሆን ለምግብነትም በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

**የሀበሻ ጎመን**



የሀበሻ ጎመን ከስኳር ድንችና ከድንች ቀጥሎ በኢትዮጵያ በአነስተኛ ቦታ የሚመረትና በስፋት የሚታወቅ የጓሮ አትክልት ነው፡፡ ተቀቅሎ፣ተጠብሶና በክትፎ መልክ ተዘጋጅቶ ከአይብ ጋር ተቀላቅሎ ለምግብነት ይውላል፡፡ የሀበሻ ጎመን ከፍተኛ የቫይታሚን ሲ እና የሚኒራል መጠን በውስጡ ይዟል፡፡

**ሰላጣ**



ሰላጣ ቅጠሉ በጥሬው ከቲማቲም፣ ከቃሪያ ና ከቀይ ሽንኩርት ጋር ተቀላቅሎ በዳቦና በእንጀራ ተደርጎ ለምግብነት ይቀርባል፡፡ ከፍተኛ መጠን ያለው የቫይታሚን ኤ፣ሲ፣ ኬ እና ሚኒራል በውስጡ ይዟል፡፡

**ካሮት**



ካሮት የቫይታሚን ኤ መጠኑ ከሌሎች አትክልቶች ይልቅ ከፍተኛ በመሆኑ ካሮትን መመገብ የዐይን ዳፍንት በሽታን ለመከላከል ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የቫይታሚን ቢ መጠኑ ከፍተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የጓሮ አትክልቶችን በአነስተኛ መሬት በመዝራት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የጓሮ አትክልቶች የተለያየ የአካል ክፍሎቻቸው ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ ሲሆን እንደ አትክልቶቹ አይነት ቅጠሎቻቸው፣ሥሮቻቸው፣አበባዎቻቸውና ፍሬያቸው ሊበላ ይችላል፡፡ የጓሮ አትክልቶች የተለያየ አይነትና መጠን የምግብ ይዘት ያላቸው ሀይል ሰጪ፣ ሰውነት ገንቢ እና በሽታ ተከላካይ ምግቦች ናቸው፡፡ የጓሮ አትክልቶችን ለማምረት የዕለት ከዕለት ክትትል፣የአመራረት እውቀትና ክህሎትን የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ ሆኖም በተወሰነ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ በመሆናቸው ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡

ምንጭ፦ (በሴቭ ዘ ችልድረን፣በትምህርት ሚኒስተርና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ት/ቢሮ የጋራ ትብብር በ2008ዓ.ም ከተዘጋጀው አጋዥ መጽሐፍ ለ6ኛ ክፍል ማስተማሪያ ተስማምቶ የቀረበ፡፡)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**በሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥና ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- በርካታ | በምንባቡ መሰረት | ብዙ |
| | ከምንባቡ ውጪ | በደስታ |

ሀ. የጓሮ አትክልት ለጤና በርካታ ጠቀሜታ አለው ፡፡

ለ. ባለፈው ሳምንት የተመረቀችው ተማሪ የወርቅ ሜዳሊያዋን በርካታ ተቀበለች፡፡

ሀ. ክህሎት ሐ . ጥሬ ሠ. መቀላቀል

ለ. ማሳ መ. ዝርያዎች ረ. ፍጆታ

## ተግባር ሶስት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ ስራቸው ከሚበሉ አትክልቶች ይመደባል፡፡

ሀ. የሀበሻ ጎመን ለ. ድንች

ሐ. ጥቅል ጎመን መ. ቃሪያ

2. ሳይበስል የሚበላ አትክልት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰላጣ ለ. ቆስጣ

ሐ. ድንች መ. የሀበሻ ጎመን

3. ከሚከተሉት አንዱ ቅጠሉ ከሚበላ አትክልት ውስጥ ይመደባል፡፡

ሀ. ካሮት ለ. ቃሪያ

ሐ. ቆስጣ መ. ስኳር ድንች

4. ከነባሩ የዶሮ ዝርያ የተሻለ ምርት የሚሰጥ ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍቺ ------- ነው፡፡

ሀ. ከቆየው ለ. ከአዲሱ

ሐ. ከተለወጠው ሐ. ከተሸሻለው

5. የህብረተሰቡ አካል ለሆኑት የስራ እድል ይፈጥራል፡፡ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰውነት ለ. ክፍል

ሐ. ዘመድ መ. ጓደኛ

6. በቀዝቃዛ ቦታ የሚመረት የጓሮ አትክልት የቱ ነው?

ሀ. ቲማቲም ለ. ቃሪያ

ሐ. ጥቅል ጎመን መ. ሰላጣ

7. የዐይን ዳፍንት በሽታ የሚከላከል አትክልት የሆነው?

ሀ. ካሮት ለ. ድንች

ሐ. ሰላጣ መ. ቲማቲም

8. ‹‹የነፍስ ወከፍ›› የሚለው ሀረግ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

ሀ. ለጽድቅ ለ. ለቡድን

ሐ. ለእያንዳንዱ መ. ነፍስን የሚጎዳ

9. ከሚከተሉት አንዱ የአትክልት ዝርያ አይደለም፡፡

ሀ. ጥቅል ጎመን ለ. ሙዝ

ሐ. የሀበሻ ጎመን መ. ቃሪያ

10.የከተማ ግብርና ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ንጹህ ምግብ ማግኘት

ለ. የምግብ ፍላጎትን ማሟላት

ሐ. በቀላሉ የተመጣጠነ ምግብ ማምረት መቻል

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## ተግባር አራት

ሀ. በግቢያችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የጓሮ አትክልቶችን አመራረትና ጠቀሜታ የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት ቃላት

### ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም መስጠት

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ትርጉም የማይሰጡ ቃላት በምሳሌው መሰረት ትርጉም በሚሰጥ መንገድ አዋቅራችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ስፈረ -- ፈረስ

በሰውሰባቸ --- ሰበሰባቸው

ቤምትህትትር- ትምህርት ቤት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ውትቀዕ | መ. መልይለሳ | ሰ.ክሳትይታ | ተ. በንወር |
| ለ. ጥዶወየሮ | ሠ. ቀልመለጠ | ሸ. ተናፈ | ቸ. ርባፀትገያህ |
| ሐ. ርንብሃ | ረ. ዝማአል | ቀ. ሀፅመፍ | |
| በ. ሲንየደያራተ | | | |

**ተግባር ሁለት**

**ከዚህ በታች ባለው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውጥታችሁ ትርጉማቸውን በቃላችሁ ተናገሩ፡፡**

ወንጀል ሰላማዊ ኑሮን ይነቀንቃል፤ ወንጀለኞች ኪስ ያወልቃሉ፤ቤት ይሰረስራሉ፤ በሚዛን ያብላሉ፤ አልፎ ተርፎ ጨለማን ተገን በማድረግ የሰውን ህይወትይቆርጣሉ ፡፡ እነዚህ አሜካላወች እስካልተመነጠሩ ድረስ ሰላማዊ ኑሮ መጎሹቱ አይቀሬ ነው፡፡

ምንጭ፦ (ሰለሞን ሐለፎም ፡፡(1997፣193)፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡

**ተግባር ሶስት**

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ይሆናሉ ተብለው ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ይበልጥ የሚስማማቸውን ምረጡ፡፡**

1. ሰፊፍ ሀ. ዝቃጭ ለ. አተላ ሐ. ጥላይ መ. ለዛ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2. ቃና | ሀ. ለዛ | ለ. መዓዛ | ሐ. ውበት | መ. ዳና |
| 3. የቀለም ቀንድ | ሀ. ምሁር | ለ. ብዕር | ሐ. ዋንጫ | መ. ቀንድ |
| 4. ፅሞና | ሀ. ትህትና | ለ. ምር | ሐ. ቀልድ | መ. ተመስጦ |
| 5. ራሮት | ሀ. ርህራሄ | ለ. ጥቁረት | ሐ. ሮሮ | መ. ስጋት |
| 6. ማመንጨት | ሀ.ማፍለቅ | ለ. መቅዳት | ሐ. መጥለፍ | መ.መቀስቀስ |
| 7. ደራ | ሀ. ኮራ | ለ. ሰፋ | ሐ. ሞቀ | መ. ተኮሰ |

## ክፍል አራት:- ጽሕፈት

### አመዛዛኝ ጽሑፍ

ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የቀረቡ ዓረፍተነገሮች አስተካክላችሁ አንድ አንቀጽ አዋቅራችሁ ጻፉ።**

ሀ. መንገደኞቹም ሩጫቸውን ትተው በቅርብ ወዳገኙት መጠለያ ተጠጉ።

ለ. በጥፊ የሚመታው ይህ ስለታም ነፋስ አቧራ አስነስቶ ከሰው አይን ውስጥ እየሞጀረ ያደናብራል።

ሐ. የአዲስ አበባ ሰማይ በጥቁር የደመና ብርድ ልብስ ተጀቡኗል።

መ. የሴቶችን ቀሚስ ወደላይ እየገለበ ይተናኮላል።

ሠ. ብዙ ሳይቆይ ‹‹ጠብ ያለህ በዳቦ›› የሚለው ዶፍ ዝናብ እየተንዠቀዠቀ ቁልቁል ወረደ።

ረ. ጉርምርምታው ያላማራቸው መንገደኞች አህያ የማይችለውን ዝናብ ለማምለጥ ወደየቤታቸው በመሯሯጥ ላይ ናቸው።

ሰ. ሀይለኛ ነፋስ ከዝናቡ ቀድሞ መንገደኞችን ማወክ ጀመረ።

ሸ. ከባድ ዝናብ ያረገዘው ደመና አጣዳፊ ምጥ ይዞት በጣር ያጉረመርማል።

## ተግባር ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን አከራካሪ አንቀፆች መሰረት አድርጋችሁ ከሀ - መ ከተዘረዘሩት አከራካሪ ዓረፍተ ነገሮች አንዱን በመምረጥ አንድ አከራካሪ ጽሑፍ በደብተራችሁ ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።**

ሀ. ንፅፅራዊ ስነ-ልሳን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን በተነፃፅሮት የሚያጠና የስነ-ልሳን ዘርፍ ነው። ለተነፃፅሮት የሚቀርቡትም ቋንቋዎች ስርወ ግንዳቸው አንድ ወይም የተለያየ ሊሆን ይችላል።ዘርፉ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን በድምፅ፣ በቃላት አገባብ እንዲሁም በአረፍተ ነገር አሰካክ ያላቸውን ዝምድና እና ልዩነት በማነፃፀር የሚያቀርብ ነው።

ምንጭ፦ (ተስፋየ ሸዋየ፣1981፣13)

ለ. … በምግብ በኩል የሚታየው የአካል ግንባታና ጥገና በመጠጥ በኩል ተቃራኒ ሆኖ ይታያል። መጠጥ በብዛትና በተከታታይ በተወሰደ ጊዜ እንደጉበት ፣ኩላሊት፣ ልብና የመሳሰሉትን የውስጥ አካላትን ለጉዳት ያጋልጣል። በእርግጥ ምግብም ቢሆን በልክና በተመጣጠነ ደረጃ ካልተወሰደ ሰውነትን ቅርፀ ቢስ ከማስመሰል አሳልፎ የተከማቸ ትርፍ ስብ በነርቮችና በደም ዝውውር ላይ ችግር ሊያመጣ ይችላል። ስናጠቃልለው ለሚበላ ነገር ቅድሚያ ሰጥተው የሚዋከቡትን ሰዎች ባህላችን አይደግፏቸውም። ስለሆነም ህብረተሰቡ ‹‹ሆዳም፣ስግብግብ፣አሳማ…›› እያለ ያጥላላቸዋል። መጠጥ ወዳጁንም ‹‹ፉቴ፣ ገልባጭ፣ አንቡላ፣ ሰካራም…›› በሚል የቅፅል ስም ይጠሯቸዋል። ያም ሆነ ይህ ምግብና መጠጥ ፈፅሞ ሊወዳደሩ አይችሉም። ምንጭ፦ ( ታሪኩ ፈንታዬ፣2008፣173)

## ተግባር ሦስት

**ተማሪዎች አንድ ርዕስ መራጣችሁ አከራካሪ ጽሁፍ በማዘጋጀት ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. ከቀደመውና ከአሁኑ ትውልድ ጠንካራ የሀገር ፍቅር ስሜት ያለው የትኛው ነው።

ለ. በሰው ሀገር ሰርቶ ከመበልጸግና በሀገር ሰርቶ ከመበልፀግ የትኛው ይሻላል።

ሐ. ከእውቀትና ከገንዘብ የትኛው ይበልጣል።

መ. ጀግና ማነው? በጦርነት ተዋግቶ ያሸነፈ ወይስ ድህነትን ተዋግቶ ያሸነፈ?

## ክፍል አምስት ሰዋስው

**የጊዜ ግስ**

### ተግባር አንድ

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን የጊዜ አይነቶች ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- አክስቴ ወደሀገሯ ልትመለስ ነው፡፡ የወደፊት ጊዜ

አክስቴ ወደሀገሯ እየተመለሰች ነው፡፡ የአሁን ጊዜ

አክስቴ ወደሀገሯ ተመልሳለች፡፡ የሃላፊ ጊዜ

ሀ. ለጆሮ እንዲስማሙ ተደርገው የተዘጋጁ ዜማዎችን ለገበያ አቅርበዋል፡፡

ለ. ቃሎቿ የተዋቡ ይሁኑ እንጂ ስታወጣቸው በጭንቀት ነበር፡፡

ሐ. በዓለማችን በአሁኑ ሰዓት በረሃማነት እየተስፋፋ ነው፡፡

መ. አዲስ አበባ ወደፊት ምቹና ፅዱ እየሆነች ትሄዳለች፡፡

ሠ. እህቴ ነገ ከጎንድር ትመጣለች፡፡

ረ. ታናሽ ወንድሜ የተወለደው ከዛሬ አስር ዓመት በፊት ነበር፡፡

ሰ. የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ወደ ሀገራችን እየመጡ ነው፡፡

ሸ. የመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ላይ ምልክቶችን ለመትከል እያሰበ ነው፡፡

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይባቸውን ዓረፍተገሮች አስተካክላችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ሁኔታ አለፈ ፈተናውን በጥሩ፡፡
ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አለፈ፡፡
ለ. አስተማረች ልጇን ሙያ አስቴር፡፡
አስቴር ልጇን ሙያ አስተማረች፡፡

ሀ. ተወካያቸውን የክፍል መረጡ ተማሪዎቹ፡፡

ለ. ያስፈልጋል ተማሪዎችን ማበረታታት ጎበዝ፡፡

ሐ. መነሳት ሰው ማንኛውም አለበት ታጥቆ ለማስወገድ ድህነትን ፡፡

መ. ሄለን የተመሰገነች በስነ-ምግባሯ ናት፡፡

ሠ. ጉልበት አለበት ሁሉም ሰው የህፃናት መከላከል ብዝበዛን፡፡

ረ. ቴክኖሎጂ አለበት ትምህርት መደገፍ በሳይንስና፡፡

ሰ. ለማቅረብ አለበት አጥፊዎችን መተባበር ህብረተሰቡ ለህግ፡፡

ሸ. ባህላችን አረጋውያንን ይገባል ሊሆን መንከባከብ፡፡

## ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. አምና

ለ. ባለፈው ሳምንት

ሐ. ከወር በኋላ

መ. የዛሬ አመት

ሠ. ሌሊት

ረ. ቶሎቶሎ

ሰ. አልፎ አልፎ

ሸ. በዚህ አመት

## ተግባር አራት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት የአሁን ጊዜ፣የሃላፊ ጊዜና የወደፊት ጊዜ በማለት በሰንጠረዥ ውስጥ መድቡ፡፡**

እየተማረ ነው　　እየሰራ ነው　　እየሰጠ ነው　　ሰጥቷል

ይሰጣል　　ይመጣል　　ሰላም እየሰፈነ ነው　　ሰብሯል

ያነባል　　ሰላም ይሰፍናል　　እየመጣ ነው　　ይሰብራል　　አንብቧል

ሰላም ሰፍኖ ነበር　　መጥቷል　　ተምሯል　　እያነበበ ነው

| ተ/ቁ | የአሁን ጊዜ | የሃላፊ ጊዜ | የትንቢት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር አከራካሪ አንቀጽ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ የሚመሳሰሉበትን ወይም የሚለያዩበትን ሀሳብ በማነጻጸር ወይም በማወዳደር የሚያቀርብ ጽሁፍ እንደሆነ ተረድተናል። በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተፃፈ ፅሁፍ በማቅረብ በምሳሌው መሰረት አንቀፅ መፃፍ ችለናል። የተዘበራረቁ ፊደላትን አገጣጥመን ፍቺ ያላቸው ቃላትን መስርተናል። ከዓረፍተ ነገር ውስጥ የጊዜ አይነቶችን ለይተን ጽፈናል። የጊዜ አይነቶች ሶስት ሲሆኑ እነሱም የአሁን ጊዜ፣ የሃላፊ ጊዜና የትንቢት(የወደፊት ጊዜ) እንደሆኑ አይተናል። የጊዜ ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርተናል።

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. የጊዜ አይነቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. አከራካሪ ጽሁፍ ምን አይነት ጽሁፍ እንደሆነ በቃል ግለጹ።
3. በከተማ ግብርና ዙሪያ የቀረቡ መርሀ ግብሮችን ከቴሌቪዥን፣ከሬዲዮ ተከታትላችሁ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፧

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አምስት
# ቱሪዝም

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ቃላትን በምእላድ ትከፋፍላላችሁ፡፡
- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በሀላፊ ጊዜ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ ሥራችሁን ትመዝናላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ሽርሽር በእንጦጦ




### ቅድመ ማዳመጥ

#### ተግባር አንድ

ሀ. ‹‹ ሽርሽር በእንጦጦ ›› በሚለው ርእስ የቀረበው ምንባብ ምን ምን ነገሮችን የሚያሳይ ይመስላችኋል?

ለ. ከዚህ በፊት የጎበኛችሁት ወይም ሽርሽር የሄዳችሁበት ቦታ ካለ ምን ምን ነገሮችን እንደተመለከታችሁ ዘርዝሩ፡፡

ሐ. የመጎብኘት እድል ቢሰጣችሁ የትኛውን ቦታ የምትመርጡ ይመስላችኋል?

የማዳመጥ ሂደት

‹‹ሽር ሽር በእንጦጦ›› በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመለየት በንቃት አዳምጡ፡፡

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹ እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ ሀሰት› በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ቅርስ የአንድን ሀገር ታሪክና ባህል ባጭሩ ይገልጻል፡፡

ለ. የእንጦጦ ተራራ ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ ይገኛል፡፡

ሐ. ‹‹ የእጦጦ ተራራ የአዲስ አበባን ጓዳ ጎድጓዳ ያሳያል›› ሲል የሰዎችን ጓዳ ማለቱ ነው፡፡

መ. አፄ ምኒልክ እንጦጦን ለቤተ መንግስትነት የመረጡት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡

ሠ. እንጦጦን የሚጎበኝ ሰው መንፈሱ ስለሚታደስ ለፈጠራ ስራ ይነቃቃል፡፡

ረ. አዲስ አበባ ንፁህ አየር የምታገኘው ከእንጦጦ ተራራ ነው፡፡

ሰ. የቱሪዝም ቦታዎችን መጠበቅ ያለብን ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ብቻ ነው፡፡

### ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በምዕላድ ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- መስህቦቻችን፡- መስህብ - ኦች - ኣችን

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ተፈጥሯዊ | ሐ. ጎብኝዎቻችን | ሠ.ችሎታቸውን |
| ለ. መስህቦች | መ. ቅርሶቻችን | ረ. መንገዳቸውን |

**ተግባር አራት**

**ተማሪዎች ስለ አንድ የጉብኝት ቦታ ከሬዲዮ፣ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ ወይም ከጋዜጣ፣ከመጽሔት አንብባችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ፡፡**

## ክፍል ሁለት:- ንባብ

### አንድነት ፓርክ

**ቅድመ ንባብ**

**ተግባር አንድ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በስዕሉ ላይ ተወያዩና የሚገልጸውን መልእክት በቃል ተናገሩ፡፡

ለ. ‹‹ የአንድነት ፓርክ ›› የት የሚገኝ ይመስላችኋል?

ሐ. የአንድነት ፓርክ በውስጡ ምን ምን ጉዳዮችን ያካትታል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

የንባብ ሂደት

**ቀጣዩን ምንባብ ስታነቡ በእያንዳንዱ አንቀፅ መጨረሻ ቆም እያላችሁ የአንቀፁን መልዕክት በአዕምሮአችሁ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ፡፡**

የአንድነት ፓርክ የሚገኝበት ታላቁ ቤተ መንግስት የተቆረቆረው በ1878ዓ.ም ሲሆን የመሰረቱትም በወቅቱ የሸዋ ንጉስ የነበሩት ዳግማዊ አጤ ምኒልክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ብጡል ናቸው፡፡ የቤተ መንግስቱ አጠቃላይ ስፋት አርባ ሄክታር ነው፡፡ ቦታው ለቤተ መንግስትነት የተመረጠው ለፍልውሃ በነበረው ቅርበትና በወቅቱ ዙሪያውን ለመቆጣጠር የሚመች ከፍታ ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ ፡፡

የአንድነት ፓርክ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ሀሳብ አመንጭነት ለፓርክነት የግንባታና የማደራጀት ስራው በ2010ዓ.ም ተጀመረ፡፡ አዳዲስ የጉብኝት መስህብ የሆኑ ግንባታዎች የተካሄዱበት ስፍራ በሙሉ ቀደም ሲል ጥሻና ገደላማ ነበር፡፡ ታሪካዊ ህንጻዎችና አደባባዮች ታሪካቸውና ፋይዳቸው በምሁራን ተጠንቶ ለጉብኝት ምቹ ሆነው የተደራጁ ዘመናዊ የቱሪስት መዳረሻዎች ናቸው፡፡

## የአንድነት ፓርክ የጉብኝት መዳረሻዎች

አንድነት ፓርክ በውስጡ  ስድስት ዋና ዋና የቱሪዝም መስህብ ቦታዎች አሉት፡፡ ከመግቢያው ጀምሮ የምናገኛቸው  እነዚህ  የአንድነት  ፓርክ ክፍሎች  የጥቁር አንበሳ ዋሻ፣ የአገር በቀል ዕፅዋት መገኛ ቦታ፣ የክልል እልፍኞች፣ የአረንጓዴ ስፍራ፣ የአንድነት መካነ እንስሳት፣ የቤተ መንግስቱ  ታሪካዊ ህንፃዎችና አውደ ርዕዮቶቻቸው ይጠቀሳሉ፡ ፡ ከታሪካዊ ህንፃዎቹ በስተቀር አምስቱ የጉብኝት መዳረሻዎች  በአዲስ መልክ የተገነቡ የቱሪስት ስፍራዎች ናቸው፡፡

1. ከላይ ካነበባችኋቸው  አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?
2. ቀጣዩ የምንባብ  ክፍል ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

በቤተ መንግስት የሚገኙ ታሪካዊ ህንፃዎች




ታላቁ ቤተ መንግስት የአጤ ምኒልክ ቤተ መንግስት በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ቤተ


መንግስት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ አገራዊና አህጉራዊ ፋይዳ ያላቸው ሁነቶች የተፈፀሙበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከ1880ዎቹ ጀምሮ የተገነቡ የነገስታት መኖሪያና ጽህፈት ቤቶች በዋነኛነት በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን የነበሩበትን ይዞታ ሳይለቁ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የሆነው የአጤ ምኒልክ የግብር አዳራሽ ሲሆን ንጉሱ በዚህ አዳራሽ እንግዶቻቸውን ያስተናግዱ እንደነበር ታውቋል፡፡ በዚህ ስፍራ መጀመሪያ የምናገኘው የፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴን (አባ መላ) መኖሪያ ነው፡፡ ቀጥሎም የአጤ ምኒልክ ባለአንድ ፎቅ መኖሪያና ጽሕፈት ቤት ያለ ሲሆን የህንፃው በሮች በእንጨት የተሰሩና በሚያምር መልኩ የአበባና የሀረግ ጌጥ የተፈለፈለበት ናቸው፡፡ ይህ ቤት ከሁለት ሌሎች ቦታዎች ጋር በድልድይ ይገናኛል፡፡ አንደኛው በሰሜናዊ አቅጣጫ የአጤ ምኒልክ የፀሎት ቤትና የሥዕል ቤት ሲሆን እንቁላል ቤት በመባል ይጠራል፡፡ በሌላ በኩል አጤ ምኒልክ ከጦር መኮንኖቻቸው ጋር የሚገናኙበት ክፍል ይገኛል፡፡ በወቅቱ የጦር ሚኒስትር የነበሩት ፊት አውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ እንደ ቢሮ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ሌላው ደግሞ የዘውድ ቤት ሲሆን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነገስታትንና ዲፕሎማቶችን ከተለያዩ ሀገራት ተቀብለው ያስተናግዱበት ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል በ1956 የዩጎዝላቪያው ፕሬዝደንት ቲቶ፣በ1965 ንግስት ኤልሳቤጥ2ኛ፣ በ1966 የፈረንሳዩ ፕሬዝደንት ቻርልስ ደጎል ይገኙበታል፡፡ ሌላኛው ከአጤ ምኒልክ ቤት ጋር በድልድይ የሚገናኘው የእቴጌ ጣይቱ ቤት ነው፡፡ ይህ ቤት ከቤተ መንግስቱ በምስራቃዊ አቅጣጫ የሚገኝ ባለአንድ ፎቅ ህንፃ ነው፡፡ በምድር ቤት የዙፋን ግብር ቤት ይገኛል፡፡ የነገስታቱ መመገቢያ አዳራሽ ሲሆን ንጉሳዊ ቤተሰቦች ምግብ የሚመገቡበት ክፍል ነበር፡፡ ይህ ቤት በደርግ ጊዜ የደርግ ምክር ቤት መሰብሰቢያ በመሆን አገልግሏል፡፡

የሀገር በቀል እፅዋት








በሀገር በቀል የዕጽዋት ጉብኝት መዳረሻ፣ ለመድሃኒት፣ ለምግብና ለውበት አገልግሎት የሚውሉ ዕጽዋትን ይጎበኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ጤናአዳም፣ኮሰረት፣ ፌጦ፣በሶብላ፣ዝግባ፣ዋንዛ ወዘተ. ይገኛሉ፡፡ በእጅ በተጠረቡ ድንጋዮች የተሰሩ ካቦች፣ መተላለፊያ መንገዶችና የጭቃ ቤትም በዚሁ ስፍራ ይገኛል፡

የጥቁር አንበሳ መካነ እንስሳት

በዚህ የጉብኝት መዳረሻ ጎብኝዎች 175 ሜትር እርዝመት ባለው ዋሻ ውስጥ ሆነውና በዙሪያው እየተዘዋወሩ በዋናነት የባሌና የዴዴሳ ዝርያ የሆነውን ባለ ጥቁር ጎፈር አንበሳ ይመለከታሉ።

## የክልል እልፍኞች








በአንድነት ፓርክ ውስጥ ከሚገኙ የጉብኝት መዳረሻዎች መካከል አንዱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ያሉ የክልል እልፍኞች የሚገኙበት ቦታ ነው። እልፍኞቹ የየክልሎቹን ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ መስህቦች በጥቂቱ ለጎብኝዎቹ ያስተዋውቃሉ፤ ስለክልሎቹ መሰረታዊ መረጃ በተንቀሳቃሽ ምስል፣በሥነ-ስዕል እና በሌሎች የባህል ውጤቶች በጥቂቱ የሚያቀርቡ ናቸው። አሠራራቸውም በዘመናዊ የኪነ-ህንፃ ጥበብ የተቃኘ እና በጎብኝዎቹ ላይ የብሩህ ተስፋ ስሜት እንዲፈጠር ታስበው የተሰሩ ናቸው።

## የአረንጓዴ ስፍራ













ይህ ቦታ ጎብኚዎች በእግር ጉዞ ወይም በጉዞ አጋዥ መሳሪያዎች የሚንሸራሸሩበት እና ከከፍታ ዙሪያ ገባውን የሚቃኙበት ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማን ከፊል ገጽታ ቁልቁል ለመመልከት ምቹ የሆነ ነው፡፡ በአረንጓዴ ስፍራው ልዩ ልዩ ተፈጥሯዊ መስህቦችን፣ ሀገራዊ ሀብቶችንና መገለጫዎችን የሚያንፀባርቁ የጥበብ ስራዎች ተካተዋል፡፡


የአንድነት መካነ እንስሳት

በዚህ የእንስሳት ስፍራ ሰው ሰራሽ የባህር እንስሳት መኖሪያ ገንዳን (አኳርያም) ሳይጨምር ዝርያቸው ወደ 30 አይነት ብዛታቸው ደግሞ 220 ገደማ የሆነ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ብርቅየ የዱር እንስሳት የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ቀጭኔ፣ አቦ ሸማኔ፣ ሚርካት፣ ኢምፓላ እና ልዩልዩ አዕዋፋት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ የአንድነት ፓርክ አሁን ባለው ቁመና የበርካታ ጎብኚዎችን ቀልብ የሚስብ ከመሆኑም በተጨማሪ ለሀገራችን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን የሚያገለግል ፓርክ ነው፡፡











ምንጭ :- አንድነት ፓርክን በተመለከተ ከተዘጋጁ ጽሁፎች ውስጥ ለማስተማሪያነት በሚያመች መልኩ የተወሰደ

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በደብተራችሁ ጻፉ።**

1. ለቱሪዝም እድገት አስተዋፅዖ የሌለው የቱ ነው?

    ሀ. ጎብኚዎች ባህላችንን እንዲያከብሩ ማድረግ

    ለ. የራሳችንን ባህል መጠበቅ፡፡

    ሐ. ማህበረሰቡን ስለቱሪዝም ጥቅም ማስተማር

    መ. ለቅርሶች ትኩረት መንፈግ

2. ‹‹የግብር አዳራሽ ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

    ሀ. ግብር የሚከፈልበት ቦታ    ለ. የነገስታት የምግብ አዳራሽ

    ሐ. የስብሰባ አዳራሽ    መ. ቤተ መንግስት

3. ‹‹ዙሪያ ገባውን›› የሚለው ሐረግ የሚያስተላልፈው መልዕክት

    ሀ. የሚወጣ የሚገባውን    ለ. የሚሽከረከረውን

    ሐ. አካባቢውን    መ. ዙሪያ መዞርን

4. የአንድነት ፓርክ በውስጡ ስንት የቱሪዝም  ዋና ዋና መስህቦች አሉት?

    ሀ. አራት    ለ. አምስት

    ሐ. ስምንት    መ. ስድስት

5. የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ----------- ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው፡፡

    ሀ. ለውጭ ምንዛሬ ማስገኛ    ለ. ለጥናትና ምርምር

    ሐ. ለእውቀትና ለመዝናናት    መ. ሁሉም መልስ የሆናሉ

6. ‹‹ አንድነት ፓርክ ›› የሚለው ርዕስ ምንን ያመለክታል?

    ሀ. ነጠላ ቁጥርን    ለ. በብዙነት ውስጥ ያለ አንድነትን

    ሐ. መረዳዳትን    መ. ተመሳሳይነትን

7. ኢትዮጵያ በዩኒስኮ ካስመዘገበቻቸው ቅርሶች መካከል የማይካተተው_ ነው፡፡

ሀ. የሀረር ግንብ　　　　　ለ. የአፄ ፋሲል ቤተመንግሰት

ሐ. የአንድነት ፓርክ　　　　መ. ኤርታሌ

## ተግባር ሶስት

**በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሀሰት» በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

ሀ. የክልል እልፍኞች የየክልሉን ባህል በተወሰነ መልኩ ይገልጻሉ፡፡

ለ. የአገር በቀል ዕጽዋት ተብለው የሚታወቁት ለምግብና ለመድሐኒትነት የሚሆኑ ናቸው፡፡

ሐ. የቤተመንግስቱ አጠቃላይ ስፋት አርባ ሄክታር መሬት ነው፡፡

መ. ታላቁ ቤተመንግስትን የመሰረቱት አፄ ኃ/ስላሴና እቴጌ መነን ናቸው፡፡

ሠ. ባለ ጥቁር ጎፈር አንበሳ ያለበት ዋሻ ርዝመት 175 ሜትር ነው፡፡

## ተግባር አራት

**ተማሪዎች ምንባቡን በትክክል በድጋሚ አንብቡና ዋናውን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተራ በተራ በቃል አብራሩላቸው፡፡**

# ክፍል ሦስት:- ቃላት

## እምሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

ማስታወሻ

ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይዘው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ አንድ ቃል በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡፡

ሀ. እማሬያዊ ፍቺ:-

የአንድ ቃል የመጀመሪያ ቀጥተኛ ፍቺ ወይም የመዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው፡፡

ምሳሌ፡-ሀ. መሬት - ምድር

ለ. ዱባ- ተቀቅሎ የሚበላ ትልቅ ፍሬ

ሐ. ቤት - ከተለያዩ ግብዓቶች የተሰራ የሰው ልጅ መጠለያ

ለ. ፍካሬያዊ ፍቺ

አንድ ቃል ከመዝገበ ቃላዊ ፍቺ በተጨማሪ ሌላ ተደራቢ ፍቺ ሊኖረው ይችላል፡፡ አንድ ቃል በቀጥታ ከሚኖረው ፍቺ ባሻገር የሚሰጠው ሚስጥራዊ ፍቺ ፍካሬያዊ ፍቺ ይባላል፡፡ ፍካሬያዊ ፍቺ ብዙውን ጊዜ የሚመሰረተው በንፅፅር ላይ ነው፡፡ ንፅፅሩም ከአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ልማድ፣እምነትና አተያይ ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡

ምሳሌ፡-ሀ. ፍየል- ለፍላፊ

ለ. መሬት-ቻይ፣ ታጋሽ

ሐ. ዱባ-ወፍራም

ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት እማሬያዊ ፍቻቸውን በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ ፡- ዝግባ- በጣም ረጅም የሆነ የዛፍ አይነት

ድንጋይ- ለተለያየ ግንባታ የሚውል ግዑዝ ነገር

| | |
|---|---|
| ሀ. ቁራ | ሠ. ንብ |
| ለ. ሙጫ | ረ. ብርቱካን |
| ሐ. ሚጥሚጣ | ሰ. ነፋስ |
| መ. ምስጥ | ሸ. እርጎ |

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ፍካሬያዊ ፍቺ በመስጠት በደብተራችሁ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡- ምላጭ- መሰሪ

መሰላል - ረጅም

ሀ. ጥይት

ለ. እሳት

ሐ. ወንፊት

መ. ጽጌረዳ

ሠ. ፈረስ

ረ. ጉልቻ

### ተግባር ሶስት

**ተማሪዎች አምስት ቃላትን ፈልጋችሁ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### በሃላፊ ጊዜ አንቀፅ መፃፍ

### ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ባለፈው ሳምንት ያከናወናችሁትን ድርጊት በሃላፊ ጊዜ የተመሰረተ አንቀፅ በደብተራችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

ምሳሌ

ጎጃም ዳሞት አውራጃ ውስጥ ማንኩሳ በምትባል አገር ቦጋለ መብራቱ የሚባሉ ብዙ ዘመን በብቸኝነት የሚኖሩ ሰው ነበሩ፡፡ ቦጋለ መብራቱ ከድሀ ቤተሰብ የተወለዱ በዚያውም ላይ ድሆች ወላጆቻቸው ገና በህፃንነታቸው ሞተውባቸው ድህነት ሲያንገላታቸው ያደጉ ነበሩ፡፡ ትንሽ ከፍ እንዳሉ መጀመሪያ የፍየልና የጥጃ እረኝነት እየተቀጠሩ በኋላም እጃቸው እርፍ ለመጨበጥ ያክል መበርታት ሲጀምር ግብርና እየተቀጠሩ ይኖሩ ነበር፡፡ በዚህ

ሁኔታ እኩል እድሜያቸውን ካሳለፉና የሚስት ማግባት ፍላጎታቸው እየቀነሰ ከሄደ በኋላ በጎልማሳነታቸው ጉልበታም ወዲያውም ጤናማ በመሆናቸው ረዳት ሳይፈልጉ ራሳቸውን ረድተው ለመኖር ቢችሉም ሚስት ካላገቡ እድሜያቸው እየገፋ አቅማቸው እየቀነሰ ሲሄድ ረዳት የሚያጡ መሆናቸውን ወላጆቻቸው አጥብቀው ስለመከሯቸው ከዚያው ከማንኩሳ ውድነሽ በጣሙ የሚባሉትን ሴት አገቡ፡፡

ምንጭ፡ ( ሀዲስ አለማየሁ ፤ፍቅር እስከ መቃብር 1996፡፡ ገጽ12 )፡፡

## ተግባር ሁለት

ከላይ በተግባር አንድ ላይ በሃላፊ ጊዜ ተመስርታችሁ የፃፋችሁትን አንቀፅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ ሌሎች ተማሪዎች ሲያነቡ ከራሳችሁ ስራ ጋር እያነጻጸራችሁ ጽሁፋችሁን ገምግሙ፡፡

## ተግባር ሶስት

‹‹ሰላም ለሰው ልጆች አስፈላጊ ነው›› በሚለው ኃይለቃል አንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ክፍል አምስት:- ሰዋስው

**ድህረ ግንድ ቅጥያ**

## ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ምሳሌውን መሠረት በማድረግ በዋና ቃሉ ላይ ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን እያጣመራችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ወንበር - ኦች ወንበሮች

መጣ -ኣችሁ መጣችሁ

ጫማ - ዎች ጫማዎች

ሀ. ደብተር - ኣችሁ

ለ. ገበሬ - ዎች

ሠ. መምህር - ኦች

ረ. ትምህርት - ኣችሁ

ሐ. መከረ - ኣት

ሰ. መጽሐፍ - ኡ - ን

መ. ተከሰተ - ኧች

ሸ. ንብረት -ኣቸው - ን

## ተግባር ሁለት

**በሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ውስጥ ያሉትን ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን በመነጠል በደብተራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡- ከቤት ከ - ቤት ስለሄደ ስለ - ሄደ

ሀ. እንደወረደ

መ. የነጀማል

ሰ. ከአዲስ አበባ

ለ. ስለፍቅር

ሠ. ወደመስኮት

ሸ. አስነሳ

ሐ. የመቅደስ

ረ. በህብረተሰብ

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ቅድመ አምድ ቅጥያ ከዋና ቃሉ ቀድሞ የሚገባ እንደሆነና ድህረ አምድ ደግሞ ከዋና ቃሉ በኋላ የሚጨመር መሆኑን ተምረናል። የቃላት እማሬያዊ ፍቺ ማለት የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ሲሆን ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ ቃላት በቀጥታ ከሚኖራቸው ፍቺ ባለፈ ያላቸውን ድብቅ ወይም ስውር ፍቺ እንደሆነ ማየት ችለናል። በመሆኑም ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት ችለናል። የሃላፊ ጊዜ የሚባለው አንድ የተፈጸመ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል መተረክ መሆኑን ተገንዝበን የሃላፊ ጊዜ ጽሁፍ ጽፈናል። እንዲሁም ያነበብነውን ጽሁፍ ጭብጥ ( ዋና መልእክት ) ማብራራት ችለናል።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ምንነት በቃላችሁ አብራሩ።
2. የቅድመና ድህረ አምድ ቅጥያዎችን ምንነት በምሳሌአስደግፋችሁ ጻፉ።
3. የጊዜ አይነቶችን በመዘርዘር ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጡ።

**4. የሚከተሉትን ቃላት በነፃና ጥገኛ ምዕላድ በመለየት አስቀምጡ**

ሀ. ስኣቶቻችን ሐ. ወንድሞቻቸው

ለ. በቴሌቪዥኖናቸው መ. ምንባብአችሁን

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት
# ጸረ-አደንዛዥ ዕፆች


ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትላችሁ ታነባላችሁ፡፡
- መረጃ ሰጪ ፅሁፎችን ትለያላችሁ፡፡
- አዳዲስ ቃላትን ከአገባቡ በመነሳት ትገምታላችሁ፡፡
- አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ሰካራሙ ተበጀ››







### ቅድመ ማዳመጥ

**ተግባር አንድ**

**ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላት በቃል ፍቺ ስጡ።**

ሀ. ገድል ሐ. ድብርት ሠ. አደንዛዥ ዕፅ

ለ. ሱስ መ. ጠንቅ ረ. መደንዘዝ

### የማዳመጥ ሂደት

**‹‹ሰካራሙ ተበጀ›› በሚል ርዕስ በገላጭ መልክ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት በትኩረት አዳምጡ።**

### አዳምጦ መረዳት

## ተግባር ሁለት

**ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻቹሁ አቅርቡ።**

ሀ. ሱስ ምንድን ነው?

ለ. ሰዎች ወደ ተለያዩ ሱሶች የሚገቡት ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. ‹‹ ከጠርሙስ ጋር ካልተገናኘ አይኑ አይገለጥም›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. ‹‹ የሚያላክኩበት ›› የሚለው ሐረግ ምንን ይገልጻል?

ሠ. የምንባቡን ጭብጥ (መልእክት) ከግል ህይወታችሁ ጋር በማገናኘት ተወያዩ፡፡

## ተግባር ሦስት

**የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ሀ. አድሮ ቃሪያ

ለ. ከድጡ ወደ ማጡ

ሐ. ሰርጉጀዋለሁ

መ. ማህበርተኛ

ሠ. ግብረ ገብ

ረ. የደበዘዘ

ሰ. የተመሰቃቀለ

ሸ. መሳለቂያ

## ተግባር አራት

**የአልኮል መጠጥ በቤተሰብ ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ በቡድን ተወያዩና በክፍል ውስጥ በንግግር መልክ አቅርቡ።**

## ክፍል ሁለት ንባብ

‹‹ጫትና መዘዙ››



### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር አንድ

ሀ. የጫት ሱስ ምን ጉዳት ያስከትላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ለ. በተለያየ ሱስ ምክንያት ያጋጠማችሁ ነገር ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹላቸው፡፡

ሐ. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

### የንባብ ሂደት

**ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በምክንያትና ውጤት እያስተሳሰራችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በተናጠል አንብቡ፡፡**

በሀገራችን በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች የሚጠቁ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ካሉት በርካታ የአደንዛዥ ዕፅ አይነቶች ውስጥ ደግሞ ጫት አንዱ ነው፡፡ በየአካባቢው የጫት ምርቶች ከሌሎች የሰብል አይነቶች ባልተናነሰ መልኩ በመጠን እየሰፋ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምርቱን ከአምራቾች ተቀብሎ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጩ ነጋዴዎች በዚሁ ልክ ተስፋፍተዋል፡፡ በትምህርት ተቋማት አካባቢ ሳይቀር ‹‹ትኩስ ጫት እናቀርባለን›› የሚሉ ማስታወቂያዎች ይስታዋላሉ፡፡ ይህም ለአደንዛዥ ዕፅ መስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋፆ አለው፡፡

ጫት መቃም በማህበራዊ ህይወት፣ በምጣኔ ሀብትና በጤና ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ያስከትላል፡፡ ጫት መቃም የሚያዘወትሩ ግለሰቦች ለከፍተኛ የጤና መታወክ ይዳረጋሉ፡፡ የስራ ጊዜያቸውን ጫት በመቃም የሚያሳልፉ ሰዎች ገንዘባቸውን ለጫት መግዣና መሰል ግብዓት ስለሚያውሉ ለችግር ይጋለጣሉ፡፡ ማህበራዊ ህይወታቸው የላላ ይሆናል፡፡ የጥሩ ስነ-ምግባር ባህሪ ባለቤት ቢሆኑም እንኳ በማህበራዊ ህይወታቸው ተቀባይነት የላቸውም፡፡

በጫት መቃም የተጠመደ ሰው በጤናው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥርበታል፡፡ አደንዛዥ ዕፁ በአዕምሮ ላይ የመነቃቃትና የደስታ ስሜት ቢያጎናፅፍም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ከፍተኛ ድብርት፣መረበሽ፣መጨነቅና አለመረጋጋትን ይፈጥራል፡፡ ሞልተው የነበሩ ተስፋዎች እንደጉም ተነው ይጠፋሉ፡፡ ቀስ በቀስም የሆድና የአንጀት ድርቀትን ያስከትላል፡፡ የምግብ ፍላጎትን በመቀነስ በተዋህሲያን አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳንሳል፡፡

1. ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ በማድረግ ከላይ ከቀረቡት አንቀጾች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ ?
2. ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አንቀጾች ስለምን የሚገልፁ ይመስላችኋል ?

በጫት ሱስ መጠመድ ለራስ ብቻ ሳይሆን መዘዙ ለቤተሰብም ጭምር ነው፡፡ ጫት ከሚቅሙ እናቶች የሚወለዱ ህፃናት በቂ ጡት ስለማያገኙ እድገታቸው ይቀጭጫል፡፡ በሌላ መልኩ በቤተሰቡ በሚፈጥረው አለመረጋጋት በልጆች ላይ ስነ-ልቦናዊ ጫና ይፈጥራል፡፡ ጫት በሚቃምበት ጊዜ ከሱስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ነገሮች፤እንደ ስኳር፣ለውዝና ጣፋጭ መጠጦች በዋናነት አብረው ይወሰዳሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች ከጫት ሱስ ጋር የሚወሰዱ ነገሮች ሲሆኑ ለተጨማሪ በሽታ መንስዔ ይሆናሉ፡፡ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ሀሽሽ

መውሰድና አልኮል መጠጣት ለድርብርብ በሽታና ጥንቃቄ ለጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ይዳርጋል፡፡

ጫት መቃም የጤና ጠንቅ ከመሆኑ ባሻገር ምጣኔ ሀብትን ያናጋል፡፡ የሚቅሙ ሰዎች በየጊዜው ለጫት መግዣ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ፡፡ የስራ ጊዜያቸውን በመቃም ስለሚያሳልፉ ገቢያቸው ይቀንሳል፡፡ በዚህ የተነሳ ቤተሰብን ለመምራት ይቸገራሉ፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ማለትም በደስታ፣ በሀዘን፣በስራና በተለያዩ ሁኔታዎች ግንኙነቶችን ያደበዝዛል፡፡ የማህበራዊ ግኘኙነት ክብርን ይቀንሳል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ አደንዛዥ እፅ የተለከፈ ሰው ለጤና፣ ለማህበራዊ ህይወት፣ለምጣኔ ሀብት እና ለመሳሰሉት ውስብስብ ችግሮች ይጋለጣል፡፡ የስራ ባህልን በመጉዳት ለጥገኝነት ይደርጋል፡፡ ስለሆነም ሁሉም ዜጋ አደንዛዥ ዕፆች ጎጅ መሆናቸውን አውቆ ግላዊ ነፃነቱን ለሱስ አሳልፎ ላለመስጠት መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡

ምንጭ:- (ከቀድሞው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 2007 ዓ.ም. ገጽ136 ለክፍሉ በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆነ**

**ደግሞ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. በሀገራችን በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች የሚጠቁ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል፡፡
ለ. ጫት መቃም በምጣኔ ሀብት እንጂ በጤና ላይ ጉዳት አያስከትልም፡፡
ሐ. በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች መጠመድ መዘዙ ከራስ አልፎ ለቤተሰብና ለሀገር ይተርፋል፡፡
መ. የአደንዛዥ ዕፆችን ዝውውር የመከላከሉ ሀላፊነት የሁሉም ዜጎች ነው
ሠ. አደንዛዥ ዕፆች ለድብርትና መረበሽ ይዳርጋሉ፡፡
ረ. ጫት አዕምሮን ስለሚያነቃቃ ጠቀሜታዉ ከፍተኛ ነው፡፡
ሰ. የጫት ሱስ ያለባቸው ሰዎች ጥሩ ስነ ምግባር ቢኖራቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

## ተግባር ሶስት

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. በትምህር ተቋማት አካባቢ ሳይቀር ትኩስ ጫት እናቀርባለን የሚሉ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ነው ፡፡

ያልጠወለገ ( ተቆርጦ ያልቆየ )

ለ. የጫት ነጋዴዎች መበራከት ለአደንዛዥ ዕፅ መስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ አለው፡፡

ተጽእኖ (አበርክቶ)

1. በጫት ሱስ መጠመድ በማህበራዊ ህይዎትና በምጣኔ ሀብት ላይ ኪሳራ ያስከትላል፡፡
2. የስራ ጊዜያቸውን በሱስ የሚያሳልፉ ሰዎች ማህበራዊ ህይዎታቸው የላላ ይሆናል፡፡
3. በጫት መቃም የተጠመዱ ሰዎች በጤናቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጠርባቸዋል፡፡
4. በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች መጠመድ መዘዙ ለቤተሰብና ለሀገርም ጭምር ነው፡፡
5. በበቂ ሁኔታ ተጠብቀው ያላደጉ ህፃናት እድገታቸው ይቀጭጫል፡፡
6. ለደባል ሱስ መጋለጥ ለድርብርብ በሽታና ለኤች. አይ. ቪ. ያጋልጣል፡፡

## ተግባር አራት

**በ ‹‹ሀ›› ምድብ ስር ለቀረቡት ቃላት ከ ‹‹ለ›› ረድፍ በፍቺ የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መጠመድ | ሀ. መታመም |
| 2. መታወክ | ለ. ራስን አለመቻል |

3. ድብርት ሐ. ምክንያት

4. መንስኤ መ. ድባቴ

5. ጥገኝነት ሠ. መያዝ

## ክፍል ሦስት:- ቃላት

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።**

ምሳሌ:- ኮረሪማ  አልማዝ በርበሬ ለማዘጋጀት ኮረሪማ ገዛች።

ምስጥ  ለአጥር የተተከለውን እንጨት ምስጥ በልቶታል።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሙቅ | ሐ.እሾህ | ሠ. ወንበር |
| ለ. ጨፌ | መ. ኩባያ | ረ. ወለላ |

**ተግባር ሁለት**

**የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች ስሩባቸው።**

ምሳሌ:- ሀ. ቆቅ  ዘመናይ ቆቅ ናት።

ለ. እሳት  የሱፍ በትምህርቱ እሳት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ባህር | መ. እርግብ | ሰ. ግስላ |
| ለ. ነቀዝ | ሠ. አንበሳ | ሸ ወርቅ |
| ሐ. አሳማ | ረ. ጎተራ | ቀ.ጥላሸት |

## ተግባር ሶስት

**በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፦ ጉቶ እማሬያዊ ፍቺ እንጨት ተቆርጦ ከስር የሚቀረው አካል

ፍካሬያዊ ፍቺ አጭር

ሀ. እስስት
ለ. ምሰሶ
ሐ. ቋንጣ
መ. ቁልፍ
ሠ. አልጋ
ረ. ኩራዝ
ሰ. ማር
ሸ.ተልባ

## ተግባር አራት

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን አዳዲስ ቃላት በምሳሌው መሰረት ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡-ሀ. የግል ንፅህናን አለመጠበቅ ለተስቦ በሽታ ያጋልጣል። ለተላላፊ በሽታ

ለ. ትናንት ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር መንገዱን ስቶ ማጥ ውስጥ ገባ። ረግረግ ቦታ(አረንቋ)

1. የቁጠባ ባህልን ማሳደግ የህይወት መድህን ነው ።
2. ከግብረገብነት ይልቅ ለንዋይ መሯሯጥ የስልጣኔ መገለጫ አይደለም።።
3. የከተማው ማህበረሰብ አካባቢውን ለማፅዳት በነቂስ ወጣ።
4.ደራሲው የጀመረውን የስነ-ፅሁፍ ስራ ባለፈው ሳምንት ቋጨ።
5. በሀገራችን የሚስተዋሉ ህፀፆችን የማስተካከሉ ድርሻ የሁላችንም መሆን አለበት።
6. ከትከሻዋ በታች ወርዶ የሚዘናፈለው ዞማ ፀጉሯ ውበቷን አጉልቶታል።

# ክፍል አራት:- ጽሕፈት

## ጅምር አንቀፆችን መጨረስ

### ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ተጀምረው ያልተጠናቀቁ አንቀጾች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. ልጅቱ ልቅም ያች ቆንጆ ናት። ጫማ የላትም ነገር ግን እግሯ እንሶስላ የሞቀች ይመስላል። ፀጉሯ ሽቶና ዘይት ነክቶት አያውቅም፤ በሳሙና ለመታጠብ እንኳን እድል አላገኘም፤ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዶ የተከበረውን ትከሻዋን አጥለቅልቆታል። መዘናፈሉም መልሰው መላልሰው ያጠፉት ይመስላል። አይኖቿ ኩል አያውቁም ነገር ግን . . . ።

ምንጭ:-(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣ኮሜት አጋዥ መፅሃፍ ከ9-10ኛ ክፍል፣2008ዓ.ም. ገጽ 307)

ለ. የሾላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት። በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካው ግቢ ውስጥ ካሉ ላሞችና በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ካሉ ገበሬዎች ይገዛል። ይህ የተገዛ ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ በተሽከርካሪ ተጭኖ ፋብሪካው ዘንድ ይደርሳል። ፋብሪካው ተቀብሎ እየመዘነ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለብጣል። ጋኑ ወተቱን በ100 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ያፈላና ወደ ሁለተኛው ማሽን በትላልቅ ቱቦ ያስተላልፈዋል። ሁለተኛው ማሽን በ22 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደገና ያፈላና ወተቱ ውስጥ ያለውን ክሬም ይለያል። ከዚያም....። (ደረጀ ገብሬ፣1996 ፣164)

### ተግባር ሁለት

**ከላይ ከቀረቡት ያልተሟሉ ሁለት አንቀጾች መካከል መረጃ ሰጪ የሆነው የትኛው ነው? ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ።**

### ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።**

ምንም እንኳን የሰላም መስፈን ለሰው ልጆች ህልውና አስፈላጊ መሆኑ ባያጠያይቅም በአንፃሩ ደግሞ ሁከትና ብጥብጥን የሚናፍቁ ሰዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም።የነዚህ ሰዎች አይናቸው መልካም ነገርን ማየት፣ጆሯቸው ቸር ወሬን መስማት አይፈልግም። ይህ

ደግሞ ያለምክንያት አይደለም፡፡ ‹‹የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል›› እንዲሉ እነዚህ ሰዎች ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሰርተው ከማግኘት ይልቅ በግርግር መሃል በአቋራጭ መክበር ስለሚፈልጉ ነው፡፡ ስለዚህ የዘወትር ፀሎታቸው ስለሰላም ሳይሆን ስለብጥብጥና ሁከት ነው፡፡ይሁን እንጂ በአቋራጭ ያገኙት ገንዘብ ሰላም እየነሳ እንደ ሰሳ ሲያስበረግጋቸው፣ እንደቆቅ ሲያስደነብራቸው ይስተዋላሉ፡፡ ምክንያቱም ‹‹ከቂጡ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም›› እነደሚባለው እያንዳንዱ እርምጃቸው በስጋትና በጥርጣሬ የተሞላ ነው፡፡

ምንጭ፡ (ታለጌታ ይመር ፣2007፣ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ ከገፅ 171-172)

## ተግባር አራት

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላት ቀጥሎ በቀረበው ባዶ ቦታ ውስጥ በማስገባት አንቀፁ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው አድርጉ፡፡**

| | |
|---|---|
| ነገር ግን | ይሆን ዘንድ |
| ስለዚህ | ያለምክንያት |
| ቢሆንም | እርግጥ ነው |
| እና | |

‹‹ሰው ከተሰማራ እንደየስሜቱ በዋለበት ስፍራ አይቀርም ማፍራቱ›› የተባለው--1-- አይደለም፡፡የሰው ልጁ በስራው ደስተኛ----2---- ውጤታማ----3---- እንደፍላጎቱ መሰማራት አለበት፡፡----4---- የእለት ጉርሱን ላለማጣት ሲል እየመረረው ----5----ሊሰራ ይችላል፡፡ ----6---- ስራውን የሚሰራው ያለፍላጎት በመሆኑ ውጤቱ አመርቂ አይሆንም፡፡----7---- ያለፍላጎት መኖር ብቻ ሳይሆን ችሎታም ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

# ክፍል አምስት:- ሰዋስው

## ተውላጠ ስም

ማስታወሻ ፡-

ተውላጠ ስም ስምን ተክቶ በመግባት የስምን ተግባር የሚፈጽም የስም ክፍል ነው፡፡ ነጠላና ብዙ ቁጠር አመልካች ተውላጠ ስሞች ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ ፡- እሱ ፣ እናንተ ፣ እኛ ተውላጠ ስሞች ከመደብ አንጻር 1ኛ ፣2ኛ እና 3ኛ መደብ ሲባሉ ከቁጥር አንጻር ነጠላና ብዙ ተብለው ይከፈላሉ፤ እንዲሁም ከጾታ አንጻር ተባዕትና አንስታ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## ተግባር አንድ

**የሚከተሉትን ቃላት በማስታወሻ ምሳሌው መሰረት ስሞችንና ተውላጠ ስሞችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

ሀ. አስቴር
ለ. ሀሰን
ሐ. እሷ
መ. እኛ
ሠ. ናትናኤል
ረ. አንቺ
ሰ. ኤደን
ሸ. አንተ
ቀ. እሱ
በ. እኔ
ተ. እናንተ
ቸ.እነሱ

| ተ/ቁ | ስም | ተውላጠ ስም |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |

## ተግባር ሁለት

**ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ በተውላጠ ስም ስር የመደባችኋቸውን ስሞች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- እሱ ነገ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ ይገባል፡፡

እሷ ዛሬ ከዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ትቀበላለች፡፡

ተግባር ሶስት

**ተስማሚ ተውላጠ ስሞችን በክፍት ቦታው በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡**

ሀ. --------- እና -------- ተባብረው ቢሰሩ ኑሯቸውን ማሸነፍ ይችላሉ:::

ለ. ------- በትምህርቷ ጎበዝ ልጅ ናት፡፡

ሐ. -------- መፅሀፍ ማንበብ የእለት ከዕለት ስራው ነው፡፡

መ. ------- ኢትዮጵያን በጣም ይወዳሉ፡፡

ሠ. --------- በህይዎቴ ስንፍናን አልወድም፡፡

ረ. ---------- ለምን ትምህርት ቤት ለመምጣት ታረፍዳለህ?

ሰ. -------- ከሌሎች ተማሪዎች በስነ-ምግባር የተመሰከረላችሁ ናችሁ፡፡

## ተግባር አራት

**በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በሚከተሉት ስሞች ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ዕፅዋት- ዕፅዋት የፀሐይ ብርሃንን ተጠቅመው ምግባቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

ብዕር - የሚፅፍበት ብዕር ደማቅ ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሠዓት | መ አዲስ አበባ | ሰ. ጠረጴዛ |
| ለ. አባይ | ሠ. እንስሳት | ሸ. ወረቀት |
| ሐ. መስኮት | ረ. እንጀራ | ቀ. እሳት |

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የተመለከትን ሲሆን እማሬያዊ ፍች ቃላት የሚኖራቸው ቀጥተኛ ፍቺ ሲሆን ፍካሬያዊ ደግሞ ቃላት ከቀጥተኛ ፍቻቸው ባሻገር የሚኖራቸው ሚስጥራዊ ፍቺ እንደሆነ ለማየት ሞክረናል፡፡በሌላ በኩል አውዳዊ ፍቺ ስንል ቃላት በተለያየ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡት ፍቺ መሆኑን አይተናል፤ አያያዥ ቃላትን በተገቢው ቦታ በማስገባት አንቀጽን አሟልተን ጽፈናል፡፡ አያያዝ ቃላት የፅሁፉ ትስስር እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የስምንና የተውላጠ ስምን ምንነት በማየት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተገቢው ቦታ በማስገባት ተጠቅመናል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. በሚከተሉት ግሶች ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

   ሀ. አወቀ ሐ. አጠበች ሠ. ሰጠ

   ለ. መጡ መ. ተደሰተች ረ. በላሁ

2. የስምና የተውላጠ ስም ምንነት፣ አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን በቃል አብራሩ፡፡
3. በጽሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላት ምን አይነት ጥቅም እንዳላቸው ግለጹ፡፡

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ሰባት
# የጥላቻ ንግግር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- መስማማትና አለመስማማትን የሚገልፁ ሀሳቦችን ታቀርባላችሁ፤
- ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር እንዴት እንደሚወገድ ትገልፃላችሁ፤
- ቅፅሎችን በመለየት ትጠቀማላችሁ፤
- የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትገልፃላችሁ፤
- ‹‹እናን›› እና ‹‹ነገር ግንን›› ተጠቅማችሁ ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ:- ማዳመጥ

### ‹‹ የጥላቻ ንግግርና የሚያስከትለው ጉዳት ››



**ቅድመ ማዳመጥ**

**ተግባር አንድ**

ሀ. ምስሉና ርዕሱ ምን አይነት ዝምድና ያላቸው ይመስላችኋል?

ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ምን እንደሚናገር ገምቱ፡፡

የማዳመጥ ሂደት

**‹‹የጥላቻ ንግግርና የሚያስከትለው ጉዳት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በትኩረት አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. በሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ የተሳተፉት ባለስልጣናት ብቻ ነበሩ፡፡

ለ. በጥላቻ ንግግር የተነሳ በዓለም ላይ ብዙ እልቂቶች ተከስተዋል፡፡

ሐ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት በት/ቤት መከላከል ይቻላል፡፡

መ. በማህበራዊ ገጽ የሚሰራጩ አግላይ መረጃዎች ከጥላቻ ንግግር አይመደቡም፡፡

ሠ. የሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ የተተገበረው በቱትሲ ጎሳዎች ላይ ነበር፡፡

ረ. የጥላቻ ንግግር በሰዎች ላይ አሉታዊ አስተሳሰብ ያሳድራል፡፡

### ተግባር ሶስት

**በሚከተሉት ቃላት አገባባዊ ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

- ምሳሌ፡- ግጭት

  ፋይዳ

- ሰዎች በጥላቻ ንግግር ወደ ግጭት መግባት የለባቸውም፡፡
  አገባባዊ ፍቺ   አለመግባባት፣ ጠብ

- ለሀገር ፋይዳ ያለው ነገር ለማበርከት መተባበር ያስፈልጋል፡፡
  አገባባዊ ፍቺ   ጠቀሜታ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. መናኛ | ሐ. ማፈንገጥ | ሠ. ማጎልበት | ሰ. ገደብ |
| ለ. ትስስር | መ. ጥላቻ | ረ. ማግለል | ሸ. በእንዝህላልነት |

### ተግባር አራት

**ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ርዕሶች መካከል አንዱን መርጣችሁ በመዘጋጀት ንግግር አቅርቡ፡፡**

ሀ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት እንዴት ሊስፋፋ ይችላል?

ለ. ህግ በማውጣት ብቻ የጥላቻ ንግግርን መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል? በምክንያት አስደግፋችሁ አብራሩ።

ሐ. በጥላቻ ንግግርና በሐሰተኛ መረጃ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## ክፍል ሁለት:- ንባብ

‹‹ የጥላቻ ንግግር››



### ቅድመ ንባብ

### ተግባር አንድ

ሀ. የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? በምን ምክንያት ሊፈጠር ይችላል?

ለ. የጥላቻ ንግግር በማህበረሰቡ ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሐ. የጥላቻ ንግግር መገለጫዎቹ ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ?

## የንብብ ሂደት

### ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ  በየተራ እየወጣችሁ ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ በትክክል አንብቡ

የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ውጤታቸው ተመሳሳይ ቢሆንም አካሄዳቸው ግን የተለያየ ነው፡፡ የጥላቻ ንግግርን ምንነት በተመለከተ ቁርጥ ያለና ወጥ ብያኔ የለውም፡፡ ይሁን እንጅ በርካታ ብያኔዎች የሚጋሯቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ማንኛውም የዘር ጥላቻን፣ የሌላ ሀገር ዜጋን ወይም ስደተኛን በጭፍኑ መጥላት፣ትዕግስት አልባና አግላይና ሌሎች  ሰበብ እየፈለጉ መገለል እንዲደርስባቸው የሚሰብኩ፣ የሚያሰራጩ፣የሚያነሳሱ፣ የሚያበረታቱ ገለፃዎች፣ ፅሁፎች፣ ምስሎችና ስዕሎች፣ ቅርፃቅርፆች በሙሉ የጥላቻ ንግግር ይሰኛሉ፡፡ የጥላቻ ንግግር እጅግ ብዙ የሆኑ በጎ እሴቶችን የመናጃ መንገድ ነው፡፡ ጥላቻ ላይ የተመሰረቱ ወንጀሎችን መጥሪያም ነው፡፡ አድሎና መገለልን ያስከትላል፡፡ የአንድን ወገን አባላት፣የሀይማኖት ተከታዮች፣ስደተኞችንና ሌሎች ቡድኖችን ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት በጭፍኑ እንዲጠሉ መንገድ ይከፍታል፡፡

1. ታሪኩን ከማንበባችሁ በፊት የሰጣችሁት ግምት ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ለምን? የምንባቡ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦችን አንስቷል?
2. ቀጣዩ የምንባብ ክፍል ምን ሀሳብ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ሐሰተኛ መረጃ የመረጃውን ሐሰተኝነት ወይም እውነተኛነት ለማጣራት በቂ ጥረት ሳይደርግ የሚሰራጭ ሲሆን ሁከት፣ ግጭትና ጥቃት እንዲደርስ የሚያደርግ ተግባር ነው፡፡ የሀሰተኛ መረጃ  ህዝብን፣ ሃይማኖትን፣ ዘርን፣ ፆታን፣ አካል ጉዳተኝነትን ወይም ሌሎች በህግ የተጠበቁ ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ የሚፈጸም የማግለልና መድሎ የመፍጠር ሁኔታንም ጭምር ያካተተ ተግባር ነው፡፡  የሀሰተኛ መረጃ  ስርጭት በሚከናወንበት ጊዜ በግለሰብ፣ በቡድን፣ በንብረትና በህይወት  ላይ ከፍተኛ  ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

የጥላቻና ሀሰተኛ  ንግግር ሆን ተብሎ፣ ታስቦበት ወይም በአንዝህላልነት የሚሰራጭ ንግግር ሲሆን በሕግ መከልከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ነው፡፡ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማህበራዊ ግንኙነት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሃገራዊ አንድነት፣ ለሰብአዊ ክብር፣ ለብዝሃነትና ለእኩልነት ጠንቅ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በመሰረታዊ  የሰው ልጅ መብት ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ መደንገግ አለባቸው፡፡ ኢትዮጵያም በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን ዓላማ ለማሳካት

አስፈላጊ የሆኑ፣ተመጣጣኝና በልኩ የተበጀ የጥላቻና የሀሰተኛ ንግግር አዋጅ ደንግጋለች፡፡

የጥላቻ ወይም ሀሰተኛ ንግግር በተለያዩ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካኝነት የሚተላለፍ ነው፡፡ የሀሰተኛ መረጃ ስርጨት በማናቸውም የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችና ስልቶች አማካኝነት ለበርካታ ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡ሰዎች መረጃን በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን መልዕክት ለመለዋወጥ፤ትስስርን ለማዳበር፤ ሀሳብን ለመጋራት የምንጠቀምበት በበይነ መረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ተግባር መረጃ የመጋራት ተግባር እውቀትን፣ ክህሎትንና ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን ለመረዳት ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ በተቃራኒው ከማህበረሰቡ እምነትና እሴት ያፈነገጡ፣እኩይ ነገሮችን ለማጉላት፣በመረጃና በማስረጃ ያልተጣሩ ነገሮችን ለማሰራጨት፣ በሰዎች መካከል ልዩነትን ለመፍጠር ሆን ተብሎ በሚሰራበት ጊዜ መጠራጠርን ይፈጥራል፡፡

ሰዎች ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ ግጭት የሚቀሰቅስ፣ ሕዝብን፤ ሃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን እና አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥላቻ ከሚያስፋፉ ንግግር እንዲቆጠቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ መቻቻልን፣ መተማመን፣ መከባበርና መግባባትን ማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማጎልበት የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃዎችን ስርጭት ለመቆጣጠር ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

የጥላቻ እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን የመከላከል ሀላፊነት የሁሉም ሰው ድርሻ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎችና መሰል ዘዴዎች አማካኝነት በጽሁፍ፣ በስዕል፣ በድምጽ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል ማሰራጨት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ በአንፃሩ ትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር፣ ትክክለኛ እና እውነተኛ የዜና ዘገባ፣ የፖለቲካ ትንታኔ ወይም ትችት፣ ልዩ ልዩ ኪነ-ጥበባዊ ትወናዎችና ፅሁፎች፣ የሃይማኖታዊ አስተምህሮቶች፣ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ምክክሮችና ውይይቶች ወዘተ እንደ ጥላቻ እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ተደርገው አይወሰዱም፡፡

ማንኛውም ሰው ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቱን ተጠቅሞ የተከለከለውን የጥላቻ ንግግር በማድረግ ለግጭትና ለብጥብጥ ምክንያት የሚሆን ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀፅ 4 መሰረት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከ፶ሺ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ የሚቀጣ ይሆናል፡፡ በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ አመት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀፅ ፫ መሰረት ክልከላ የተደረገበትን

ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ደግሞ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ በቀላል እስራት ወይም ከብር ፶ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡ የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ግን ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

ሐሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ እና ሁከት ወይም ግጭት ከተከሰተ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡ በጥላቻ ንግግር ወይም በሐሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈጸም ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ግን ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ እና ጥፋተኛውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን ይችላል፡፡

ምንጭ (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 26ኛ አመት ቁጥር 26 12339 መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም መሰረት ተደርጎ ለማስተማር ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ሐሰተኛ መረጃ በቂ ማጣራት ሳይደግበት የሚተላለፍ መረጃ ነው፡፡
ለ. የጥላቻ ንግግር ማግለልና መድሎን ያጠቃልላል፡፡
ሐ. ሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡
መ. የጥላቻ ንግግር በሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡
ሠ. ለሐሰተኛ መረጃ ስርጭት መገናኛ ብዙሃን ድርሻ የላቸውም፡፡
ረ. የጥላቻ ንግግር በማሕበረሰቡ ላይ ችግር አያስከትልም፡፡
ሰ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን መከላከል የፍርድ ቤት ድርሻ ነው፡፡
ሸ. መቻቻልና መከባበርን ማዳበር የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ይጠቅማል፡፡

**ተግባር ሶስት**

**የሚከተሉትን ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፈልጋችሁ በደብተራችሁ ፃፉ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. አብነት | ሐ. ምናብ | ሠ. ሙስና | ሰ. ዳኅሰ | ቀ. አጥቢያ |
| ለ. ደባ | መ. ለበጣ | ረ. ሰርግና ምላሽ | ሸ. አጤነ | በ.ብርሃን |

## ክፍል ሶስት ቃላት

## የቃላት አገባባዊ ፍቺ

**ተግባር አንድ**

**በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሚሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የውሃ ሽታ | ሀ. አንድነት |
| 2. ህብር | ለ. ግምገማ |
| 3. ቃል አባይ | ሐ. ብርድ |
| 4. ቆፈን | መ. ዋሾ |
| 5. ሂስ | ሠ. ደብዛው የጠፋ |

**ተግባር ሁለት**

**ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጣችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ስኬት | ሐ. ቆረጠ | ሠ. መዘርጋት |
| ለ. አንጋፋ | መ. መዋለል | ረ. ታታሪ |

## ክፍል አራት:- ጽሕፈት

### አስመስሎ መፃፍ

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ሀቅና የግል አስተያየት በማለት በቃላችሁ መልሱ።**

ምሳሌ

- ባልና ሚስቱ የታረቁት በሀገር ሽማግሌዎች ሳይሆን አልቀረም። የግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ
- ተማሪው ያስመዘገበው ውጤት ወደ ሚቀጥለው የክፍል ደረጃ አያሸጋግረውም። በሀቅ ላይ የተመሰረተ

ሀ. ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ሽልማት ተሰጣቸው።

ለ. ዘመናችን ሳይንስና ቴክኖሎጅ እየተስፋፋ የመጣበት ዘመን ነው።

ሐ. ሁሉም ጎበዝ ተማሪዎች በስነ- ምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው።

መ. ሰርግ መደገሱን የተወቸው ገንዘብ ስለቸገራት ሳይሆን አይቀርም።

ሠ. ህፃናት በስነ- ምግባር ታንፀው ማደግ አለባቸው።

ረ. በወጣትነት ዘመን ትዳር መያዝ ለድህነት ያጋልጣል።

ሰ. ሁሉም ቋንቋዎች የተናጋሪዎችን ባህልና ወግ በመግለፅ ረገድ እኩል ናቸው።

ሸ. የኑሮ ውድነት በቀጣይ አመት መሻሻሉ አይቀሬ ነው።

ቀ. ህፃናት እስከ ስድስት ወር ድረስ የእናት ጡት ቢጠቡ ለጤናቸው ተስማሚ ነው።

በ. የሕዳሴ ግድብ ከሀገራችን አልፎ ለጎረቤት ሀገሮች የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።

ተግባር ሁለት

**ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክክል አንብባችሁ ተመሳሳይ ፅሁፍ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

የክረምት ወቅት ነው፡፡ ዝናቡ ያዝ ለቀቅ እያደረገ ሲያስቸግር ውሏል፡፡ ፀሐይም በተራዋ ብቅ ጥልቅ እያለች ቆይታ በመካከሉ ጭራሹን ተሸሸጋለች፡፤ ወጨፎ ያዘለው ነፋስም ደረስ መለስ እያለ ሰው ማወኩን ተያይዞታል፡፡ ወደ ሀገሯ ለመሄድ ያሰበችው መንገደኛ ያንን አስቸጋሪ በርሃ በጠራራ ፀሐይ ከማቋረጥ በጠፍ ጨረቃ መጓዝ እንደሚሻል ሲያወሩ ሰምታለች፡፡ በየስራው ቦታ ደፋ ቀና ስትል ኖራ ባጠራቀመችው ገንዘብ የገዛችውን አዲስ ልብስ ለብሳ በቁንጠኛ አረማመድ ሰበርሰካ እያለች ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ እስከ ውድቅት ከተጓዘች በኋላ ቅስፍ የሚያደርግ ውጋት ስለተሰማት እርምጃዋን ቀነሰች፡፡ የልብ ትርታዋ ጨምሯል፤ትንፋሿ በዝቷል፡፡ ድካሙ ልቧን ፍስስ እያደረገ ስላስቸገራት ትንሿን ለመሰብሰብ አረፍ አለች፡፡ ትንፋሿ መለስ ሲል ቀና ብላ ብታይ የክረምት ሌሊት አይመስልም፡፡ ከዳር እስከ ዳር ፍንጥቅጥቅ ያሉት ከዋክብት ለዚያ ድቅድቅ ጨለማ ፀዳል ሰጥተውታል፡፡ ባጠራቀመችው አዲስ ጉልበት ዳገቱን ጨርሳ አውላላ ሜዳ ላይ ደረሰች፡፡ ወዲያው ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ ለቁጥር የሚያዳግቱ አውሬዎች ከበቧት፡፡በድንጋጤ ላብ አጥምቋት ብንን ብትል ለካስ ይሔ ሁሉ በህልሟ ኖሯል፡፡

ምንጭ፡- (ከአስረኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅሀፍ የተወሰደ 2004፤5-6)

ተግባር ሦስት፡-

በቀረበላችሁ ምንባብ ላይ ያላችሁን አምለካከት በፅሁፍ አቅርቡ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

ቅፅሎችን መለየት

ተግባር አንድ

**ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ነጠላ ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለይታችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ.ሀያት እና መአዛ ትረካ ይወዳሉ፡፡ ነጠላ ዐረፍተ ነገር

ለ.ናትናኤል ያነበበውን መፅሀፍ ለወንድሙ መለሰ፡፡ ውስብስብ ዐረፍተ ነገር

ሀ. አስናቀችና ዘሪቱ እህትማማቾች ናቸው፡፡

ለ. የአየር ባየር ንግድ መነገድ ሀገርንና ወገንን ይጎዳል፡፡

ሐ. ተማሪዎቹ ወደ ሰባተኛ ክፍል ተዘዋወሩ፡፡

መ. ሀዲስ አለማየሁ የፍቅር እስከ መቃብር ደራሲ ናቸው፡፡

ሠ. በበዓላት ጊዜ አዳዲስ ልብሶችን መልበስ እወዳለሁ፡፡

ረ. ሰውን ያለስራው መጉዳት ህሊናን ያደማል፡፡

ሰ. መምህሮቻችን በስነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡

ሸ. አለሙ ለእናቱ ውሃ ቀዳ፡፡

ቀ. ኳስ መጫወት እወዳለሁ ግን እንድጫወት አይፈቀድልኝም፡፡

በ. መሀመድ በሚገባ ጊዜውን ከፋፍሎ ስለሚያጠና ፈተናውን አለፈ፡፡

## ተግባር ሁለት

**ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለዩና በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ

ፍቅርተ ጓደኛዋ ያቀበለቻትን ኳስ መታች፡፡ አቀበለቻት፣ መታች

የጓሮ አትክልት በመሸጥ ቤታቸውን አሳመሩ፡፡ በመሸጥ፣ አሳመሩ

ሀ. መአዛ አባቷ ስለመጡ ተቀበለቻቸው፡፡

ለ. ያሲን ከተቀመጠበት ፈጥኖና በርግጎ ተነሳ፡፡

ሐ. አዛውንቶቹ በጥምቀት በዓል በርኖስ ለብሰዋል፡፡

መ. አያቴ የገዛችው መኪና በጣም ያምራል፡፡

ሠ. ከትምህርት ቤት ሲመለስ የደንብ ልብሱን ቀየረ፡፡

ረ. የሞት አደጋ ሲያጋጥም የሟች ቤተሰብን ማፅናናት ያስፈልጋል፡

## ተግባር ሶስት

**''እናን'' እና ''ነገር'' ግን የሚሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም በምሳሌው መሰረት ስምንት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።**

ምሳሌ

ሀ. ነጃት እና መሰረት ያነበቡትን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻቸው ነገሯቸው።

ለ. ያች ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት ነገር ግን መቅረት ታበዛለች።

## ተግባር አራት

**ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅፅሎች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአይነት፣ የባህሪና የመጠን አመልካች እያላችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ መድቡ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰነፍ | በጎ | ሞኝ | ሆዳም | ሰማያዊ |
| አጭር | ረጅም | ደንዳና | ሮዝ | ቀያይ |
| ንቁ | ግዙፍ | አረንጓዴ | ጠባብ | |

| ተ/ቁ | አይነት አመልካች ቅፅል | ባህሪ አመልካች ቅፅል | መጠን አመልካች ቅፅል |
|---|---|---|---|
| 1 | ቢጫ | ሩህሩህ | ቀጭን |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

### ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሀቅና የግል አስተያየት ምንነት ለማየት ሞክረናል፡፡ ሀቅ የሚባለው በእውነታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የግል አስተያየት ደግሞ በየግለሰቡ አመለካከት የሚወሰንና የሚሰነዘር ሀሳብ እንደሆነ አይተናል፡፡ ቅፅል ከስም በፊት እየገባ ስሙን ከአይነት ፣ ከመጠንና ከባህሪ አንፃር የሚገልጽ መሆኑን ተምረናል፡፡ እና፣ ነገር ግን የተባሉትን አያያዥ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ተጠቅመናል፡፡ የጥላቻ ንግግር ምንነትና ጉዳት ተረድተን መከላከልና ማስወገድ የሚቻልበትን መንገድ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ያላቸውን ግንኙነት አብራሩና እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተወያዩ፡፡
2. እና፣ ነገር ግን በሚሉት አያያዥ ቃላት አራት ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
3. ሀቅ እና የግል አስተያየት ምንነትና ልዩነት አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ስምንት
# ኤች አይ ቪ ኤድስ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለብዙ ቅጥያ ምዕላዶችን ታነባላችሁ፡፡
- የራሳችሁን አመለካከት ትጽፋላችሁ፡፡
- የፅሁፍ አላባውያንን ትገልፃላችሁ፡፡
- ለምዕላዶች ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ:- ማዳመጥ

‹‹ ያልጠረጠረ ተመነጠረ ››





### ቅድመ ማዳመጥ

### ተግባር አንድ

**ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ‹‹ያልጠረጠረ ተመነጠረ›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?

ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል ገምቱ፡፡

ሐ. ማንኛውም ሰው ወደ ችግር እንዳይገባ አስቀድሞ ምን ማድረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የማዳመጥ ሂደት

‹‹ያልጠረጠረ ተመነጠረ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የድርጊት ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ዋናውን ሀሳብ በቃል ተናገሩ፡፡

## አዳምጦ መናገር

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በፅሁፍ ፍቺ ስጡ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጠቃሚ | መ. ተጋለጥ | ሰ. አገገመ |
| ለ. እጣ ፋንታ | ሠ. መረጋጋት | ሸ. ትርፍ |
| ሐ. ስላፈራሁ | ረ. ምክር | ቀ. ማቋረጥ |

### ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን በቃል አቅርቡ፡፡**

ሀ. በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ እንዴት ሊተላለፍ ይችላል?

ለ. እራሳችንን ከኤድስ በሽታ እንዴት መከላከል እንችላለን?

ሐ. የኤድስ በሽታ ከሌሎች በሽታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ግለፁ፡፡

ሠ. እናንተ ስለኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መማራችሁ ምን ጠቀሜታ አለው?

ረ. ከባለታሪኩ ምን ተረዳችሁ? እናንተ ባለታሪኩን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

### ተግባር አራት

**ለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች? በሚለው ርዕስ ላይ ተወያዩና ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት ንባብ

### የኤች. አይ.ቪ. ኤድስ ተፅዕኖ





### ቅድመ ንባብ

#### ተግባር አንድ

ሀ. ሰዎች ስለኤች አይ ቪ ኤድስ በግልጽ አለመወያየታቸው ምን ጉዳት ያስከትላል?

ለ. ቫይረሱ በዋናነት የሚተላለፍባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ወጣቶችን ለበሽታው ተጋላጭ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድን ነው?

### የንባብ ሂደት

**ቀጥሎ «የኤች አይ ቪ ኤድስ ተፅዕኖ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማስተዋል በለሆሳስ አንብቡ፡፡**

የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል፡፡የማህበረሰቡ ጤናና ምጣኔ ሃብት ላይ የሚያሳድረውም ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም በወጣቶችና በጎልማሶች ላይ ያለው ስርጭት የጎላ ነው፡፡ የተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በበሽታው እየተጠቁ በሚመጡበት ወቅት በሀገር ላይ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ያጋጥማል፡፡

በዚህም በሀገር እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ የቫይረሱ መስፋፋት የምጣኔ ሀብታዊና የጤና ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ የሀገርን የህዝብ ስብጥርን ያዛባል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ኤች ኤ ቪ. ኤድስ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ከ15-49 የዕድሜ ክልል ያሉት ናቸው፡፡ በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙት ደግሞ አምራች ዜጎች ናቸው፡፡ ማምረት የማይችሉት ህፃናትን የሚያድጉትና አረጋዊያን የሚደገፉት በነዚህ አምራች ክፍሎች ነው፡፡ ወጣቶችና ጎልማሶች በቫይረሱ እየተጠቁ ከሄዱ ደግሞ ህፃናትና አረጋዊያን ያላሳዳጊና ጧሪ ይቀራሉ፡፡ በዚህም በሀገርም ሆነ በህዝብ ምጣኔ ሀብት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትላል፡፡በተጨማሪም የቫይረሱ ስርጭት መስፋፋት ሆስፒታሎች በኤድስ ህሙማን እንዲጨናነቁ በማድረግ የጤና አግልግሎት ችግር ይፈጥራል፡፡ በዚህ ምክንያት በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በሚመለከት ለሚያዙ መርሃ ግብሮች እንደሚወጣ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ገንዘብ ለሌሎች የልማት ስራዎች ቢውል በህዝብ ህይዎት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ ይችል ነበር፡፡

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ? ቀሪው የምንባብ ክፍል ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዜጎችን ለእንግልትና ለስቃይ ዳርጓል፡፡ በሺ የሚቆጠሩ ህፃናት ያለወላጅ ቀርተዋል፡፡ ይህም ለመንግስትና ለማህበረሰቡ አስቸጋሪ ፈተና ሆኗል፡፡ ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ወጣት ሴቶች እራሳቸውን፣ ታናናሽ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ለጎዳና ህይዎትና ሴተኛ አዳሪነት ተዳርገዋል፡፡ ወንዶችም ቢሆን የጎዳና ተዳዳሪ ሆነዋል፡፡ ኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሰዎችም በተለያዩ በሽታዎች ስለሚጠቁና ቶሎም ስለማይድኑ ከስራ ይቀራሉ፡፡ በስራ ላይ ያላቸው ውጤታማነት ከዕለት ወደ ዕለት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ይህ ደግሞ በግለሰብ ህይወት ላይ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡

ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያለባቸው ሰዎች ከጤናቸው መታወክ በተጨማሪ የሚደርስባቸው የስነ-ልቦና ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ዛሬም ቢሆን በበሽታው የተያዙ ሰዎችን የማግለሉ ችግር ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ በመሆኑ ህሙማን ቫይረሱ በደማቸው መኖሩ ከተረጋገጠ ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንደወትሮው ላይቀጥል ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የኤድስ ህሙማን የስነ-ልቦና ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ በተለይም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በሌላ በሽታ ለተያዙ ሰዎች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አይነት ለኤድስ ህሙማንም ስለማይደረግ ለኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ታማሚዎች ችግሩ እጥፍ ድርብ ነው፡፡ ይህ በራሱ በሽታውን ሊያባብሰው ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሀገር በማህበረሰብና በግለሰብ ዘንድ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ያስከትላል፡፡ ስለዚህ በበሽታው ከመያዝ በፊት እራስን መጠበቅ፣ ከተያዙም በኋላ ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ የድርሻን መወጣት ያስፈልጋል፡፡

(ስ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ፡፡ 1995 የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ት/ት ገፅ 29-31 ለስድስተኛ ክፍል በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ተግባር ሁለት

**ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡**

ሀ. መታወክ ሐ. መስፋፋት ሠ. እንግልት

ለ. መሰልጠን መ. ቀውስ ረ. ደጋፊ

## ተግባር ሶስት

**በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በፍቺ የሚተካቸውን ቃላትና ሀረጋት እያስገባችሁ ፃፉ፡፡**

ሀ. የህሙማን መጠን በየዓመቱ እየጨመረ ነው፡፡

ለ. ኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ ኤድስ በፍጥነት ከሚተላለፍባቸው ሀገራት አንዷ ናት፡፡

ሐ. በቫይረሱተጠቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ለበሽታ ያጋልጣል፡፡

መ. በርካታ ወጣቶች የአደንዛዥ ዕፅ ከተጠቀሙ እራሳቸውን መቆጣጠር ያቅታቸዋል፡፡

ሠ. የጤና ተቋማት ለበሽታውተጠቂዎች ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡

ረ. ቫይረሱ በአይን የማይታይ ተህዋስ ነው፡፡

### ተግባር አራት

**ኤች አይቪ ኤድስ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች በቡድን በመወያየት ቀጥሎ በተሰጠው ሰንጠረዥ ወስጥ ፃፉ።**

| ተ/ቁ | የሚተላለፍባቸው መንገዶች | የማይተላለፍባቸው መንገዶች |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

## ክፍል ሶስት:- ቃላት

### የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

### ተግባር አንድ

**በ‹‹ሀ›› ስርለቀረቡት ቃላትና ሀረጎችን በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ውስጥ ተቃራኒ የሚሆኑትን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጣፋጭ | ሀ. መሞቅ |
| 2. ጠቃሚ | ለ. አዝናኝ |
| 3. መበርታት | ሐ. መንቃት |
| 4. መደባለቅ | መ. መለያየት |
| 5. መብረድ | ሠ. መራራ |
| 6. ማጥቃት | ረ. መዘንጋት |
| 7. መፍዘዝ | ሰ. ጎጅ |
| 8. ማባባስ | ሸ. መከላከል |
| 9. መጠንቀቅ | ቀ. ማሻሻል |
| 10.አሰቃቂ | በ. መድከም |

## ተግባር ሁለት

**ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ቃል እየመረጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።**

1. ሀ. አከናወነ ለ. ሰራ ሐ. ፈፀመ መ. ተወ
2. ሀ. ተደነቀ ለ. ተሸለመ ሐ. ተጠሳ መ. ተመሰገነ
3. ሀ. አሯሯጥ ለ. አሰዳደር ሐ. አወቃቀር መ. አደራደር
4. ሀ. ዘገየ ለ. ፈጠነ ሐ. ቀለጠፈ መ. ሮጠ
5. ሀ. ወገን ለ. ዘመድ ሐ. ቤተሰብ መ. ጎረቤት
6. ሀ. ተበከለ ለ. ደፈረሰ ሐ. ጠራ መ. ቆሸሸ
7. ሀ. ማጥፋት ለ. ማልማት ሐ. ማበልጸግ መ. ማዳበር
8. ሀ. መበርገግ ለ. መሸበር ሐ. መደንበር መ. መዝናናት
9. ሀ. ጎጂ ለ. ጠቃሚ ሐ. አስፈላጊ መ. ወሳኝ
10. ሀ. መናደድ ለ. መደሰት ሐ. መበሳጨት መ. መቆጣት

## ተግባር ሶስት

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ እየመረጣችሁ አስገቡ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| መንገድ | ቀረጥ ቀረጥ | መቋጫው | ጥርግርግ | በተረጋጋ መንፈስ |
| ምናቡ | ጥቅልል | ብርድ ብርድ | ዘመም | ጥንካሬ |

ሀ. የዘሬ ጠዋቱ የከበደ እናት ቁጣ አየለን በ-----------እየታየው ስራ አላሰራ አለው።

ለ. ልትወድቅ የደረሰች ------------ያለች ጎጆ ውስጥ ሲያጠና ያድራል።

ሐ. ካፊያ ስለመታኝ ---------------አለኝ።

መ. መድሐኒት ወስጄ ስለነበር ሆዴን-------------ያደርገኛል።

ሠ. በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት---------------ፈተና ነው፡፡

ረ. የእሷ ችግር ከፊቴ ድቅን እያለ ስራዬን ------------መስራት አልቻልኩም፡፡

ሰ. ሰላምን በተለያየ --------------ማየት ይቻላል፡፡

ሸ. ማርን አዘውትሮ መብላት ለሰውነት -----------------ይረዳል፡፡

ቀ. ልጁ የቀረበለትን ምግብ ---------------አድርጎ በላ፡፡

በ. ዉሻው ስለበረደው ---------------ብሎ ተኝቷል፡፡

## ክፍል አራት:- ጽሕፈት

ማስታወሻ:-

የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጎራ ለይተው የሚያካሂዱት የሀሳብ ፍጭት ወይም ሙግት ነው፡፡እንደዚህ አይነት የሀሳብ ፍጭት በሚከናወንበት ጊዜ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የራሱን አመለካከት በሌሎች ላይ እንደፈለገው ከመጫን መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

የክርክር አተገባበር መርሆዎች:-

ሀ. ግልፅነት ያልተለየው አቀራረብ፤

ለ. በመረጃ ላይ የተመሰረተ አቀራረብ፤

ሐ. ስሜታዊነትን ማስወገድ፤

መ. እርግጠኛ ሆኖ ማቅረብ፤

ሀ. የክርክር ዝግጅት:-

- የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ፤
- ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ፤
- ከተሰበሰበው መረጃ ጠቃሚ የሆኑትን ብቻ መምረጥ፤

- ለአድማጮች ክርክሩን ከማቅረብ በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ፤
- ለክርክር ከመቅረብ በፊት መልካም ስነ ምግባር ተጎናጽፎ መገኘት፤

ለ. የክርክር አቀራረብ:-

- ራስንና የመከራከሪያ ርዕስ ጉዳዩን ለአድማጮች ማስተዋወቅ፤
- ፍሬ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ፤
- ክርክሩን ረጋ ባለ መንፈስ ማቅረብ፤
- ተቃራኒ ቡድን የሚያነሳውን ሀሳብ በማስታወሻ በመያዝ በመረጃ አስደግፎ ሀሳቡን በሀሳብ መርታት፤
- ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለማድረግ፤
- ክርክሩን ከአድማጮች ችሎታ ጋር መጥኖ ማቅረብ፤
- ለክርክር የተመደበውን ጊዜ ማክበር፤
- የክርክሩ ሂደት ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳይወጣ መጠንቀቅ፤
- የዳኞችን ውሳኔ በፀጋ መቀበል፤
- ክርክሩ ሲጠናቀቅ ታዳሚዎችን ማመስገን፡፡

ምንጭ፡-(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣1999-438)

## ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ የክርክር መመሪያን ተከትላችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አቅርቡ፡፡**

ሀ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከሃገር እድገት ጋር በተያያዘ ጎጂ ነው ጠቃሚ

ለ. የኮሮና ቫይረስን መከላከል ይቻላል ወይስ አይቻልም፡፡

ሐ. ለአንድ ሀገር እድገት መሰረቱ እርሻ ወይስ ኢንዱስትሪ፡፡

### ተግባር ሁለት

**በምሳሌ የቀረበውን ጽሁፍ አንብባችሁ ከስር ከቀረቡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ መግቢያ፣ሀተታና መደምደሚ ያ ያለው ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።**

ምሳሌ

ደን የዛሬውና የነገው ትውልድ የጋራ ሀብት ነው። በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ትኩረት ካልተሰጠው ወደ ፊት የማንወጣው ችግር ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን።ደኖቻችንን መጠበቅና መንከባከብ አለብን ስንል የሚሰጡንን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ዛፎች ፍሬያቸው ለምግብነት፣ እንጨታቸው ለማገዶና ለቤት መስሪያ፣ ስሮቻቸው ለአፈር ጥበቃ፣ ደኑ ለዱር እንስሳትና አእዋፋት መጠለያ፣ ቅጠሎቻቸው ለመድሃኒትና ለእንስሳት መኖ ይውላል። ከዚህም በተጨማሪ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብና የአካባቢውን የአየር ንብረት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። የምንመገበውንም ንፁህ አየር ይለግሱናል።

በአጠቃላይ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ የበቀሉ ዛፎችን በአግባቡ በመንከባከብና በመጠበቅ ከሚሰጡን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች በተጨማሪ የተፈጥሮ ሚዛንም እንዲጠበቅ ማድረግ ይገባል።

| | |
|---|---|
| ሀ. ፍትህ | መ. የትራፊክ አደጋ |
| ለ. የአየር ንብርት | ሠ. የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ |
| ሐ. መቻቻል | |

## ክፍል አምስት:- ሰዋስው

### ሳቢ/ተሻጋሪና ኢሳቢ/ኢተሻጋሪ ግስ

### ተግባር አንድ

**ከሚከተሉት ግሶች መካከል ሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰቀለ | ፃፈ | መገበ | አዘነ |
| ሰበረ | ሄደ | አነበበ | ሳከ |
| በጠሰ | ሸጠ | ቀደደ | ጨለመ |
| ሰጠ | ሆነ | ለበሰ | |

## ተግባር ሁለት

**ከሚከተሉት ግሶች መካከል ኢሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፈነዳ | ዘለለ | ቀጠነ | ቀበጠ |
| ነደደ | ደረሰ | አየለ | ወፈረ |
| ገዛ | ደከመ | ሳቀ | አኮረፈ |

## ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ምዕላዶች ነጣጥላችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡**

ሀ. ገጠመኞቻቸውን

ለ. በስነምግባራቸው

ሐ. ቤተክርስቲያናት

መ. ወራሾቻቸውን

ሠ. ሀላፊነቶቻቸውን

ረ. ወዳጅነታቸውን

ሰ. መስጊዱን

ሸ. ቅርንጫፎቻቸው

ቀ. ልጆቻቸውን

በ. በሚዛናዊነታቸው

## ተግባር አራት

**የሚከተሉትን ምዕላዶች አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡**

ሀ. ትምህርት-ቤት-ኦች-ን

ለ. በሬ-ዎች-ኣቸው-ን

ሐ. መቆጣጠር-ኢያ-ዎች-ኡ-ን

መ. አሳሳቢ-ነት-ኡ-ን

ሠ. እ-ሰራ-በት-ኣለሁ

ረ. ጓደኛ-ነት-ኣቸው- ም

ሰ. ከ-እንቅስቃሴ-ኣቸው

ሸ. አገልግሎት-ኣቸው-ን

ቀ. አስ-ተማሪ-ነት-ኣቸው-ን

በ. ማህበር-እ-ሰብ-አዊ-ነት-ኣችሁ-ን

ማጠቃለያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የድርሰት ክፍሎችን አይተናል፡፡ የድርሰት ክፍሎች የሚባሉት መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ መሆናቸውን፣መግቢያ ለሐተታ ሀሳቡ እንደመንደርደሪያ ሆኖ የሚገባ፣ ሐተታ የጽሁፉ አጠቃላይ ሀሳብ በዝርዝር የሚቀርብበት ሲሆን መደምደሚያ ደግሞ ሐተታው ላይ የቀረበው ሀሳብ ጠቅለል ተደርጎ ባጭሩ የሚገለጽበት ክፍል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የክርክር መመሪያ የዝግጅት እና አቀራረብ ጊዜ በማለት ለይተን መመሪያውን ተከትለን ክርክር አካሂደናል፡፡ ሳቢ(ተሻጋሪ) እና ኢሳቢ ( ኢተሻጋሪ) ግሶችን ለማየት ሞክረናል፡፡ ሳቢ ግስ ከተሳቢ ስም ጋር ሆኖ የሚዋቀርና ድርጊት ፈፃሚና ተቀባይ ያለው ሲሆን ኢሳቢ ግስ ግን ድርጊቱ በባለቤቱ ላይ የሚፈጸም መሆኑን ተምረናል፡፡ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተንና አጣምረን በመጻፍ አንብበናል፡፡ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ ዓረፍተ ነገሮችን የሚያሟሉ ቃላትን በማስገባት አስተካክለን ጽፈናል፡፡ ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ በፍቺ ልዩ የሆነውን ለይተን አሳይተናል፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. የጽሁፍ ክፍሎችን ጠቅሳችሁ ለእያንዳንዱ ማብራሪያ ስጡ፡፡
2. የሳቢ/ተሻጋሪና ኢሳቢ/የማይሻገሩ ግስ ምንነት፣ አንድነትና ልዩነት ግለጹ፡፡
3. የቅድመና ድህረ ክርክር ተግባራት ዘርዝሩ፡፡
4. ሳቢ/ተሻጋሪና ኢሳቢ/የማይሻገሩ ግሶችን መሰረት አድርጋችሁ ሶስት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ባህላዊ ልማዶች

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የተስማማችሁበትን ሀሳብ ታቀርባላችሁ፤
- አጫጭር ምንባብ አንብባችሁ ወደ ሰንጠረዥ ትቀይራላችሁ፤
- በቃል የሚነበብላችሁን አስተካክላችሁ ትጽፋላችሁ፤
- ከርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ትጽፋላችሁ፤
- የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ጠብቃችሁ ታነባላችሁ፤

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

### ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት



### ቅድመ ማዳመጥ

#### ተግባር አንድ

**ሀ. በአካባቢያችሁ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ታዉቃላችሁ? የምታውቁትን ተናገሩ?**

ለ. ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት እንዴት ይካሄዳል?

ሐ. ምስሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ?

### የማዳመጥ ሂደት

**«ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች» በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን እየለያችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መናገር

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።**

ሀ. በፍርድ ቤት የወንጀል ምርመራና በአውጫጭኝ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ምን ሊሆን ይችላል።

ለ. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እንደየ ማህበረሰቡ የተለያዩ ናቸው ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው?

ሐ. ሰዎች ጥፋት አጥፍተው በሽምግልና ቢዳኙ በህግ የሚፀና ይመስላችኋል?

መ. ሽምግልና በእድሜ የገፉ ሰዎች እንዲሆኑ የሚደረገው ልምንድን ነው?

ሠ. የዘመድ ዳኝነት፣ሽምግልና እና አፈርሳታ ሰላም እንዲሰፍን ጉልህ አስተዋፆ አላቸው ሲባል እንዴት ይገለፃል ?

### ተግባር ሶስት

**ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፉ።**

ሀ. ማስተናበር

ለ. አለመግባባቶች

ሐ. እርቅ

መ. ይረግባል

ሠ. ክረት

ረ. ሚዛናዊነት

ሰ. ተደማጭነት

ሸ. ፈንጠር ብለው

ቀ. አፈርሳታ

### ተግባር አራት

**በቡድን ሆናችሁ በትምህርት ቤታችሁ የሚፈጠሩ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ የስነዜጋና ስነ-ምግባር ክበብ ተጠሪዎችን በመጠየቅ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥበቃላችሁ አቅርቡ።**

### ተግባር አምስት

**ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ ቃላትና ሀረጋት በትክክል አዳምጡና አስተካክላችሁ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።**

## ክፍል ሁለት:- ንባብ

### ድግስ



**ቅድመ ንባብ**

**ተግባር አንድ**

ሀ. በቤታችሁ ውስጥ ድግስ የሚዘጋጀው በምን በምን አጋጣሚዎች ነው?

ለ. በአካባቢያችሁ ወይም በቤተሰባችሁ በድግስ ሰበብ ያጋጠመ ችግር ካለ ጥቀሱና የተወሰደውን የመፍትሄ ሀሳብ ተናገሩ።

ሐ. ድግስ ከመደገሳችን በፊት አስቀድመን ምን ምን ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ አለብን?

**የንባብ ሂደት**

ድግስ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ ግልፅ ያልሆኑ ቃላትና ሀረጋት ሲያጋጥማችሁ በማስታወሻ ጻፉ።

ድግስ በበዓላትና በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚደረግ ዝግጅት ነው፡፡ በሀገራችን በበዓላት ምክንያት ደግሶ ወዳጅ ዘመድን ሰብስቦ ማብላትና ማጠጣት ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ልማድ ነው፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች በእንቁጣጣሽ፣ በገና፣ በፋሲካና በመሳሰሉት፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ በአረፋ፣በመውሊድና በሌሎች በዓላት ወቅት ቤታቸውን ለየት ያደርጉታል፡፡ ሰርግ፣ተዝካር፣ ሰደቃ መሰል ባህሎችም እንዲሁ ብዙዎችን ድል ያለ ድግስ ሲጠይቁ የቆዩ ናቸው፡፡ በሹመትና በምርቃት ጊዜም ብዙ ሰዎች ድግስ ደግሰው ከመሰሎቻቸው ጋር መደሰትን የተለመደ ነገር እያደረጉት ቆይተዋል፡፡

እነዚህና ሌሎችም ድግሶች ከዓላማዎቻቸው አንፃር ሲታዩ ሊደገፉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ህዝባችን አብሮ በመኖር፣በመብላትና በመጠጣት አልፎም በእንግዳ ተቀባይነቱ ከሌላው የሚለይበትን ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ድግሶቻችን ከሚያስከትሉት ውጤት አንፃር ሲገመገሙ የሚነቀፉበት ብዙ ገፅታዎች ይታይባቸዋል፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት አንቀጽ ምን ተረዳችሁ?
2. አቅምን ያላገናዘበ ድግስ መደገስ ምን ምን ችግሮችን ይፈጥራል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ድግስ የሚደግሰው የተረፈውና ያለው ብቻ አይደለም፡፡ የሌለውም ተበድሮና ተለቅቶ ያደርገዋል፡፡ ከወር ወር ቆሎ፣ቂጣ፣ጎመን እየበላ፣ በጠፋም ቀን እንዲያው እየተዋለና እየታደረ በተኖረበት ቤት ሁሉ በበዓላት ዋዜማ ብዙ ነገሮች ይታሰባሉ፡፡ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ሽንኩርት፣ቅመማ ቅመም፣ቅቤ፣ዶሮ፣በግ፣ቅርጫ ስጋ ወዘተ. የግድ አስፈላጊ ነገሮች ሆነው ይገኛሉ፡፡ በሰርግና በሌሎች ባህላዊ አጋጣሚዎችም ብዙ ጊዜ ሰዎች ከአቅማቸው በላይ ሲያስቡና ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ድርጊታቸው የሚያስከትለው ችግር ከእነርሱም ተሰውሮባቸው ሳይሆን በይሉኝታና ከማን አንሼ በሚል ስሜት ተነድተው ባልፈለጉት ጣጣ ውስጥ ይዘፈቃሉ፡፡ በቀላል ወጪ ከዳሩ ወይም ካገቡ የሚሰነዘርባቸውን ትችት እየፈሩና የተናቁ እየመሰላቸው ያላቸውን አሟጠው ይደግሳሉ፡፡ ጥሎሽና ቀለበቱ፣በቤት ውስጥ የሚዘጋጀው ምግብና መጠጡ፣የእቃ ውሰቱ፣ ሽርሽሩና ጓዙ ወዘተ.አግቢዎችና ዳሪዎች ተጨንቀው የሚያደርጓቸው፣ሌሎችም እያለሙ የሚባንኑባቸው ቀልብ የሚነሱ፣ ስጋ የሚጨርሱ ነገሮች ናቸው፡፡

ይህ ለሁሉም አይቻልም፤ የሚቻልም ቢሆን ለውድድር ካልሆነ በስተቀር አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ እምብዛም አይደለም፡፡ ካቅሙ በላይ የደገሰው ወገን በድግሱ ሳቢያ ከሚመጣው ችግር በቀላሉ ሊላቀቅ አይችልም፡፡ ከተረፈው በስተቀር አለው የሚባለው እራሱ የአለውን አሟጥጦ ስለሚደግስ እንደገና መቋቋም ያዳግተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታይ ኑሮውን

በሚገባ መምራት አይችልም፡፡ ሳይኖረው ተበድሮ የደገሰ እዳውን መክፈል ስለማይችል ያልጠበቀው ጉዳት ይደርስበታል፡፡ይህንንበመሰለ ምክንያት በእዳ ተይዘውቤተሰቦቻቸውን ጥለው የጠፉ ጥቂት አይደሉም፡፡

ድግስ በሰለጠነውም ዓለም ቢሆን ጭራሹንም የቀረ ነገር ባለመሆኑ አያስፈልግምና አይኑር ማለት አይቻልም፡፡ የማያስፈልገውና ሊኖርም የማይገባው ድግስ የሚያስከትለው ችግር ነው፡፡ ችግሩ እንዲቀር ችግሩን የወለደው አደጋገስ መቅረት አለበት፡፡ በይሉኝታና ከማን አንሼ በሚል ስሜት ትርፉ ድካም፣ኪሳራና እዳ ከሆነው የድግስ ልማድና ባህል ለመላቀቅ ሁሉም በግሉና በጋራ ሊወስን ይገባል፡፡

ምንጭ፦(አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል 1997፣55-56 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሁለት

**በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ሰዎች በበዓላት ጊዜ ቤታቸውን ለየት ያደርጉታል ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. ሰዎች ሳይተርፋቸው ተቸግረው የሚደግሱት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ሐ. ከአቅም በላይ መደገስ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

መ. ችግሩ እንዲቀር ችግሩን የወለደው የድግስ ሥርዓት መቅረት አለበት የሚለው አገላለፅ ምን ማለት ነው፡፡

ሠ. የምንባቡዋና መልዕክት ምንድን ነው?

### ተግባር ሶስት

**በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት በፍቺ የሚስማሙትን ከ‹‹ለ›› ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ድል ያለ | ሀ. ተገፋፍተው |
| 2. ሲወርድ ሲወራረድ | ለ. ይገባሉ |

3. ይዘፈቃሉ ሐ. ችግር

4. ጥሎሽ መ. የሞቀ

5. ተነድተው ሠ. የማጫ ስጦታ

6. ጣጣ ረ. ተያይዞ የመጣ

## ተግባር አራት

**በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. በአጠቃላይ ድግስ መደገስ የሚደገፍበት ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ. ምንም አይነት ጉዳት ስለሌለው

   ለ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚያናጋ

   ሐ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚያሳድግ

   መ. ሽልማት ስለሚያስገኝ

2. አንዳንድ ሰዎች ያላቸውን አሚጠውና ተበድረው የሚደግሱት ለምንድን ነው?

   ሀ. የተናቁ ስለሚመስላቸው ለ. አስደሳች በመሆኑ

   ሐ. መልካም ባህል በመሆኑ መ. ትልቅ ትርፍ ስለሚያስገኝ

3. እንደ ምንባቡ አገላለጽ ሰው ቀጣይ ኑሮውን መምራት የሚያዳግተው ምን ሲሆን ነው?

   ሀ. ድግስ ሳይደግስ ሲቀር ለ. በአቅሙ ልክ ሲደግስ

   ሐ. በጣም ደስ ሲለው መ. ችግሩን መቋቋም ሲያቅተው

4. ድግስ አስፈላጊ የሚሆነው መቼ ነው?

   ሀ. በአቅም ልክ ሲደገስ ለ. ቤተሰብ ሲቀራረብበት

   ሐ. ከእዳ ነፃ ሲሆን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. ሰዎች ከአቅም በላይ መደገስ የሚያመጣው ጣጣ ተሰውሮባቸው ሳይሆን ከማን አንሽ በማለት ችግር ውስጥ ይገባሉ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ----------- ነው፡፡

ሀ. ግልፅ ሆኖላቸው ለ. ተረድተውት

ሐ. ሳይረዱት ቀርተው መ. መረዳት ሳይፈልጉ

6. ‹‹ቀልብ የሚነሳ፣ ስጋ የሚጨርስ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. የሚያከሳ ለ. የሚያስደስት

ሐ. ማራኪ የሆኑ መ. በጣም የሚያስጨንቅ

7. እንደምንባቡ ሀሳብ ድግስ የሚነቀፈው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ያለውን አሟጦ መደገሱ ለ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚቀንስ

ሐ. ከትርፍ መደገሱ መ. እንግዳ ተቀባይ አለማድረጉ

8. በድግስ ሰበብ ከሚመጣ ችግር መላቀቅ እንደማይቻል የሚገልፀው አንቀጽ

ሀ. አንቀጽ አንድ ለ. አንቀጽ ሁለት

ሐ. አንቀጽ አራት መ. አንቀጽ አምስት

## ተግባር አምስት

**ካነበባችሁት ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።**

# ክፍል ሶስት:- ቃላት

የቃላት መጥበቅና መላላት

## ተግባር አንድ

**ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች በምሳሌው መሰረት ፍቻቸውን በደብተራችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡- ደሙ ፈላ- ተናደደ፣ተቆጣ

ልቡ ተነሳ- ለመሄድ ተቻኮለ

ሀ.ሆዱን ሰጠ　　　መ. ቃሉን ሰጠ

ለ.ሀሳቡን ጣለ　　　ሠ. ጆሮ ሰጠኝ

ሐ. ነብር ሆነ　　　ረ. መንታ ልብ

ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ በዓረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ።**

ምሳሌ፡- መመገብ

የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው። ሲጠብቅ

ህፃናትን በሰዓቱ መመገብ ለእድገታቸው ወሳኝ ነው። ሲላላ

ሀ. ወተት　　　መ. ለጋ

ለ. መዳር　　　ሠ. ሳለ

ሐ. መማር　　　ረ. አያት

ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን አውዳዊ ፍች አሳዩ።**

ሀ. ማቋረጥ　　　ሐ. ቅርብ　　　ሠ. መቋቋም

ለ. ከፍተኛ　　　መ. መቀላቀል　　　ረ. መጨመር

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**ማመልከቻ**

ተግባር አንድ

**ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀጽ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቃችሁ አንብቡ።**

ዘነበ ፈረሱን እየጫነ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ አንድ ሰው ካዳራሹ ወጥቶ ወደርሱ ቀረበና ‹‹ስዓቱ ያንተ ነው፤በልዩ ተሸንፏል›› አለው። ይህን እንዳወቀ፣ ወዲያው የፀፀት ስሜት ተሰማው። በዚህ ወቅት ስለወንድሙ እንጅ ስለስዓቱ አላሰበም ነበር። ‹‹ወደቤቴ

ልሂድ? ወይስ ልቅር?›› እያለ ግራ ተጋብቶ ቆመ፡፡ የጨረታው ታዳሚዎች ካዳራሹ ወጡ፤በልዩም በመካከላቸው ነበር፡፡ ወንድሙ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ባየው ጊዜ፣ሀሳቡን እንደለወጠ ተረዳና፣‹‹ስለስዓቱ አመሰግንሃለሁ ዘነበ፣ከእንግዲህ በኋላ ወንድምህ እንተን እየተከተለ የሚሄድበትን ጊዜ ደግመህ አታየውም!›› በማለት፣ ጮሆ ተናገረ፡፡ ‹‹አንተም! ሁለተኛ እኔ ላንተ እሰራ የነበረውን ሁሉ ፈፅሞ ደግመህ አታየውም!›› ብሎ ሲመልስለት፣ ነብር ሆኖ ነበር፡፡ ወዲያውም ፈረሱ ላይ እምር ብሎ ወጥቶ እየጋለበ ሄደ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሁለቱም ከአባታቻው ጋር አብረው ይኖሩበት የነበረውን ቤት እግራቸው እረግጦት አያውቅም፡፡

ምንጭ፦ (በዓለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፣ትርጉም አምሳሉ አክሊሉ፣1981)

ተግባር ሁለት

**ከላይ የቀረበውን አንቀፅ በድጋሜ አንብባችሁ ፅሁፉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በቡድን ተወያይታችሁ አጭር ንግግር አድርጉ፡፡**

ተግባር ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክልል በማንበብ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በባዶ ቦታው ውስጥ አስገብታቸሁ ፃፉ፡፡**

በጣሊያን ወረራ ዘመን ለሀገራቸው ነፃነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር-----1---- ዘርጋ ናጂቁመቱ ረጅም ----2---አጥንቶቹ ሰፋፊ ------3----- መልኩ ቀይ-----4-----ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሶስትዮሽ የተሸረበ ነበር----5-----ያፀጉሩ በጀርባውና በትከሻው ላይ ተንዠርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናፅፈዋል------6--- ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆንጠቅላላ ገፅታው የሰው አይን የሚማርክ ሽበላ ----7-----ቆንጆ ነበር-------8------ዘርጋ አራት አመታት ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖርሹሩባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር-----9----በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሚት ያየችው ሴት ሁሉ------10----አይኔ ይፍሰስልህ ሳትል አታልፍም ነበር፡፡

ምንጭ፦ (አለም እሸቱ፣አለማየሁ ነሪን በመጥቀስ፣1999-24)

## ተግባር አራት

**በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘተሩት የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ጋር የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ትምህርተ ጥቅስ | ሀ. ተቆርጦ የቀረ ሀሳብ መኖሩን ለማመልከት |
| 2. ነጠላ ሰረዝ | ለ. እራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ሀሳቦችን ለመለየት |
| 3. ድርብ ሰረዝ | ሐ. ከሌላ ሰው የተወሰደ ሃሳብ መኖሩን ለማመልከት |
| 4. ትምህርተ ስላቅ | መ.ሀይለኛ ስሜቶችን ለመግለፅ ያገለግላል |
| 5. ቃል አጋኖ | ሠ. ተከታታይነት ያላቸውን ሀሳቦች ለመለየ |
| 6. ነጠብጣብ | ረ. ማሾፍን፣ ማሽሟጠጥን፣ ለመግለፅ |

## ተግባር አምስት

**ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ወደ ሰንጠረዥ ቀይራችሁ ፃፉ፡፡**

የደን ስርጭት በኢትዮጵያ በስኩዌር ኪሎ ሜትር ከ1973-1990ዓ.ም

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ1973-1990 ዓ.ም ባሉት አመታት ውስጥ የደን ስርጭቱ እየቀነሰ እንደመጣ ማየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከ1973-1976ዓ.ም ጥቅጥቅ ደን 30243 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 2.64% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990ዓ.ም ወደ 2346 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና ወደ 0.2% ቀንሷል፡፡ በመጠኑ የተመናመነ ደን ደግሞ ከ1973-1976 ዓ.ም 14158 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 1.24% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990ዓ.ም ወደ 7466 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 0.65% በመቶኛ ቀንሷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ደን ከ1973-1976 ዓ.ም 10009 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 0.87% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990 ዓ.ም ባለው ጊዜ 45055 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 3.93% በመቶኛ ማደግ ችሏል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ጥቅጥቅ ደንና በመጠኑ የተመናመነ ደን ቁጥሩ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነው ደን እየተሻሻለ የመጣ መሆኑ ነው፡፡

ምንጭ፡- (የብዝሃ ህይወት ሀብት በኢትዮጵያ 1998)

## ተግባር ስድስት

**ከዚህ በታች በምሳሌነት የቀረበውን የማመልከቻ ደብዳቤ መሰረት  በማድረግ የተማሪ ስነ ምግባር ችግር መኖሩን የሚገልፅ ማመልከቻ ደብዳቤ ለትምህርት ቤታችሁ አስተዳደር በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።**

ምሳሌ

ቀን 12/12/2013ዓ.ም

ለሰላም 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

<u>ጉዳዩ፡-ውጤት እንዲስተካከልልኝ መጠየቅን ይመለከታል፡፡</u>

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው እኔ ተማሪ ሉሊት ታደሰ የሰላም 1ኛ ደረጃ የ6ኛ ክፍል ተማሪ መሆኔ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የ1ኛው ወሰነ ትምህርት አጠቃላይ ውጤት ድምር ስለተሳሳተብኝ ሁለተኛ ደረጃ መውጣት ስችል አምስተኛ  ስለወጣሁ ትምህርት ቤቱ ትክክለኛ ውጤቴን አይቶ እንዲያስተካክልልኝ ስል በትህትና አመለክታለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ፊርማ--------

ሉሊት ታደሰ

# ክፍል አምስት ሰዋስው

## የኃላፊ ጊዜ

### ተግባር አንድ

**ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በኃላፊ ጊዜ የተመሰረቱትን ለይታችሁ አውጡ።**

ሀ. ልጁ የተዋሰውን መጽሐፍ ባለፈው ሳምንት መለሰ፡፡

ለ. ደራሲው ጥሩ የልቦለድ መጽሐፍ ለመፃፍ እያሰበ ነው፡፡

ሐ. ኀበዙ ተማሪ አንደኛ ለመውጣት ጥረት እያደረገ ነው፡፡

መ. ባለፈው ዓመት የቆሸሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር፡፡

ሠ. እንግዳው ትናንት ማታ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

ረ. ጨዋታውን ፊት ለፊት ተቀምጬ ለመመልከት ወስኛለሁ፡፡

ሰ. ባለፈው ዓመት ውድድሩን ያሸነፈው የኔ ፈረስ ነበር፡፡

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ግሶች በመጠቀም በምሳሌው መሰረት በኃላፊ ጊዜ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።**

ምሳሌ፡-ወሰደ

ኤርሚያስ ትናንት የገዛውን ጫማ ወሰደ፡፡

ሀ. ዘራ

ሐ. ወደደ

ለ. ጠበቀ

መ. ለበሰ

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስርአተ ነጥብ በጽሁፍ ውስጥ ሁለት ጠቀሜታ እንዳለው ተምረናል፡፡ ይኸውም የጽሁፍን ሀሳብ አሻሚ ባልሆነ መንገድ መረዳት እንዲቻል ማድረግና ጽሁፍ እንዴት መነበብ እንዳለበት ጥቆማ መስጠት እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ደብዳቤ ሀሳብ ማስተላለፊያ አንዱ መንገድ መሆኑንና የመስሪያ ቤትና የግል ደብዳቤ ተብሎ እንደሚታወቅ፣ የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ከመስሪያ ቤት ወደመስሪያ ቤት፣ወደግለሰብና ከግለሰብ ወደመስሪያ ቤት የሚፃፍ ሲሆን፣ የግል ደብዳቤ ደግሞ ከግለሰብ ወደግለሰብ የሚፃፍ መሆኑን አይተናል፡፡ ለፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ሰጥተናል፡፡ ለቃላት ተመሳሳይ፣ አውዳዊ ፍቺ፤ ሲጠብቅ ሲላላ የሚኖረውን ፍቺ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርተናል፡፡ በሀላፊ ጊዜ የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተናል፡፡ የሀላፊ ጊዜ ተጠቅመን ዓረፍተ ነገር መስርተናል፡፡

የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ከግል ደብዳቤ የሚለይበትን ባህሪ ግለጹ፡፡
2. ስርዓተ ነጥብ በጽሑፍ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ በምሳሌ አስደግፋችሁ ተናገሩ፡፡
3. የሚከተሉትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት አረፍተ ነገር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

   ሀ. አረዱት　　ሐ. ዓባይ　　ሠ. አርማ

   ለ. ሰፊ　　መ. ከፋ

4. በሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

   ሀ. ራሱን ቀበረ　　ሐ. ሰባራ ስንጥር

   ለ. ልቡ ቀና　　መ. ቀን ወጣ

አማርኛ
፮ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስር
# ሴቶችን ማብቃት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች�:- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የተሰማችሁን ምክንያታዊ ሆናችሁ ትገልፃላችሁ፤
- አስተካክላችሁ ታነባላችሁ፤
- የሰው የህይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፤
- ስርዓተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድታችሁ ታነባላችሁ፤
- ርቱዕና ኢርቱዕ ዓረፍተ ነገሮችን ትጠቀማላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ:- ማዳመጥ

## ‹‹ህልመኛዋ ወጣት››

### ቅድመ ማዳመጥ





### ተግባር አንድ

**ተማሪዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

ሀ. ስዕሎቹን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለፁ?

ለ. በርዕሱና በስዕሎቹ መካከል ምን አይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

ሐ. በአካባቢያችሁ ስኬታማ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላችሁ? የስኬታቸውስ ሚስጥር ምን ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

**መምህራችሁ‹‹ህልመኛዋ ወጣት››በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሲያነቡላችሁነ የድርጊት ቅደም ተከተሉን በጥሞና እያዳመጣችሁ ባዶ በታውን አሟልታችሁ ጻፉ።**

ሀ. የቤቱን ስራ በመስራት __________ ትወጣለች፡፡

ለ. ወርቅነሽ___________ቤተሰቦቿን ከማገልገል ይልቅ ለብቻዋ ማሰብ ጀመረች፡፡

ሐ. ‹‹የት ሄድሽ ?›› ሲሏት አባቷ _________ብላ ወደአክስቴ መሄድ እፈልጋለሁ አለቻቸው፡፡

መ. ዕድሜዋ ______ ስለነበር በክፍል ውስጥ ትልቋ እሷ ነበረች፡፡

ሠ. የተለያየ ______ ቢያጋጥማትም ተቋቁማ ውጤታማ መሆን ችላለች፡፡

ረ. መንግስትንና ባለሀብቶችን _____________ ትምህርት ቤት አስገነባች፡፡

ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ.ገፀ ባህሪዋ ያጋጠማትን መሰናክሎች ተቋቁማ ማለፍ የቻለችው እንዴት ነበር?

ለ. ወርቅነሽ ወደ አዲስ አበባ ባትመጣ ኖሮ ምን አይነት ህይወት የሚኖራት ይመስላችኋል?

ሐ. ‹‹የዚሁ እጣ ፋንታ ተቋዳሽ ነበረች›› የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

መ. የወርቅነሽ ወንድሞች ቢወዷትም ስራ ሊያግዟት ያልቻሉት ለምን ነበር?

ሠ. ተማሪዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ ታሪክ በድርጊት ቅደም ተከትል ተናገሩ፡፡

ተግባር ሶስት

**ተማሪዎች ከላይ ካዳመጣችሁት ምንባብ ያገኛችሁትን ቁም ነገር ተወያዩና በክፍል ውስጥ በየተራ ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት ንባብ

### ጀግኒት ትችላለች



ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ



ፓይለት አምሳለ ጓሉ




ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ

## ቅድመ ንባብ

### ተግባር አንድ

**ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።**

ሀ. ከላይ በስዕሉ የቀረቡት ሴቶች ታዋቂ የሆኑበትን ምክንያት ገምቱ።

ለ. በሀገራችን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሴቶች ቁጥር አናሳ መሆን ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

### ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።**

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| የ - ተፈራ - ረመ -ቻቸው - ን | የተፈራረመቻቸውን |
| ያ - ፀደቀ - ቻቸው - ን | ያፀደቀቻቸውን |
| የ - ማይደርስ - ኡ - በት | የማይደርሱበት |
| ባለ - ሙያ - ዎች - ን | ባለሙያዎችን |

## የንባብ ሂደት

**‹‹ጀግኒት ትችላለች ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ።**

በአንድ ሀገር የስርዓተ ፆታ እኩልነት እዲሰፍን፣ተገቢው የስርዓተ ፆታ ተግባቦትና መተሳሰብ እንዲኖር፣የሴቶች መብት እንዲከበር፣ እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነታቸው በአግባቡ እንዲረጋገጥ በትምህርት መደገፍ አለበት፡፡ አለበለዚያ አድሏዊ የስርዓተ ፆታ አመለካከትና ማህበራዊ እሴቶች፣ደንቦችና እምነቶች የሴቶችን የመማር መብት እውንነት ያደናቅፋሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች የሚማሩ ሴቶች ቁጥር አናሳ ይሆናል፡፡ቤተሰብ የአንድ ማህበራዊ ትስስር የሚጀመርበት መነሻ ተቋም እንዲሆን የሚጠበቅ ቢሆንም አድሏዊ ስርዓተ ፆታ ባለበት ማህበረሰብ የመብት ረገጣ የሚጀመርበትና የሚበረታታበት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህም ወላጆች ወንዶች ልጆቻቸውን ኀበዝ ሴቶቹን ደግሞ ሰነፍ እድረገው ሊቆጥሩ ይችላሉ፡፡ ወንዶችን በመደገፍ፣በማበረታታት በአንፃሩ ደግሞ ለሴቶች ድጋፍ እና ማበረታታት የማይደረግ ከሆነ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ማስፈን አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ ሴቶችን ለማብቃት በሚሰራው ስራ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በቤት ውስጥም የእኩልነት መብታቸው ተነፍጎ እንደወንዶች ታውቃላችሁ፣ ትችላላችሁ፣ እየተባሉ የማያድጉ ከሆነ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፤በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ይቀንሳል፤ በራስ መተማመናቸውም ይጎዳል፡፡ እነዚህና መሰል ስርዓተ ፆታዊ አድሎዎች የሴት ተማሪዎችን ውጤታማነት በእጅጉ ይፈታተናሉ፡፡

ትምህርት ቤቶችም ቢሆን በስርዓተ ፆታ ምክንያት ለሚፈጠረው የትምህርት ልዩነት ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው ነፃነት ሰፊ ነው፡፡ በብዙ ትምህርት ቤቶች መፀዳጃ ቤቶች፣የቤተ ሙከራ መቀመጫዎች፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የተመቹ ናቸው፡፡ የመማሪያ መጽሐፍቱም በሴቶች ትምህር ላይ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለያዩ መጽሐፍት ውስጥ ያሉትን ምሳሌዎች ብንመለከት እንኳን ወንዶችን ዶክተር፣ኢንጅነር፣ ፓይለት፣ተመራማሪ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ስዕሎቹም እንዲሁ ወንዶቹን ሲዝናኑ ሲጫወቱና ሲመራመሩ ያሳያሉ፡፡ ሴቶቹን ግን በቤት ውስጥ ተግባራት ተሰማርተው ቤት ሲጠርጉ፣ልብስ ሲያጥቡ፣ምግብ ሲያዘጋጁና ዝቅተኛ በተባሉ ስራዎች ላይ ሲሳተፉ ያሳያሉ፡፡‹‹ ወንድ ወደችሎት ሴት ወደማጀት›› የሚለውን ብሂል አንቅሮ በመትፋት ሴቶችን ማብቃት እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አይነት የሴቶችን ሚና አሳንሶ ማቅረብና ማሳየት ሴቶች በትምህርት ልቀው ራሳቸውን አሻሽለው በከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ ቦታዎች ላይ የመሳተፍ ህልማቸውን ስለሚጎዳ ሁሉም ሰው ሊጠነቀቅ ይገባል፡፡

1. ተማሪዎች እስከአሁን ካነበባችሁት ታሪክ ምን ተገነዘባችሁ?
2. ከዚህ ቀጥሎ ያለው የምንባብ ክፍል ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ስለሆነም የሴቶችን ድርብ ሀላፊነት ለማቃለልና የስራ ተነሳሽነታቸውን የበለጠ ለማጎልበት መማር የሚገባቸውን ሁሉ ለማስተማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡የባህሪ፣ ያስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በትምህርት ነው፡፡ ሴቶች የመማር እድሉን ካገኙ የራሳቸውን ፍላጎት በራሳቸው የመወሰን፣ የሚፈልጉትን ስራ የመስራት በራሳቸው ተማምነው የመኖር ብቃት ይኖራቸዋል፡፡ በመማራቸው የእድገት እንቅፋት የሆኑት ኋላቀር አመለካከቶች ቀስ በቀስ ይወገዳሉ፡፡ ለሁሉም ፆታዎች ፍትሃዊ ትምህርት እንዲያገኙ ‹‹ትምህርት ለሁሉም›› የሚለውን መርህ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለተግባራዊነቱም ሴት ልጆች ትምህርት ጀምረው እንዳያቋርጡ ትምህርት ቤቶችን ከመኖሪያ አካባቢ በቅርብ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ሴቶችን በአርዓያነት ማቅረብ የሴቶችን አቅምና ተሳትፎ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያም ሴቶችን ለማብቃት የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን፣አድሎአዊና ኢፍትሃዊ አሰራርን፣ ፆታን ማዕከል ያደረገ ጥቃትን ከመከላከል አንፃር የህግ ማዕቀፎችን በመጠኑም ቢሆን አዘጋጅታለች፡፡ ከታች እስከ ላይ መዋቅሮችን ዘርግታ ሴቶችን በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃዎችላይ እያሳተፈች ትገኛለች፡፡ተቋማትን መስርታ፣በጀት በጅታና ባለሙያዎችን አሰማርታ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ በተጨማሪም የተፈራረመቻቸውንና ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፋዊ፣አህጉራዊና ክልላዊ ስምምነቶችን እንዲሁም በህገ መንግስቱ ያፀደቀቻቸውን ድንጋጌዎች በማክበርና በማስከበር ረገድ ጠንካራ ስራ በመስራት ሴቶችን ለማብቃት እየሰራች ትገኛለች፡፡ሴቶች እድሉን ካገኙ በየትኛውም ደረጃ መብቃትና ማንኛውም የሰው ልጅ የደረሰበትን የማይደርሱበት ምንም አይነት ምክንያት የለም፡፡ ለዚህም ምስክሩ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ደረጃና ድንቅ ድንቅ ስራዎችን የሰሩ ሴቶችን ታሪክ ማየት ያስፈልጋል፡፡

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲሰፍን በትምህርት መደገፍ አለበት፡፡

ለ. ማህበረሰቡ ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች  ክብር በመስጠቱ የሴቶችን እኩልነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሐ. የሴቶችን የመማር እድል ለማሳደግ ትምህርት ቤቶች በቅርብ እርቀት መገንባት አለባቸው፡፡

መ. ከፍተኛ ቦታ ላይ የደረሱ ሴቶችን በአርዓያነት ማቅረብ ሌሎች ሴቶችን አያበረታታም፡፡

ሠ. በኢትዮጵያ የስፖርት ሜዳዎች ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች የተመቹ ናቸው፡፡

ረ. ኢትዮጵያ የሴቶችን መብት ለማስከበር አለማቀፋዊ ስምምነቶችን ፈርማለች፡፡

### ተግባር አራት

**ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፡-ተነፍጎ (አንቀፅ አንድ)   ተከልክሎ

ደንብ (አንቀፅ አንድ)   መተዳደሪያ ህግ

ሀ.  እንዲሰፍን (አንቀጽ አንድ)

ለ. ማዕቀፎች (አንቀጽ አራት)

ሐ. ትስስር (አንቀጽ አንድ)

መ. ሚና (አንቀጽ ሁለት)

ሠ. አርአያ (አንቀጽ ሶስት)

ረ. ማጎልበት (አንቀጽ ሶስት)

ሰ. መዋቅር (አንቀፅ አራት)

## ክፍል ሶስት:- ቃላት

**ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል**

## ተግባር አንድ

**ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡- ሀቀኛ- ቃል አባይ
ማድነቅ-ማኮሰስ

ሀ. አድኋዊ
ለ. እውን
ሐ. መግባባት
መ. ድሎት
ሠ. ክብር
ረ. ማጀት
ሰ. አናሳ

## ተግባር ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር ጥምር ቃል መስርቱና ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡-ስርዓት-ስነ    ስነ ስርዓት
ወለድ-ልብ    ልብ ወለድ

ሀ. ጥበብ-ኪነ
ለ. ምግባር-ስነ
ሐ. ቃላት- መዝገበ
መ.ሰናይ- ምግባረ
ሠ.ገጠም-ኩታ
ረ. ትምህርት-ስርዓት
ሰ. ድስት - ብረት

## ተግባር ሶስት

**የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. ህፃኑ ልጅ የብር ፍልቃቂ ይመስላል፡፡

   ሀ. በጣም ደስ የሚል　　ለ. አስቀያሚ

   ሐ. በጣም የሚያስጠላ　　መ.ነጭ የሆነ

2. የብር አሎሎ የመሰለው አይኗ አላፊ አግዳሚውን ያንከራትታል፡፡

   ሀ. ሞጭሟጫ　　ለ. ትንንሽ

   ሐ. ትልልቅ　　ሐ. ጌጣጌጥ

3. አፍንጫው ስንደዶ የመሰለ ነው፡፡

   ሀ. ደፍጣጣ　　ለ. አስጠሊታ

   ሐ. ቀጥ ያለ　　መ. የተጣመመ

4. የወተት አረፋ የመሰለው ጥርሷ ስትስቅ ላየው አፍ ያስከፍታል፡፡

   ሀ. ችምችም ያለ ጥርስ　　ለ. የበለዘ ጥርስ

   ሐ. ጉራማይሌ ጥርስ　　መ. በጣም ነጭ ጥርስ

5. የሌሊቱ ፅልመት ተገፎ ብርሃን ሲወጣ ሁሉም ሰው ከመኝታው ተስፋን ይዞ ይነሳል፡፡

   ሀ. ጨለማው ተወግዶ　　ለ. ጨለማው ተተክቶ

   ሐ. ብርሃን አስወግዶ　　መ. ምሽትን ቀይሮ

6. ሙዚቀኛው በራሱ ቅኝት የራሱን ቅላፄ በመፍጠር ሙዚቃ አወጣ፡፡

   ሀ. ጩኸት　　ለ. እንጉርጉሮ

   ሐ. ሙሾ　　መ. የዜማ አይነት

## ተግባር አራት

**በምሳሌው መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላዱን በመለየት በሰንጠረዥ ውስጥ ጻፉ፡፡**

| ተ/ቁ | ቃላት | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ1 | ልጆቻቸውን | ልጅ | - ኦች- ኣቸው - ን |
| 2 | ሴትነት | ሴት | - ነት |
| 1 | ገበሬዎች | | |
| 2 | ባርኔጣቸው | | |
| 3 | ደብተሬ | | |
| 4 | ቤታቸው | | |
| 5 | ዘመዶቻቸውን | | |
| 6 | እርሳሶች | | |
| 7 | ቤተሰቦቻችሁን | | |

## ክፍል አራት:- ጽሕፈት

### የህይወት ታሪክ

ማስታወሻ

የህይዎት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ

- የህይወት ታሪክ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ሲኖር አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተግባሮችን ሊያከናውን ይችላል፡፡ መልካም ነገርን ለትውልድ ያበረከተ ሰው ስሙ ለዘላለም ሲወደስ፣ለሀገርና ለወገን ኩራት እንደሆነ ይኖራል፡፡‹‹መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውላል›› የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡ ይኸውም የራስ የህይወት ታሪክና የግለሰብ የህይወት ታሪክ በመባል ይታወቃል፡፡

  የራስ የህይወት ታሪክ

- የራስ የህይወት ታሪክ የሚባለው አንድ ሰው በህይወት እያለ የራሱን የህወት ታሪክ ራሱ ሲጽፈው ነው፡፡

- የራስ ህይወት ታሪክ ለመፃፍ የሚያስብ ሰው ከስሜት ነፃ ሆኖ ሳንጨምር ሳንቀንስ መፃፍ እንዳለበት ማመን ይገባዋል፡፡ ከዚያም የሚከተሉትን መመሪያዎች በመከተል መፃፍ ይቻላል፡፡
    - ○ የትውልድ ስፍራና የትውልድ ዘመንን መግለፅ
    - ○ ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መግለፅ
    - ○ የትምህርት ደረጃን መግለፅ
    - ○ በህይወት ዘመን ያበረከቱትን ጉልህ አስተዋፅዖዎች በቅደም ተከተል መፃፍ
    - ○ ታሪኩን በቅደም ተከተል ማደራጀት
    - ○ ታሪኩን በቀላልና በግልፅ የቋንቋ አጠቃቀም ማቅረብ፡፡

የግለሰብ የህይወት ታሪክ

- የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ በሌላ ጸሀፊ ሲጻፍ የግለሰብ የህይወት ታሪክ ይባላል፡፡ የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ሰውየው በህይወት ዘመኑ እያለ ያበረከተውን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተዋፅዖ ሳንጨምር ሳንቀንስ መጻፍ አለበት፡፡
- የህይወት ታሪክ ልቦለድ ወይም የፈጠራ ስራ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ማለት ግን ፀሀፊው እንጨት እንጨት ባለ የቋንቋ አጠቃቀም ታሪኩን እንደወረደ ያቅርበው ማለት አይደለም፡፡
- የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡
    - ○ ታሪኩ ስለሚፃፍለት ግለሰብ የተፃፉ ፅሁፎች ካሉ በማንበብ አልያም ግለሰቡን የሚያውቁ ሰወችን በማነጋገር መረጃ ማሰባሰብ
    - ○ ግለሰቡ የተወለደበትን ቦታና የትውልድ ዘመን መግለፅ
    - ○ ስለ አስተዳደጉ ሁኔታ በዝርዝር ማቅረብ
    - ○ የግለሰቡን የትምህርት ደረጃ መግለፅ
    - ○ ግለሰቡ ያበረከታቸውን አስተዋፅዖዎች መፃፍ

- የግለሰቡን አጠቃላይ ታሪክ ቀላልና ግልፅ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀምመግለፅ
- ግለሰቡ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ የሞተበትን ዘመን መፃፍ
- ስለ ግለሰቡ ታሪክ መረጃ የሰጠን አካላት በማመስገን መግለፅ
- ስለግለሰቡ የተነበበ መፅሀፍ ካለ በዋቢነት ማቅረብ፡፡

ተግባር አንድ

**መምህራችሁ ደቂቃ ይያዙላችሁና ከዚህ በታች የቀረበውን የህይወት ታሪክ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አንብቡ፡፡**

**ጳውሎስ ኞኞ**

ጳውሎስ ኞኞ ቁልቢ አካባቢ ህዳር 11 ቀን 1926ዓ.ም ተወለደ፡፡ ትምህርቱን ከአራተኛ ክፍል ቢያቋርጥም ላዛሪስት ሚሽን አዳሪ ትምህርት ቤት ገብቶ ነበር፡፡ ዳሩ ግን እናቱ ገና የሁለት አመት ህፃን ሳለ ከአባቱ ጋር ተለያይተው ስለነበር በተዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ ይዘውት እየሄዱ ነበር ያሳደጉት፡፡ ከእናቱ ጋር መሆን ኑሮን ለማሸነፍ የተጠቀመባቸው አያሌ የስራ አይነቶችና ስልቶች የጳውሎስን ብልህና ብሩህ አዕምሮ ያሳያሉ፡፡ እንቁላል፣ ፓስታ፣የሎሚ ጭማቂ ራሱ እየጨመቀ፣ ጭራ፣ የመላዕክትና የአርበኞችን ስዕል እያዘጋጀ ይሸጥ ነበር፡፡

በወር ስምንት ብር እየተከፈለው በእርሻ ሚኒስቴር ውስጥ ስራ የጀመረው ጳውሎስ የኋላ ኋላ በጽሕፈት ሰራተኝነት ወደ ጤና ጥበቃ ተዛውሮ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገባ፡፡ በዚሁ ስፍራ ላይ እያለ ለጋዜጣ አንዳንድ ጽሑፎችን መላክ ጀመረ፡፡ ቀስ በቀስ እጁን እያፍታታ ወደ ስነ-ፅሁፍ ሙያ ብቅ ሲል የጋዜጠኝነት ዓለም ጠራው፡፡ ያን ጊዜ ‹‹የኢትዮጵያ ድምፅ›› የምትባልና በሀገር ፍቅር ስር የምትተዳደር ሳምንታዊ ጋዜጣ ነበረች፡፡ ጳውሎስ ሰማንያ ብር የሚገኝበትን ስራ ትቶ በሀምሳ ብር ደመወዝ የድምፅ ጋዜጣ ሰራተኛ ሆነ፡፡ ችሎታውን የተመለከቱ ሀላፊዎችና ባለስልጣኖች እውቅ ጋዜጠኛ እንደሚወጣው ተነበዩለት፡፡

የብዕሩንም ድምፅ በድምፅ ጋዜጣ በኩል ማሰማት ጀመረ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ በታደለው የማስተባበር፣ የመቀስቀና የማቀናጀት ጥበብ ጋዜጣዋን ለህዝብ በስፋት አስተዋወቀ፡፡ በዓመት አስር ሺህ ተገምቶ የነበረው የስርጭት ቁጥርም በወር ወደ ሰላሳ ሺህ ደረሰ፡፡ ይህም አዲስ ዘመን ጋዜጣን እንዲወድቅ(ገበያው በእጅጉ እንዲቀንስ) በማድረጉ

ጳውሎስ በመንግስት ባለስልጣኖች ተግሳፅ ደረሰበት፡፡

ጳውሎስ የተቸገረን መርዳት ቋሚ ተግባሩ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ የፈፀመው ተግባር አያሌ ቢሆንም በተለይ በ1965ዓ.ም ከወሎ በረሀብ ተሰደው የመጡ ወገኖቻችንን አንድ ቦታ አሰባስቦ ‹‹የተራቡ ወንድሞቻችንን ፋሲካን እናስፈስክ!›› የሚል ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አውጥቶ ተገቢውን እርዳታ ማድረጉ ይታወሳል፡፡
ጳውሎስን በጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሰርቷል፡፡ከዚህ ውጭ የአራዳው ታደሰ፣ የጌታቸው ሚስቶች፣የኔዎቹ ገረዶች፣አስደናቂታሪኮች፣የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት፣ አፄ ምኒልክ ወዘተ. መጽሐፍትን ደርሶና አዘጋጅቶ ለህዝብ አቅርቧል፡፡ይህ በራሱ ከፍተኛ ትግልና ጥረት ካሰበው ግብ ለመድረስ የበቃ ህዝባዊና ተወዳጅ ጋዜጠኛ ግንቦት 29 ቀን 1984ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡

ምንጭ፦ (አለም እሸቱ ፣ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ 1999፣88-89)

## ተግባር ሁለት

ሀ. ከላይ ያነበባችሁትን የህይወት ታሪክ በድጋሜ ስርዓተ ነጥቦቹን ጠብቃችሁ

ድምጻችሁን በማሰማት አንብቡ፡፡

ለ. ጳውሎስ ኞኞ  በሚል ርዕስ የቀረበውን የህይወት ታሪክ ገምግሙና የጽሑፉን

አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች ለይታችሁ በማውጣት በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

## ተግባር ሶስት

የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን ተከትላችሁ የአንድ ግለሰብየህይወት ታሪክፃፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### ርቱዕ/ቀጥተኛና ኢ-ርቱዕ/ቀጥተኛ ያልሆነ

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ተቀላቅለው የቀረቡትን ቃላት ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ በማለት ለይታችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ ፃፉ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በላ | ተደበደበ | ሰበረ | ፈላ | ተሰበረ |
| ተለወጠ | ተመታ | ተሰነጠቀ | ተሰራ | ሳለ |
| ሸለመ | ጠጣ | ተበላ | ተሰወረ | ተቀየረ |
| ሳጠ | መታ | ፃፈ | ተወዳደረ | |

| ተ/ቁ | ርቱዕ | ኢርቱዕ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ሳጠ | ተመታ |
| | ፈላ | ተሰበረ |
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |

**ተግባር ሁለት**

**የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ወደ ኢርቱዕ በመቀየር በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።**

ምሳሌ፡-ፈጨ - ተፈጨ

ፈለጠ - ተፈለጠ

ሀ. ረሳ
ለ. ሰረቀ
ሐ. ጋገረ

መ. መረቀ

ሠ. መከረ

ረ. ቀባ

## ተግባር ሶስት

**የሚከተሉትን ቃላት ርቱዕ እና ኢርቱዕ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ቀጠለ

ርቱዕ = አለሙ የተቋረጠውን የመብራት ገመድ ቀጠለ፡፡

ኢርቱዕ = ተቋርጦ የነበረው የመብራት ገመድ በአለሙ ተቀጠለ፡፡

ሀ. ባረከ ሐ. ቦጨቀ ሠ. ለወጠ

ለ. ቆለፈ መ. ፈለገ ረ. ነቀለ

**ማጠቃለያ**

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በምንባቡ መሰረት ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት የቻልን ሲሆን አውዳዊ ፍች ማለት ቃላት እንደ አገባባቸው የሚሰጡት ትርጉም ማለት ነው። በሌላ በኩል ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺዎችን ለመስጠት ሞክረናል። ቃላትን እርስ በእርሳቸው በማጣመር ድርብ ቃል መስርተናል። ድርብ ቃል ማለት የተለያየ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በማጣመር ቃላቱ በፊት ከሚሰጡ ፍቺ የተለየ ፍቺ እንዲሰጥ ማድረግ ነው። እንዲሁም ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተን በመጻፍ አሳይተናል። በመጨረሻም የህይዎት ታሪክ የራስና የግለሰብ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል አይተናል። የራስ የህይወት ታሪክ አንድ ሰው የራሱን የህይወት ታሪክ ሲጽፍ ሲሆን፣ የግለሰብ የህይወት ታሪክ ደግሞ የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ በሌላ ጸሀፊ ሲጻፍ እንደሆነ ተረድተናል።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ስጡ።

   ሀ. ሀራጅ　　　　ሐ.ማጀት

   ለ. መሰሪ　　　　መ.ማሞካሸት

2. የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱ።

   ሀ. ገጠም- ኩታ　　　　ሐ. አደር-ላብ

   ለ. መንግስት-ቤተ　　　　መ. አደር-አርብቶ

3. የሚከተሉትን ቃላት በነፃና ጥገኛ ምእላዶች ለይታችሁ ጻፉ።

   ሀ ደስታችንን　　　　ሐ.ተማሪዎቻችሁን

   ለ. ስልጣኑን　　　　መ. መለኮታዊነቱን

4. በራስ እና በግለሰብ የህይወት ታሪክ አጻጻፍ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለፁ።

## የቃላት ፍቺ

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ሁለንተናዊ | ስመና፣ጠቅላላ አካል፣መላ ሰውነት |
| ህቡዕ | ድብቅ፣ ሚስጥራዊ፣ ይፋ ያልሆነ |
| ህብር | የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር፣ጠባይ፣ ባህሪ፣ ለዛ |
| ሙዳ | በልክ በልክ የተቆረጠ የስጋ ቁራጭ |
| ማህበር | ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ድርጅት |
| ማሳ | ተደጋግሞ የታረሰ፤ የለማ መሬት |
| ማጀት | የምግብ ማብሰያ ክፍል፣ ጓዳ፣ ማድ ቤት |
| ምናብ | በስሜት ህዋሳት የማይደረስባቸውን ነገሮች በህሊና እንዲደረስባቸው የሚያድርግ ተፈጥሮአዊ ሀይል |
| ሞፈር | የእርሻ መሳሪያ፣ የገበሬ ማረሻ እቃ፣ |
| ቀንበር | በእርሻ ጊዜ በሁለቱ በሬዎች ትከሻ ላይ የሚቀመጥ በምራን የሚታሰር የእርሻ መሳሪያ ነው |
| ቀውስ | እብድ ፣ ወፈፌ፣ ንክ |
| ቆፈን | ብርድ፣ ቅዝቃዜ፣ ውርጭ |
| ተግዳሮት | መኮፈስ፣ ትዕቢት፣ ማናለብኝነት፣ |
| ትውፊት | የተወረሰ እምነት፣ ነባር የአኗኗር አባባል፣ ወግ፣ታሪክ፣ ባህል |
| አርአያ | አምሳል፣የመልክ ምሳሌ፣ አብነት |
| አሻራ | ጣትን ቀለም አስነክቶ በማንኛውም ነገር ላይ ሲጫኑት የሚቀረው ምልክት፣ የቡና ገለፈት፣ገለባ |
| አውጫጭኝ | ወንጀል የሰራ ሰው ህዝቡ ተሰብስቦ ማጋለጥ፣ መጠቆም |
| አጥቢያ | አካባቢ፣ ሰበካ፣ ቀበሌ፣ቀዬ፣ ንጋት፣ ማግስት |
| እሾህ | በልዩ ልዩ ዛፎች ላይ የሚገኝ የሚዋጋ አሜከላ፣ ተንኮለኛ፣ ክፉ እንከን፣ ጥፋት፣ጉድለት፣ ህፀፅ፣ ነውር፣ ነቀፋ |

| | |
|---|---|
| እውን | ምናባዊና ህሊናዊ ብቻ የሆነውን በራሱ ህልውና ካለውና ነባራዊ ከሆነው ለመለየት የሚጠቅም |
| ወንፊት | ከአክርማ፣ ከሰንደዶ የሚሰራ ማንዘርዘሪያ፣ ወሬኛ |
| ዝርያ | የትውልድ ሀረጉ የሚታወቅ፣ በደም ግንኙነት የተሳሰረ ዝምድና |
| ደባ | ተንኮል፣ ሴራ፣ ተሸሸገ፣ተደበቀ |
| ጥበብ | ዘዴ፣ዕውቀት |
| ፅልመት | ጨለማ ፣ጥቁረት |

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀሳቡን ጣለ | ተረጋጋ |
| ሆዱን ሰጠ | ሚስጥሩን ገልጦ አወያየ |
| ልቡ ተነሳ | ለመሄድ ተቻኮለ |
| መንታ ልብ | ወላዋይ |
| ስመ ጥር | ታዋቂ |
| ቃሉን ሰጠ | መሰከረ |
| ነብር ሆነ | ተቆጣ |
| አድሮ ቃሪያ | የማይሻሻል |
| የቀለም ቀንድ | ምሁር |
| የውሃ ሽታ | ደብዛው የጠፋ |
| ደሙ ፈላ | ተናደደ |
| ድርብ ድል | በስኬት ላይ ስኬት |
| ጆሮ ሰጠ | አዳመጠ |
| ግብረ ገብ | መልካም ስነ-ምግባር |

## ዋቢ ጽሑፎች

ሀዲስ አለማየሁ፡፡ (1996 ዓ.ም)፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሔኖክ ያሬድ፡፡ (2005 ዓ.ም)፡፡አበበ ቢቂላ የተወለደው  መቼ ነው፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ

መዘመር ግርማ (2011 ዓ.ም)፡፡ ሁቱትሲ የወጣቷ ልብ አንጠልጣ  ትውስታዎች የትርጉም ስራ፡፡

ማርታ እሸቱና ነፃነት ጌትነት፡፡ (2004 ዓ.ም) ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 10ኛ ክፍል፡፡አዲስ አበባ፣በት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ሜሪ ጀን ግሌይና ሳባ ገ/መድህን ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ ተምሳሌት፡፡ ፅሀይ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራዊ ቅንጅት አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሰለሞን ሐለፎም፡፡(1997 ዓ.ም) ፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድጅት፡፡

ሳሙኤል አየለና ታሪኳ መላኩ፡፡ (1997 ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሳባ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡(2005 ዓ.ም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስትቲትዩት፡፡(1995 ዓ.ም)፡፡ የኤች አይ ቪ ኤድስ ትምህርት፡፡አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፡፡ (2009 ዓ.ም)፡፡ ኪንና ባህል፣ታትሞ ከወጣው ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2010 ዓ.ም)፡፡ አጭርና ቀላል  የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታለጌታ ይመር፡፡(2007 ዓ.ም)፡፡ ሁለገብ  የአማርኛ  ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፣ሴቭ ዘ ችልድረን እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጋራ ትብብር፡፡ (2008 ዓ.ም)፡፡ ለምግብነት የሚውሉ የጓሮ አትክልቶች በሚል የተዘጋጀ  አጋዥ መፅሀፍ፡፡

አለም እሸቱ፡፡(1999 ዓ.ም)፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7-10ኛ ክፍል፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለቃ ደስታ ተ/ክለወልድ፡፡(1962ዓ.ም)፡፡ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ (1981 ዓ.ም)፡፡ በአለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ  ድርጅት፡፤

ዘሪሁን አስፋው ፡፡(2004 ዓ.ም)፡፡  የስነ-ጽሑፋፍ መሰረታውያን፡፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት፡፡ ባህርዳር፣(ያልታተመ)፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፡፡(2007ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ (2012 ዓ.ም)፡፡ የጥላቻ ንግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፡፡ሀያ ስድስተኛ አመት ቁጥር 26 ገፅ 12339፡፡ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም መተሚያ ድርጅት፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡(1996 ዓ.ም) ፡፡ተግባራዊ የፅህፈት መማሪያ፡፡አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፡፡(2008 ዓ.ም)፡፡ ኮሜት አጋዥ መፅሃፍ ከ9-10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(2009 ዓ.ም)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ፋንታሁን እንግዳ፡፡ (2000 ዓ.ም) ፡፡ ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ፡፡ አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 | |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 | |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 | |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | | |

# አማርኛ

## እንደመጀመሪያ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ

## ፯ኛ ክፍል